ምዕራፍ 5

እርስ በርስ ተያይዞ የመኖር ጥበብ

ምዕራፍ አምስት

እርስ በርስ ተያይዞ የመኖር ጥበብ

ቤተሰብ ጠንካራ እንዲሆን ጥበብ ምንኛ አስፈላጊ እንደሆነ በዚህ ክፍል እንመለከታለን። ቀደም ብለን ባየናቸው የተለያዩ ርዕሶች ላይ ጠንካራ ክርስቲያናዊ ቤተሰብን ለመመሥረት እና ለማጽናት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥም እንዳለ እንደ አንድ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ፍሬያማ ይሆንም ዘንድ አስፈላጊ ናቸው ያልናቸው ነጥቦች እንደ ተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ ጥበብ ደግሞ ምን ሚና እንዳለው እንመለከታለን።

የአማኝ ቤተሰብ ወይም ጠንካራ ቤተሰብ ብለን የምንጠራው ዓይነተኛ ቤተሰብ አንድነቱ ጎብረቱ የሚመነጨው ከውጪ ያለውን በማየት "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ" በሚለው መርህ ሳይሆን ከውስጥ እርስ በርስ በመያያዝ ውስጥ በሚተገበረው ጥበብ ወይም ዘዴ ነው።

"ጥበብ ቤቷን ሠራች፤ ሰባቱን ምሰሶዎቿንም ጠርባ አቆመች" (ምሳሌ 9፡1)።

በጥበብ የተሠራ ቤት እንዴት ያለ ግሩም ቤት ይሆን። እነዚህስ ሰባት ሞሰሶች ምን ይሆኑ?

ዛሬ ምናልባትም ጠንካራ ቤተሰብ ብለን በምናየው በዚህ ጎብረት ወይም ቤተሰብ ውስጥ እርስ በርሳቸው በአንድነት ተያይዘው እንዲቆዩ፤ ግን ደግሞ እያንዳንዱ ግለሰብ ልዩነቱ ተጠብቆ እንዲኖር የሚያስፈልጉ እነዚህ ሰባት ትላልቅ ምሰሶች ምን ይሆኑ? ብዬ አስባለሁ። እነዚህን ሰባት ምሰሶች እንደሚከተለው ልዘርዝራቸው። መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 14፡1 *"ብልሃተኛ ሴት ቤቷን ትሠራለች፤ ሰነፍ ሴት ግን በእጇ ታፈርሰዋለች"* ይላል። ቤት ሰው የሚሰራው የሚያፈርሰውም ነገር ነው። ሰው ቤቱን ሊሰራ የሚችለው ጥበብን፣ ማስተዋልን እና ዕውቀትን ከእግዚአብሔር ሲያገኝ ነው። ልክ ቤት በጥበብ እንደሚሰራው ሰው ቤቱን፣ ትዳሩን አጠንክሮ መስራት ይችላል፤ ራሱን ለስንፍና አሳልፎ ከሰጠ ደግሞ ቤቱን ማፍረስ ይችላል።

በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 24፡3-4 ላይ ቤት *"በጥበብ ይሠራል፤ በማስተዋልም ይጸናል፤ በዕውቀትም ውድና ውብ በሆነ ንብረት ክፍሎቹ ይሞላሉ"* ይላል። እግዚአብሔር ሰውን በእንዲህ ያለ ዕውቀት ይሞላል። ቤታችንን እና ትዳራችንን የሚሰራባቸውንና በውስጣቸው ከላይ ያነሳናቸውን ሰባት ምሰሶዎችን የያዙትን በእነዚህ ሦስት ነገሮች ማለትም በዕውቀት፣ በማስተዋል እና በጥበብ ከፋፍለን እንመልከታቸው።

በመቀጠል ደግሞ ስለ ሦስት ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም ስለ ተግባቦት፣ መሰጠት እና መያያዝ እንመልከት።

ሀ. ተግባቦት (Communication)

ሰው የተነገረውን በትክክል አዳምጦ የተባለው ነገር እንደገባው የሚረዳበት ጥበብ ያስፈልገዋል። በሰዎች መካከል መግባባት ሲጠፋ በሕይወት ውስጥ ዋጋ የሚያስከፍል ነገር ሊፈጠር ይችላል። ተግባቦት ወይም ግንኙነት ምን ያህል ከኀልውና ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለው ለማሳየት ከጦር ሜዳ የተሻለ ምሳሌን ማቅረብ አይቻልም።

በጦር ሜዳ ዛሬ ላይ ሥራ ላይ በመዋል ያገለገለው የግንኙነት ኮድ ለነገ አያገለግልም። በሬዲዮ ግንኙነት ኮድ ከነመፍቻ ቁልፉ እጅግ አስፈላጊ ነው። ደግሞም ወታደሮች እዚያው ጦር ሰፈር ውስጥ ወይም በውጊያ አውደ ግንባር ላይ በምሽት ሲንቀሳቀሱ ድንገት መነጋገር ቢያስፈልጋቸው የዕለቱን መነጋገሪያ ኮድ ማወቅ ይጠበቅባቸዋልና ያንን ኮድ ከበላይ አለቆቻቸው መቀበል አለባቸው።

አንድ ወቅት ላይ አንድ የጦር አዛዥ የዕለቱ የግንኙነት ኮድ ግንኪያ ሹካ መሆኑን ለበታች ወታደሮቹ ያስታውቃል። አንዱ ወታደር "ሹካ!" ሲል ሌላው "ግንኪያ!" ማለት ነው የሚጠበቅበት። በዚህ ዓይነት መንገድ እርስ በርሳቸው ጉዳት ሳይደራረሱ እና የማያስፈልግ አደጋ ሳይፈጥሩ ሌሊቱን በሰላም ይንቀሳቀሳሉ።

ይህንን ኮድ በቅጡ ያልተረዳው አንድ ወታደር በምሽት ሲዘዋወር ተበታትነው በጥበቃ ላይ የተሰማሩ ሌሎች ወታደሮች ጠመንጃቸውን አቀባብለው አሳቻ ቦታ ላይ ያገኙትን ይህን ወታደር የዕለቱን ኮድ ሲጠሩለት እርሱ ግን በድንጋጤ ትናንትና አገልግሎት ላይ ውሎ የነበረውን ኮድ "ሞልፋ" ብሎ ጠራላቸው። ከዚህ በኋላ ምን እንደ ተከተለ የምናውቀው ነገር ነው።

አምን የተግባቦት በቅጡ አለመኖር ሕይወትን የሚያክል ክቡር ነገር ለማያስፈልግ መስዋዕትነት ይዳርጋል። የሰው ሕይወት እርባና እንደ ሌለው አንዳች ነገር በከንቱ ወድቆ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል። ልክ እንደዚሁ በቤተሰብ አባላት መካከልም የጤነኛ ተግባቦት አለመኖር ወይም መዛባት መዘዙ ብዙ ነውና ሊጤን ይገባል።

ልጅቷ አንድ ጊዜ አባቷን "እባክህን አባቢ አንድ ነገር አድርግልኝ?" አለችው። "ምን ላደርግልሽ?" ብሎ ቢጠይቃት "ከእናቴ ጋር ስትጣሉ ወይም በሃሳብ ልዩነት ስትከራከሩ ጥራኝ" አለችው። እንግዲህ አባት ከእናትዬዋ ጋር ሲጋጭ ልጅቷን ሲጠራ ይታያችሁ። አባትም "ለመሆኑ ይህንን ለምን ፈለግሽው?" ብሎ ጠየቃት። "ለሁለት ነገር" አለችው። እነዚህ ሁለት ያለቻቸው ነገሮች ግን በጣም ጠቃሚ ናቸው።

"አንደኛው መቼም ስትጣሉ ገጥሞኝ ስለማያውቅ ነው እንጅ መጣላታችሁ አይቀርም። እኔ እና እናትሽ ተጣልተን እናውቅም፣

አንጣላምም ብትለኝ ደግሞ አላምንህም፡፡ ምክንያቱም አይደለም አብረው የሚኖሩ ሰዎች ሌላም ሰው እንኳ ይጋጫል፣ ይጣላልም፡፡ ሳይጣሉ የሚኖሩ ሰዎች ያሉ አይመስለኝም፣ በበኩሌ ሊኖሩ አይችሉም ብዬ ነው የማምነው፡፡ እናም መጋጨታችሁ አይቀርም፣ እኔ ግን አሁን የምፈልገው ሁለተኛው ነገር ስትጋጩ ልዩነቶቻችሁን እንዴት እንደምትፈቱ ለመማር ወይም ለማወቅ ስለምፈልግ ያንጊዜ ጥራኝ" አለችው፡፡

ግጭት በተለያየ መንገድ እንደሚፈታ ይታወቃል፡፡ አንዳንዱ በቡጢ፣ አንዳንዱ ደግሞ "ቆይ ጠብቀኝ፣ ጉድህን አደባባይ አወጣልሃለሁ፣ የምትሰራኝን ሥራ ሁሉ ሄጄ ለቤተ ክርስቲያን እነግርልሃለሁ" ነው የሚባባሉት? ወይንስ ምድጃ ላይ እንደ ተጣደ ጀበና የሚንተከተከውን ጊዜያዊ ስሜታቸውን ጸጥ በማሰኘት እንደ ባለ አዕምሮ ጉዳዩን በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ይነጋገራሉ?

ልጓም የሌለውን ሌጣ ፈረስ እንደሚጋልብ ሰው በስሜት ሽምጥ ይነጉዳሉ፣ ወይስ የተሸከሙት የቤተሰብ ኃላፊነት ከብዷቸውና በእጃቸው ላይ ያለው የልጆቻቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ግድ ብሏቸው ርቱዕና ጤናማ የግንኙነት መስመር ፈጥረው ይወያያሉ? ለትክክለኛስ ለውጥ ተግተው ይሰራሉን? የሚያስፈልገው ይሄ ነው፡፡

ግጭት ካለ ግጭቱን ለመፍታት የሚረዳ አንዳች ዘዴ መኖር ይኖርበታል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው ጥበብ *"ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፣ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣*

ለመናገር የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሰራምና" (ያዕቆብ 1፡19) ብሎ እንደ መከረን ልንኖር ይገባል፡፡ ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን የሚመጣው ነገር አያድርስ ነው፡፡

የተግባቦት ዋነኛው ነገር ማድመጥ ነው፡፡ በባል እና ሚስት እንዲሁም በልጆች እና በወላጆች መካከል ተግባቦት እንዲኖርና ነገሩ ጠርቶ እንዲወጣ ለማድረግ በመጀመሪያ የሚያስፈልገን ጥበብ መደማመጥ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌ 18፡13 ላይ ሲናገር *"ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ፣ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል"* ይላል፡፡ አንድን ነገር ሳይሰማ በመሰለኝ እንደሚመልስ ሰው ማለት ነው፡፡ የተባለውን ነገር ሳይሰማ በመሰለኝ ካወራውና ቤቱ ተቃጥሎ ከባድ ጥፋት ካደረሰ በኋላ፤ "ውይ እኔ እኮ እንዲህ ያልክ መስሎኝ ነው" ብሎ በሚመልስ ሰው ውጤቱ ስንፍና እፍረት ነው የሚሆንበት፡፡ ስለዚህ ወገኖቼ ማዳመጥን እንምረጥ፡፡ ችግር ካለ መስማት ነው የሚሻለው፡፡ ስንሰማው የበለጠ እንረዳዋለን፡፡ እንዲያውም እርግጠኛ ለመሆን ከፈለግን ምን ማለቱ እንደሆነ ተናጋሪውን መልሰን እንጠይቀው፡፡ በደንብ በሰማን ቁጥር አስተውለን ለመናገር እንችላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ይህንን ነው፡፡

አዳማጮች በትክክለኛው ተግባቦት ውስጥ ሆነን መስማታችንን ብቻ ሳይሆን ለምንመልሳቸው ቃላትም ትኩረት እንስጥ፡፡ አንዳንድ ጊዜ "እኔ አፌ እንጂ ልቤ እኮ በጣም ንጹህ ነው፡፡ በሆዴ ነገር አልይዝም፡፡ ብቻ ትንሽ ስናገር ሰው ሁሉ ጥምድ አድርጎ ይይዘኛል" እንላለን፡፡ አያችሁ ስህተቱ እዚህ ላይ ነው፡፡ ከአንደበታችን

የሚወጡት ቃላት እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። ትክክለኛ ተግባቦት ይኖር ዘንድ የንግግራችን ይዘት እንዴት ፋይዳ ቢስ ይሆናል? ዋጋ አለው። መጽሐፈ ምሳሌ *"በከንፈሩ ከሚወሳልት ሰነፍ ይልቅ ያለ ነውር የሚሄድ ድሃ ይሻላል" (ምሳሌ 19:1)* ብሎ ነው የሚናገረው። ይህ ማለት ሰው በከንፈሩ ከሚወሰልት ይልቅ ድሃ ሆኖ ጥሩ ማንነት ኖሮት ስለ ቃሉ ቢኖር ይሻላል ማለቱ ነው። የምንናገራቸው ቃላት በጣም ኃይል አላቸው። የተፈጠርነውና ዳግም የተወለድነው እኮ በቃል ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የምናደርገውም በቃል ነው። በመንፈሳዊ ውጊያዎቻችን ላይ ትልቁ መሳሪያችን ቃል ነው። በግንኙነታችን ውስጥ ተግባቦታችን የሰመረ እንዲሆን ከአፋችን ለሚወጣው ቃል ይዘት መጠንቀቅ ይኖርብናል።

በቅድሚያ አሁን ለዚህ ሰው የምነግረው ነገር እውነት ነው ወይ? ብሎ መጠየቁ መልካም ነው። ከመናገር በፊት እውነት ነው ወይ ብሎ ራስን መጠየቁ እውነትን መናገራችንን ማረጋገጥ አለብን።

በሁለተኛ ደረጃ የምንናገረው ነገር ደግሞ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው ወይ? አይገርምም? ሙሉ እውነት እና ጎደሎ እውነት የሚባል ነገር እኮ አለ። ሰው የሚስማማውን ብቻ ሸርፎ እና ሸራርፎ መናገር ስለሚችል ነው።

ሦስተኛ የምንናገረው ነገር አስፈላጊ ነው ወይ? ላልናገር ልተወው የምችለውን ነገር መተው በተግባቦት ውስጥ ሰላም እንዲጠበቅ ያደርጋል። "ከአፍ የወጣ አፋፍ" እንደሚባለው አነጋገር አንድ ጊዜ ከአፋችን ያመለጠንን መመለስ አንችልም።

አራተኛ የምንናገረው ቃል ሰሚውን ይጠቅመዋል ወይ? ያንጸዋል ወይስ ይጎዳዋል? እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎችን መጠየቁ ጥሩ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ መልዕክቱ ምዕራፍ 4፡6 ላይ ሲናገር *"ለእያንዳንዱ ሰው እንዴት መልስ መስጠት እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ በጨው እንደ ተቀመመ ሁልጊዜ በጸጋ የተሞላ ይሁን"* ይላል። ይህ ማለት መስማት ብቻም ሳይሆን ከአንደበታችሁ አውጥታችሁ ስለምትናገሩት ቃል ይዘት ተጠንቀቁ ማለቱ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ሰምተን ደግሞም ለቃላችንም ተጠንቅቀን ጥበብ ይጎድለናል። ይህ የሚጎድለን ጥበብ ምንድነው? የምንናገረው ነገር ትክክል ሆኖ የምንናገረውን ቃል እንወቅ፤ ደግሞም ሰሚም እንሁን። ሌላው ሰውዬውን በደንብ ሰምቼውና ምን እንዳለ ገብቶኝ የምመልሰውን አስተካክዩ ይገር መጥቼ እንኳን አንድ የሚጎድለኝ ጥበብ አለ። ያም ጥበብ ስለምናገረው ነገር ጊዜ እና ቦታ መምረጥ ነው። ለተግባቦት ጊዜ እና ቦታ መምረጥ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

መጽሐፈ ምሳሌ 15፡23 ላይ *"ሰው ተገቢ መልስ በመስጠት ደስታን ያገኛል፤ በወቅቱም የተሰጠ ቃል ምንኛ መልካም ነው"* የሚል ቃል አለ።

አንድ ቃል በጊዜው እና አለጊዜው ሲነገር ትልቅ የትርጉም ልዩነት ይፈጥራል፣ ውጤቱም እንደዚሁ ይለያያል። ትዝ ይላችኋል ልባሟ ሴት አስቴር ያለችው? ይህች ሴት ለንጉሡ የምትናገረው የተጨበጠ እና እውነትነት ያለው ጉዳይ ነበራት።

አስቴር ዘመዶቿን ሊፈጁባት እንደሆነና ዘመዶቿን ሊፈጅ የተዘጋጀው ሰውም ማን እንደሆነ አውቃለች። ነገሩ ሙሉ በሙሉ እውነት በመሆኑ አስቸኳይ ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነበር። እናም ስለዚሁ ጉዳይ ለንጉሡ ለመንገር ንጉሡ የራት ግብዣ አዘጋጅታ ንጉሡ እንዲገኝላት ጠራችው። ንጉሡም ጥሪዋን አክብሮ እንደተገኘ ፊቱን ትኩር ብላ አየችው። ሆኖም የንጉሡ ፊት ጥሩ አልነበረምና የያዘችውን ጉዳይ ለመንገር ጊዜው አለመሆኑን በመረዳት ሌላ ግብዣ አዘጋጅታ ልትነግረው በማሰብ ለጊዜው ወገኖቿ ያሉበትን ችግር ላለመንገር ወሰነች። ይህን ርምጃ በወሰደች ሰዓት ወገኖቿ ከፍተኛ ድንጋጤና ጭንቀት ውስጥ ነበሩ። የእርሷም ሆነ የወገኖቿ ጠላት የሆነው ሰው የመሰቀያውን ግንድ መትከል ነበረበትና። ወገኖች ሆይ! ትክክለኛውን ጊዜ እና ቦታ ለማግኘት ቀስቱን ወይም ፍላጻውን አነጣጥሮ መወንጨፍ ተገቢውን ዒላማ እንዲያገኘው ያደርገዋል።

እግዚአብሔር ከሰው ጋር መግባባትን የሚወድ አምላክ ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ስለ ተግባቦት ከ2500 በላይ ጥቅሶች ተጠቅሰው እናገኛለን። እግዚአብሔር ሰውን ለማነጋገር ስለሚፈቅድ የሚያነጋግረን በየራሳችን ቋንቋ ነው። የግንኙነታችን ደረጃ መውደቅንም ሆነ መነሳትን ሊያመጣልን የሚችል ነገር በመሆኑ

ከእርሱ ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት ወይም ተግባቦት አቅልለን ልናየው አይገባም። ስለዚህ እርሱ ከሰው ጋር ጎብረት፣ ግንኙነት ለማድረግ ሥጋ ለብሶ የመጣ አምላክ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥበብን እና ማስተዋልን እንዲሰጠን አብዝተን ልንጸልይ ይገባል።

በዘፍጥረት ምዕራፍ አሰራ አንድ ላይ የተጠቀሱትና እነዚያ ግንብ ይገነቡ የነበሩ የባቢሎንን ሰዎች ታሪክ ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። ለመሥራት እኮ የሚከለክላቸው ነገር አልነበረም። ከሰማይ እግዚአብሔር አይቶ ከዚህ ድርጊት እንዲከለከሉ አንድ ነገር ብቻ ነው ያደረገው። እርሱም ቋንቋቸውን ደበላለቀው። ግንኙነታቸው ወይም ተግባቦታቸው እንዲበታተን፣ አንድ ቋንቋ እንዳይሆንላቸው አደረገ። ለምሳሌ አንድ ሰው ወዳጁን "ሚዶ ስጠኝ" ብሎ ከጠየቀ ሚዶ በአማርኛችን ምንድነው? ማበጠሪያ ነው። ሚዶ በፖልሽኛ ቋንቋ ግን ሳሙና ነው። ልክ እንደዚሁ የባቤል ግንብ ሠራተኞች መግባባት ተሳናቸው። የቋንቋ መግባባታቸው ስለ ተደበላለቀም ከመሥራት አይከለከሉም የተባሉት ሰዎች በምድር ላይ ሁሉ ተበትነው ቀሩ። እግዚአብሔር ከዚህ ይጠብቀን! እናም ተግባቦት ጌታን በትዳራችን፣ በቤተሰብ ግንኙነታችን ውስጥ ጠንካራ እና የሰመረ ቤተሰባዊ ተግባቦት እንዲሰጠን አስተምረኝ፣ ስጠኝ፣ አድርግልኝ ልንለው የሚገባን ነገር ነው።

ለዚህ እውነት ራሴን ምሳሌ አድርጌ ላቅርብ። ባለቤቴ አልሚ ሁልጊዜ የምትመክረኝ ነገር እላት። ይኸውም ምንድነው ሁሌ ከውጭ

ወደ ቤት ስትመጣና ገና በሩን ከፍተህ ስትገባ "ልጆች ለምን እንዲህ አደረጋችሁ? ማን ነው ይህን ያደረገው? ለምንስ ያንን እንደዚያ አላደረጋችሁትም? አትበል። የምትለው ነገር እውነት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ወደ ቤት ስትገባ መቅደም ያለበት ፈገግታ በተሞላ ፊት "እንዴት ዋላችሁ? ደህና አመሻችሁ?" በል። ከዚያ ሌላውን በተገቢው ጊዜ ትደርስበታለህ። እውነቷን ነው! የምንናገረው ነገር ጊዜና ቦታን የጠበቀ ካልሆነ በተግባቦት ላይ ትልቅ ተጽዕኖን ይፈጥራል።

ለ. መሰጠት

ሌላው ትልቁ እና ሁለተኛው ነገር መሰጠት ነው። መሰጠት ማለት ፈጽሞ መውደድ፣ ሁልጊዜ አብሮ መቆም፣ በጊዜውም አለጊዜውም ለአንድ ጉዳይ አልፎ መሰጠት እና መጣበቅ ማለት ነው። ይህንን ሃሳብ ለማብራራት በሉቃስ 9፡57-62 ያለውን ክፍል እንመልከት።

"በመንገድ ሲሄዱም አንድ ሰው ቀርቦ፣ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው። ኢየሱስም ቀበሮዎች ጉድጓድ፣ የሰማይ ወፎችም ጎጆ አላቸው፤ የሰው ልጅ ግን አንገቱን እንኳን የሚያሰገባበት የለውም አለው።

ሌላውን ሰው ግን ተከተለኝ አለው። ሰውዬውም ጌታ ሆይ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን ልቅበር አለው። ኢየሱስም ሙታን

ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ተዋቸው፤ አንተ ግን ሂደህ የእግዚአብሔርን መንግስት ስበክ አለው። ሌላ ሰው ደግሞ፤ ጌታ ሆይ መከተልስ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን ልመለስና መጀመሪያ የቤቴን ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለ።

ኢየሱስ ግን ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግስት የተገባ አይደለም አለው"።

ይህንን ጥቅስ ስለ ክርስቶስና ክርስቶስን ከመከተል ጋር ስናያይዘው በጣም ግልጽ ነው የሚሆንልን። ይህ ታሪክ የሚናገረው ስለ መሰጠት ስለሆነ በጣም ብዙ ትምህርት የምንማርበት ክፍል ነው።

የመጀመሪያው ሰውዬ ጌታን አይቶት በቃ እከተልሃለሁ አለው። ጌታ የሰውዬውን ልብ ሲያይ ግን ሙሉ በሙሉ አልተሰጠም። ሰውዬው የሚፈልገው ነገር እንዳለው ገባው። የቤት ጥያቄ ከሆነ እኔም ራሴን እንኳን የማስጠጋበት ቦታ የለኝም፤ ቤት ባይኖርም መሰጠት መኖር ስላለበት እንዲሁ በአገልግሎት መሳተፉ ብቻ በቂ አይደለም። መሰጠትም መኖር አለበት።

ሁለተኛው ሰው ደግሞ ጌታ ሆይ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን ልቅበር አለው። ይህ ችግር የለበትም። የዚህ ሰው ችግሩ የተሳሳተ ቅድሚያ መስጠቱ ነው። ይሄ ቅደም ተከተሉ የተዛባበት ሰው ነው።

ሦስተኛውም ሰው እንደዚሁ ደግሞ፤ ጌታ ሆይ መከተልስ

እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን መጀመሪያ ተመልሼ ሄጄ የቤቴን ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ ሲለው ዕርፍ ጨብጦ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ለእግዚአብሔር መንግስት የተገባ አይደለም ነው ያለው፡፡ መሰጠት ትኩረት ማድረግን የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ ጌታ ይህን ሲል የተሳሳተ ትኩረት ሲኖርህ መሰጠት አትችልም ማለቱ ነው፡፡ መሰጠት የምትችለው ትክክለኛው ትኩረት ሲኖርህ ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መሰጠት ትክክለኛ ቅድሚያ መስጠትን የሚጠይቅ ነገር ነው፡፡ መሰጠት የሚኖረው ትክክለኛው ትኩረት ሲኖርህ እና ትክክለኛ ቅድሚያ ስትሰጥ፤ በመሰጠት ስር እነዚህ ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ ትክክለኛ ትኩረት እና ትክክለኛ ቅድሚያ መስጠት፡፡

ወደ ተነሳንበት ጉዳይ እንመለስ፡፡ በቤተሰብ ህይወት ውስጥ ጠንካራ ቤተሰብ የሚመሠረተው መሰጠት ሲኖር ነው፡፡ መሰጠቱ የሚረጋገጠው ግን ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ ሁለት ነገሮች ሲኖሩ ነው፡፡ ሁልጊዜ ጠንካራ ቤት የሚሰሩ ሰዎች ቅደም ተከተል የሚሰጡት ነገር በጣም ግልጽ መሆን አለበት፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የነገራቸው እርሱ አንደኛ ሲሆን፤ ሁለተኛው ቤተሰባቸው፤ ሌሎች ነገሮችን ከዚያ በኋላ ማምጣት ትችላለህ፡፡ ሦስተኛው፤ አራተኛው፤ አምስተኛው ደረጃ ብለን ልንለያይ እንችል ይሆናል፡፡ ሁልጊዜ እግዚአብሔር ጠንካራ ቤተሰብ እንዲሰሩ የሰጣቸው ይህን የተረዱ ሰዎች በመሰጠት ጉዳይ ላይ ግልጽ የሆነ አቋም እና ትክክለኛው ትኩረት ያላቸው ናቸው፡፡ ሌላ ነገር እየሰሩ እንኳን ባሉበት ቅደም ተከተላቸው ትክክል ስለሆነ ምን እንደሚገኙ

የሚያውቁ ናቸው፡፡ ቃሉ በቤታቸው ውስጥ እና በቤታቸው ዙሪያ የሚከናወነው ነገር እንዴት ቤተሰቡ እየጠነከረ እንዲሄድ ማድረግን ያውቁበታል፡፡ አያችሁ መሰጠትና ዝም ብሎ ተሳትፎ ማድረግ ሁለቱ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ መሰጠቱ ሳይኖረን ዝም ብለን በብዙ ነገሮች ተሳትፎ ማድረግ እንችላለን፡፡

እነሆ አንድ ማሳያ ታሪክ፡- አንድ አሳማ እና አንዲት ዶሮ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ዶሮዋ "ጌቶቻችንን ቁርስ ሰርተን እናስደስታቸው" ስትል ሃሳብ አቀረበች፡፡ ከዚያም አሳማው አሰበ፤ አሰላሰለና ዶሮዋ ለቁርስ ከእሷ የሚጠበቀው ተሳትፎ እንቁላል መስጠት ብቻ ስለሆነበት አሳማው ግን ቁርስ ላቅርብ ብሎ ካሰበ የሚጠበቅበት ራሱን መስጠት መሆኑን ስለተገነዘበ በጉዳዩ እንደማይስማማ እንዲህ ሲል ነገራት ይባላል፡፡ "ጌቶቻችንን ቁርስ ሰርተን በማብላት ማስደሰቱ ለአንቺ መሳተፍ ብቻ ነው፡፡ ለእኔ ግን ራሴን መስዋዕት አድርጌ ማቅረብን ነው የሚጠይቀኝ"፡፡ በእርግጥም መሰጠት መስዋዕትነትን ይጠይቃል፡፡ መሳተፍ እና መሰጠት ሁለቱ በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ለአንድ ነገር ትኩረት ሲኖረን እና ቅደም ተከተሉ በትክክል ሲመጣ ትክክለኛው መሰጠት ይመጣል፡፡ እያችሁ መሰጠት በህይወታችን ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በተለይ በቤተሰብ ውስጥ ያለን ነገር እንደተያያዘ እንዲቆይ የምንፈልግ ከሆነ ትክክለኛ ትኩረት ሊኖረን ይገባል፡፡ መሰጠት አለብን ካልተሰጠን ትዳሩ፤ ቤቱ፤ አይሰራም፤ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ጠላት የሚፈትሸውም ያንን ነው፡፡

ለሲያኖ የተባለ ዘፋኝ ግለ-ታሪኩን ሲናገር አባቱ በልጅነቱ ሙዚቃ እንዲማር ሙዚቃ ትምህርት ቤት አስገባው። ልጁም ሙዚቃ ተማረ፤ ከዚያም የድምጽ አወጣጥ ትምህርት ወሰዶ በጣም ግሩም ሙዚቀኛ ሆነ። ከዚያም ኮሌጅ ደረጃ ሲደርስ ትምህርት ቤቱ ስለወደደው፤ ሌላ ዓይነት ትምህርት እንዲያስተምር አስተማሪ አድርጎ አሰለጠነው። ዲግሪውን ከተቀበለ በኋላ በየትኛው የሙያ ዘርፍ እንደሚቀጥል ለመምረጥ ተቸገረ። ወደ ሙዚቃው ያድላ ወይስ ከኮሌጅ የተመረቀበትን የሚወደውን ትምህርት በማስተማር ይቀጥል? ከዚያም አባቱን ሊያማክረው ወደ አባቱ ሄደና፤ "በየትኛው የሙያ መስክ እንደምሰማራ ለመምረጥ ጨንቆኛል። የትኛውን ልምረጥ?" ሲል አባቱን ጠየቀው። አባትም ልጁን "እነዚህ የተጨነቅክባቸው ምርጫዎችህ ምንና ምን ናቸው?" አለው። "ሙዚቀኛነት ወይም አስተማሪነት? ልጄ ሆይ! ምንጊዜም በሁለት ወንበር ላይ መቀመጥ ስትሞክር በመካከል ባለው ቀዳዳ ትወድቃለህ። በሁለት ወንበር መቀመጥ ስለማይቻል ህይወት እንደዚህ ነው። ራስክን ለአንዱ ስትሰጥ ይሳካልሃልና በመረጥከው በአንዱ ወንበር ላይ ተቀመጥ" አለው።

ቤተሰብም ሆነ ትዳር እንደዚሁ ነው። ሰዎች በትዳር ውስጥ ተቀምጠው ሃሳባቸው በሌላ ነገር ከተከፋፈለባቸው በሁለት እና በሦስት ወንበር ላይ ነው የሚቀመጡት። ከዚያም በአንዱ ወንበር ላይ በቅጡ መቀመጥ ይሳናቸውና ይወድቃሉ። በአንድ ወንበር ላይ መቀመጥ ቤተሰቡን በቅድሚያ ባል፣ ሚስት እና ልጆች መኖር

የሚችሉበትን ጥበብ ሲያገኙ፣ በአንድ ወንበር ላይ መቀመጥ ሲችሉ፣ መሰጠቱ ሲኖር ቤቱ እንደ ተያያዘ ይቆማል። ቀደም ባለው ክፍል ላይ እንደ ተነጋገርነው እነዚያ 43 ዓመት በትዳር የቆዩት ሌስና ቼሪ የተባሉ ባል እና ሚስት ትዝ ይሏችኋል? ከ16 ዓመት በኋላ የቀረውን ዓመታት በሙሉ ሰውዬው እስር ቤት ሆኖ ሳለ የባል እና ሚስት ግንኙነታቸው ግን አልተቋረጠም። ልጆቹም ቢሆኑ ዛሬም ድረስ ለአባታቸው ያላቸው መሰጠታቸው ስላልተቋረጠ እስር ቤት ድረስ እየሄዱ ይጠይቁታል። ከቃል ኪዳናቸው ጽኑነት የተነሳ አንዳቸው ለሌላው ያላቸው መሰጠት የማይናወጥ ሆኗል።

ጠንካራ ትዳር እና ቤተሰብ መሰጠትን ይጠይቃል። ለዚህ ነው የመጽሐፈ መክበብ ጸሐፊ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፉ ምዕራፍ 4፡12 ላይ "በሦስት የተገመደ ገመድም ቶሎ አይበጠስም" የሚለን። ለምንድነው የማይበጠሰው? ስንል አንደኛው ምክንያት አንዱ ገመድ ራሱን በመሰጠት ከሌላው ገመድ አጠላልፎ በመጣመሩ፤ ሁለተኛው ደግሞ የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ በሦስተኛው ላይ ራሳቸውን በመሰጠት ስላጠላለፉ ነው። በእነዚህ ገመዶች መካከል መሰጠት የሚባል ነገር ስላለ ይህ በሦስት የተገመደ ገመድ ቶሎ አይበጠስም። ጠንካራ ቤተሰብም እንደዚሁ ነው መሰጠት መኖር መቻል አለበት።

ሐ. መቀራረብ

ሦስተኛው ሃሳቤ መቀራረብ ነው። ቀደም ሲል ስለ ተግባቦት፣ መሰጠት ተነጋግረናል። አሁን ደግሞ ስለ መቀራረብ፣ መያያዝ ትንሽ መናገር እፈልጋለሁ።

ብዙውን ጊዜ ለልጆቻችን ስጦታ ገዝተን ለመስጠት ምን ብገዛለት ይሻላል ብለን እንጨነቃለን። ስጦታው ደግሞ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ነገር መሆን አለበት። አብዛኛውን ጊዜ ስጦታ ለመስጠት የሚዘጋጁ ሰዎች ነፍሳቸው እስክትወጣ ድረስ የሚጨነቁት ብዙ ነገር አንስተው የሚጥሉት ለዚህ አይደል?

አንድ አባት አንድ ጊዜ ለልጁ ለገና በዓል ስጦታ ምን ገዝቶ እንደሚሰጠው ሃሳብ ገባው። እናም ልጁን ጠራውና "ልጄ ለገና በዓል የሚሆን ስጦታ ምን ልግዛልህ?" ሲል ጠየቀው። ልጁም "አባዬ እኔ የምፈልገው አንተ ከእኔ ጋር አብረኸኝ የምትጫወት ከሆነ አሜሪካኖቹ እግር ኳስ የሚጫወቱበትን ኳስ ግዛልኝ። ከዚያም እኔ ስወረውርልህ አንተ ትቀልባለህ፤ እኔም ደግሞ በተራዬ አንተ ስትወረውርልኝ እቀልባለሁ። አንተ ልታጫውተኝ ካልቻልክ ግን ከጎረቤታችን ልጅ ጋር የምጫወትበትን የተለመደውን የእግር ኳስ ግዛልኝ" አለው።

ልጁ ይህን ሲለው አባት ከእንቅልፍ የተቀሰቀሰ ያህል ነበር የባነነው። ለካስ ልጁን የራበው ኳስ ጨዋታው ሳይሆን ከአባቱ ጋር ጎብረት ማድረግ፣ ፍቅር መለዋወጥ፣ አባት ጊዜ ሰጥቶት አብሮት እንዲሆን ነበር። እንወደዋለን ለምንለው ሰው የምንሰጠው እጅግ የከበረ ስጦታ ቢኖረን ጊዜያችንን ነው።

በቤተሰብ ውስጥ መያያዝን ከሚፈጥሩት ነገሮች መካከል መቀራረብ ዋነኛው ነው። "ልጅ እዋቂ ፊት ምን ያደርጋል? በሉ

ወደ ጓዳ ግቡ" ወይም ደግሞ "ከልጅ አትጫወት ይወጋሃል በእንጨት" እየተባልን ስላደግን ነገራችን ተበላሽቷል። አንድ ጊዜ ሰዎች ኢየሱስ ህጻናቱን እንዲባርካቸው ወደ እርሱ ባመጧቸው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ገሰጿቸው። ኢየሱስም ይህን የደቀ መዛሙርቱን ነገር አይቶ "ህጻናት ወደ እኔ ይምጡ አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና" አላቸው (ማርቆስ 10፡12)። ለምን? ስንል ምክንያቱም ጌታ ለመቀራረብ ዋጋ ስለሚሰጠው ነው።

መቀራረብ በወላጆች እና በልጆች መካከል ብቻ ሳይሆን በባል እና በሚስት በአጠቃላይ በቤተሰብ መካከል ለመያያዝ የሚያስፈልግ ቅመም ነው። መቀራረብ ያስፈልጋል። አብረው አንድ ቤት ውስጥ በደባልነት በሚኖሩ እና በባለ ትዳሮች መካከል ያለውን ልዩነት በጣም የሚያሰፋው አንዱ ያላቸው መያያዝ ነው። በደባልነት የሚኖሩ ሰዎች ቅርበታቸው በትዳር ተጣምረው አብረው ከሚኖሩ ሰዎች የተለየ ነው። በባለ ትዳሮች መካከል አንዳች ችግር ካለ ቶሎ ሳንካ የሚገጥመው መቀራረባቸው ሲሆን፤ በትዳር ሕይወታቸው ውስጥ ያለው የእርስ በርስ መያያዛቸውም አደጋ ይፈጠርበታል። መቀራረቡና መያያዙ እንኩን ከተፈጠረበት ደግሞ በመካከላቸው ክፍተት እየተከሰተ ይመጣል። መቀራረቡን ለመፍጠር ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። የእኔ ዘመዶች አገር ቤት ከተጋቡ በኋላ ባል የትዳር ጓደኛውን እንደ ዕቃ ገጠር አስቀምጠ እርሱ ግን ከተማ እየሰራ በዓመት አንድ ጊዜ ለመስቀል በዓል ልብስ ይዞላት ይሄዳል። ይሄ

ምን የሚሉት ትዳር ነው?

እንደምታውቁት በአገራችን ባል እና ሚስት የእኔ ቆንጆ፣ ውዴ፣ እንትናዬ እየተባባሉ መጠራራቱ ይቀርና አቶ እንትና ወይም ወይዘሮ እከሌ፣ ወይም ደግሞ በልጃቸው ስም የእንትና እናት፣ የእንትና አባት ተብሎ ከተጠራሩ እነዚህ ነገሮች ሲመጡ መቀራረቡ ችግር ገጥሞታል ማለት ነው። ቅድም እንዳልነው ግን እንደ ቤተሰብ ከተግባቦታችን፣ ከመሰጠታችን ሌላም በጣም ጥሩው ቅመም መቀራረቡን መጠበቅ ይመስለኛል።

ቪክቶር ላይ እና ጆርይ ፓዬፕ የተባሉ ሁለት ጸሐፊዎች ከጻፉት "ቤተሰብ ለቤተሰብ" (Family to Family) ከሚል መጽሐፍ ውስጥ ያገኘሁትን መጠነኛ መረጃ ልንገራችሁ። ከአሜሪካ ባለ ትዳሮች ውስጥ በቀን አንድ ጊዜ አብረው ምግብ የሚበሉት ሰላሳ አራት ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። በቀን አብሮ መብላት የሚችሉት ብዙ ቤተሰብ ካለ ብቻ ነው። ስድሳ ስድስት በመቶ የሚሆኑት ግን ጨርሶ ማዕድ ላይ የማይገናኙና ሁሉም በየራሳቸው የሚበሉ ናቸው። ከልጆቻቸው ጋር አብረው የሚያሳልፉት አባቶች በቀን ውስጥ በአማካይ ከስምንት እስከ አስር ደቂቃ ብቻ ነው። እርሱም ቢሆን ቴሌቪዥኑን ጨምሮ ነው። አብረው የሚጸልዩ የአሜሪካ ቤተሰቦች ቁጥር አስራ ሁለት በመቶ ብቻ ሲሆኑ፤ ሰማንያ ስምንት በመቶ የሚሆኑት በጸሎት ዙሪያ አይገናኙም ማለት ነው። አሜሪካ ውስጥ ባል እና ሚስት አብረው ለብቻቸው ሆነው የሚጫወቱበት እና ትርጉም ያለው ግንኙነት የሚያደርጉበት ጊዜ

በቀን ውስጥ አራት ደቂቃ ብቻ ነው የሚሆነው።

ይህንን ወደ ራሳችን ህይወት ትንሽ እንውሰደው። እውነት እንነጋገር! ምን ያህል ነው የምንቀራረበው? ፈረንጆች ይህን ችግራቸውን የሚፈቱበት ብዙ መንገድ አላቸው። አለሁልህ፣ አብሬህ ነኝ ለማለት ስልክ አላቸው፤ ወጣቶች አጭር የጽሁፍ መልዕክት ይላላካሉ። የካርድ እና የአበባ ስጦታ ይሰጣጣሉ። የሚወዱትን ነገር የሚያደርጉበትና የሚቀራረቡበት ብዙ ዓይነት መንገድ አላቸው። "እኔ እንጃ የት እንዳለ አላውቅም፤ የት እንዳለች አላውቅም" አይባባሉም። ታዲያ እኛስ ምንድነው በቤታችን ውስጥ እያደርግን ያለነው? ይህን መሰሉን መቀራረብ ለማምጣት ምን ያህል ነው ጊዜ የምንሰጠው? ምን ያህልስ ነው ጥረት የምናደርገው? በማዕድ ገበታችን፣ በጨዋታ፣ በጸሎት ሰዓት መገናኘት እንችላለን። አስቤዛ ለመግዛት አብረን ወደ ምግብ ሽቀጣ ሽቀጥ መደብሮች መሄድ እንችላለን። በቤተሰባችን ውስጥ ብዙ መገናኛ መንገዶችን ፈልገን መቀራረብ እንችላለን። መቀራረቡን ካለመጣነው ጠንካራ ቤተሰብ ለማምጣት ያለን ነገር በጣም ከባድ ነው የሚሆነው።

የትኛውም መሥሪያ ቤት ሄዳችሁ ብትመለከቱ ሠራተኞቻቸውን ስለ ተግባቦት፣ ለሥራቸው እና ለመሥሪያ ቤቱ ማደግ ስላላቸው መሰጠት ለማስተማር በየመሥሪያ ቤቱ ከፍተኛ ገንዘብ ነው የሚያፈሱት። በየሳምንቱ የሦስት፣ የአራት ቀን ሴሚናር እየተባለ ስለ ተግባቦት፣ መሰጠት፣ መያያዝ ያስተምሯቸዋል። ይህን የሚያደርጉትም ጉዳዩ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

እንግዲህ እኔ ለራሴም ሆነ ለእናንተ ያለኝ ጥያቄ ለዚህ ለውጪው ነገር እንዲህ የምንማር ከሆነ ጌታን በቤታችን ውስጥ ላለው ነገር አስተምረኝ ብለን እንዴት አንማርም? የምማርባቸውን መጽሐፎችንስ እንዴት አላነብም? ሊመክሩኝ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ተቀምጬ መግባባት የሚባለው ነገር እንዴት ነው ብዬ ለምን አልጠይቅም? የመያያዝ፣ የመቀራረብ ዘዴው እንዴት ነው? እናንተ እንዴት ነው የምታደርጉት? ብዬ እንዴት አልጠይቅም። መሰጠትን የምንፈትሽበት መንገዱ ምንድነው? አንድ ወንበር ላይ መቀመጥ አቅቶኛልና ምን ተመክረኛለህ እንዴት አንባባልም? እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ እንጀምር። ይህንን ካደረግን ለለውጥ ተነስተናል ማለት ነው።

በያዕቆብ 1፡5–8 ላይ *"ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል። ዳሩ ግን ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባህር ማዕበል ነው። ያ ሰው ከጌታ አንዳች ነገር አገኛለሁ ብሎ አያስብ፤ እርሱ በሁለት ሃሳብ የተያዘና በመንገዱ ሁሉ የሚወላውል ነው"* የሚል ቃል አለ።

የጥበብ እና የዕውቀት ምንጭ እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነ፤ እነዚህን ምሰሶዎች በህይወታችን እና በትዳር ግንኙነታችን ውስጥ መትከል እንድንችል፤ እግዚአብሔር ጥበብ፣ ዕውቀት እና ማስተዋል እንዲሰጠን እርሱን መጠየቅ እንችላለን። ስንጠይቅ ግን ሳንጠራጠር

እግዚአብሔር ሊሰጠኝ ይችላል፣ ይወዳልም ብለን እንቅረብ። ይህን እናደርግ ዘንድ እግዚአብሔር ይርዳን!

ምዕራፍ 6

ራዕይ ያለው ቤተሰብ

ምዕራፍ ስድስት

ራዕይ ያለው ቤተሰብ

ባለፉት ምዕራፎች አንድን ጠንካራ ቤተሰብ ሊያስገኙ የሚችሉ አበይት ጉዳዮችን ግራ እና ቀኝ እያልን ለማየት ሞክረናል። የእግዚአብሔርንም ቃል በመጥቀስ ምሳሌዎችን እየመዘዝን ከተለያየ አቅጣጫ ተመልክተናል። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከትነውም ቤተሰብ አውደ ውጊያ ነውና እንዲሁ በአንድ ጀንበር ጠንካራ ቤት አይሰራም። መንፈሳዊ ትንቅንቅ ያለበት በመሆኑ ያለ እግዚአብሔር እርዳታ እና ብርቱ ጸጋ ጥረት ሁሉ እንደማይሰምር እናውቃለን።

የምንናገረው እንደ ቤተሰብ መሪዎች፣ እንደ ወላጆች፣ እኛ ልንፈጽማቸው ስለሚገቡን ተግባራትና ስለምንወጣቸው ግዴታዎች ነው።

ቤተሰብን የመሠረተው እግዚአብሔር በመሆኑ፣ ቤተሰብ በእግዚአብሔር ሃሳብ ውስጥ የሚኖር፣ እርሱን የሚያመልክ፣ የእርሱንም ዓላማ በምድር ላይ እንደ አንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ የሚያስፈጽም ሊሆን ይገባል።

በምዕራፍ አምስት ላይ የቤተሰብን አንድነት ለመጠበቅ የሚያስችለንን ጥበብ መመልከት ጀምረን ተግባቦት፣ መሰጠት እና መቀራረብ ምን ያህል የቤተሰብን ጤንነት እና አንድነት እንደሚጠብቁ አይተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ራዕይ ያለው ቤተሰብ የሚለውን ነጥብ አብረን እንመልከት።

ሰዎች ወደ ቢሮዬ ይመጡ እና ማግባት እንደሚፈልጉ እና እንዳቀዱም ሲያማክሩኝ ሁልጊዜ ልፈትሸው የምፈልገው አንድ ነገርና እኔም ለእነርሱ እንዲሆንላቸው የምመኝላቸው "ምን የጠራ ራዕይ ኖሯቸው ወደ ጋብቻ መግባት ፈለጉ?" የሚለውን ነው። አሁን ይህን ጋብቻ ምን ታደርጉበታላችሁ? የማግባት ዓላማችሁስ ምንድነው? ጌታን መኪና ስጠኝ ብለን ብንለምነው በመኪናው ምን ልናደርግበት ፈልገን ነው የለመነው? ወደ ሥራ ቦታ እንመላለስበታለን፣ ልጆች ትምህርት ቤት እናደርስበታለን፣ እናመጣበታለንም። ልክ እንዲሁ እግዚአብሔርን ጋብቻ፣ ትዳር፣ ቤተሰብ መመሥረት የሚባለውንም ነገር ስጠኝ ብዬ ስጠይቀው ምን ልታደርግበት? ብሎ ቢለኝ የምሰጠው መልሴ ምንድነው?

ይሄ ቀላል ነገር ይመስላል፤ ግን አይደለም። ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ቶሎ ሊመልሱት የሚፈልጉት ልጅ ለመውለድ፣ ዘር ለመተካት ስለምፈልግ የሚለውን ነው። የብቸኝነት ኑሮ ስለ ከበደኝ ኑሮን ማቅለል እፈልጋለሁ ማለት ይቻላል። ሰው የወሲብ ስሜቱን ለማርካት ፈልጎም መጠየቅ ይችላል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉና ትክክለኛ ነገሮች ናቸው። እግዚአብሔር

አስቀድሞ ጋብቻን ሲመሠርት የሰጠን ነገሮች ናቸው። ይሁን እንጂ ጋብቻ ከዚህስ የሚበልጥ ጉዳይ የለውም ወይ?

ይህንን ጥያቄ ከመለስን ቤቱን በአለት ላይ ለመመሥረት እንዳሰበ ሰው እንሆናለን። ምክንያቱም ሰው ቤት ለመሰራት ብድግ ብሎ የመሰለውን እንጨት እየመዘዘ እና ያገኘውን ድንጋይ እየኮለኮለ ከሰራ ዝም ብሎ የካበው ስለሚሆን ቀኑን ጠብቆ ይናዳል። ነገር ግን ሰው ቆም ብሎ ቤቱን በምን እንደሚሰራው፣ ስንት እንደሚያስወጣው ሂሳቡን ቢያሰላው፣ ንድፉ ቢኖረው ግን ዘላቂ ቤት ሊሰራ ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ጸሎት ቤት የሚሆን ህንጻ መግዛት ፈልገው ካላገኙ የሚወስዱት አንዱ አማራጭ ለሌላ ዓላማ የተሰራን ህንጻ ገዝቶ የህንጻውን ቅርጽ ለውጦ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሆን አድርገው መጠቀም ነው። ከመጀመሪያው ለዚሁ ተብሎ ባይሰራም እንኳ ጥሩ ንድፍ ተሰርቶለት ይታደስና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል።

ትዳር የተፈለገበት ሌላ ራዕይ፣ ሌላ ዓላማ የለም ወይ? ቤተሰብ ለመመሥረት ርምጃ ሲጀመር ከዚህ የላቀ ግብ ሊኖር አይገባም ወይ? ዘር ለመተካት ተብሎም ከሆነ እኮ ልጅ ተወልዶም የቤተሰብ ችግር አንድ ቦታ ሊቆም የማይችልበት ምክንያት የለም። የኑሮን ቀንበር ለመጋራት፣ የትዳርን ሸክም ለማቅለል፣ ተብሎ ወደ ቤተሰብ ምሥረታ ተገብቶ እኮ ኑኡ. . .ኡ ወይኔ በምን ክፉ ቀን ነው ወደዚህ ትዳር ውስጥ የገባሁት? ማነው ከዚህ የሚያወጣኝ? የሚል እሮሮ እና ብሶት ሊከተል ይችላል።

እንግዲያውስ ትዳር ለመመሥረት የጋብቻ መንስዔ ከዚህ ለየት ያለ አንድ የከበረና የላቀ ግብ መኖር አለበት። እግዚአብሔር የባረከው ሰው ይህንን ትክክለኛ የጋብቻ ዓላማ እና ራዕይ አንግቦ ወደ ትዳር ይገባል። በዚያም ውስጥ ለዚያ ግብ ይኖራል። ለዚህ ነው ይህ ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት።

አንድ ሰው ትዳር ለመመሥረት ቢፈልግ በቅድሚያ ትዳሩን ለምን ጉዳይ እንደፈለገው ቢረዳ መንገዱ ቀናና ትክክል ይሆናል። ራዕይ ግብ ያስፈልገዋል። አለበለዚያ መጀመሪያ ለገበያ አዳራሽነት የተሰራን ህንጻ ገዝቶ ወደ ቤተ ክርስቲያን ህንጻነት ልለውጠው ሲባል ለብዙ አላስፈላጊ ወጪ እንደሚዳርገው ትዳሩም ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ይሆናል።

የቤተሰብ ህይወት ከመነሻው ንድፍ እንዲኖረን እግዚአብሔር ካልረዳን በስተቀር ልቦናችን ተከፍቶልን ይህን የከበረ ነገር እግዚአብሔር ለምን እንደሚሰጠን፣ በእጃችን ሲገባም ምን እንደምናደርግበት ካልገባን በስተቀር ቤቱ እየተገነባም ሳለ እንደመጣለት ቤት እንደሚሰራ ሰው ነው የምንሆነው። ለነገሩ ቤቱ መሰራቱን ይሰራል። ነገር ግን በጣም አታካችና አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። መለኪያም አይኖረውም። የሚንገሻገሽው፣ እግሮ እጓ የሚለው ነገር አበዛዙ የትዬለሌ ነው። እየሮጡ ሱሪ የመታጠቅ ያህል ክፉ ፈተና ነው የሚሆነው። ከምስጋና ይልቅ እሮሮ፣ ከሃሌሉያ ይልቅ ኤሎሄ ይሰማበታል።

ሀ. እግዚአብሔር የራዕይ አምላክ ነው

ታሪካቸው በጌታ ቃል ውስጥ የተጠቀሱ ቤተሰቦችን፣ እግዚአብሔር የጠራቸውን፣ ህይወቱን የገለጠባቸውን ሰዎች በሙሉ ብትመለከቱ ሁሉንም ከራዕይ እና ከዓላማ ጋር አያይዞ ነው የጠራቸው። እግዚአብሔር አዳምን ወስዶ ወንድና ሴት አድርጎ ሰርቶ ያስቀመጠው በኤደን ገነት ነው። ዘፍጥረት ምዕራፍ 2:15 ላይ *"እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወስዶ እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት በኤደን የአትክልት ስፍራ አስቀመጠው"* ይላል፤ በኋላ ላይ ኃጢአት ገብቶ አመሰቃቀለው እንጂ። እግዚአብሔር ለአዳም ቤተሰብን፣ ቤትን፣ ኑሮን እና ሊሠራው የሚገባውንም ሥራ ጭምር ነበር የሰጠው። አዳም እንኳን ኤደን ገነት የተቀመጠው በእግዚአብሔር አጀንዳ ነበር።

ኖኅ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር እንደ ማናችንም ነበር የኖረው። የሰው አመጽ በምድር ላይ ሲበዛና የልቡም ሃሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ሲያዘነብል እግዚአብሔር ለኖኅ በልቡ ራዕይን ሰጠው። ኖኅም ለዚህ ራዕይ በጽድቅ ለመኖር መረጠ። ያንጊዜ ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አገኘ። እንዲህም አለው *"ኖኅ ሰውን ሁሉ ላጠፋ ነው፤ ምድር በሰው አመጽ ስለተሞላች በእርግጥ ሰውንም ምድርንም አጠፋለሁ። አንተ ግን በጎፈር እንጨት መርከብ ሥራ፤ ለመርከቧም ክፍሎች አብጅላት፤ ውሰጧንም ውጭዋን በቅጥራን ለብጠው"* (ዘፍጥረት 6:13-16) በማለት እርሱና ቤተሰቡ የሚሰፉትን ሥራ ሰጠው። እነዚህ ጥቂት ነፍሳትም በዚያን ዘመን በተሰጣቸው ዓላማ እና ራዕይ ያንን

የሚያክል መርከብ እየሰሩ ኖሩ።

ህዝቡ የተሰራውን መርከብ ባያደንቀውም ለኖኅ እና ለቤተሰቡ ግን ከጥፋት ማምለጫ፣ ከፍርድም መትረፊያ ሆኖላቸዋል።

የእግዚአብሔርን ሰዎች በሙሉ ተመልከቷቸው። ሁሉም በእግዚአብሔር ቃል ስለሚኖሩ በኑሯቸው የእግዚአብሔር አጀንዳ፣ ራዕይ ነበራቸው። አብርሃም በጣዖት አምላኪ ቤተሰቦቹ መካከል ሲኖር ሳለ እግዚአብሔር *"አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ። ታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ፣ ደግሞም እባርክሃለሁ፣ ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፣ ለሌሎች በረከት ትሆናለህ። የሚባርኩህን እባርካለሁ፣ የሚረግሙህን እረግማለሁ፣ በምድር የሚኖሩ ህዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ"* በማለት ለዓላማው ጠራው (ዘፍጥረት 12፡1-3)። ከዚያች ቀን ጀምሮም እግዚአብሔር ወዳለው ምድር እስከሚደርስ ድረስ የአብርሃም ኑሮ ድንኳኑን እየተከለ እና እየነቀለ መጓዝ ሆነ። ደጋግሜ መናገር የምፈልገው ሃሳብ ይህ ነው። እግዚአብሔር ቤትን፣ ትዳርን፣ ከሰው ጋር አብሮ መኖርን፣ በቃል ኪዳን መጣመርን፣ ልጆችን ማፍራት የሚያክል ነገር ሲሰጠን ለአጀንዳው፣ ለራዕዩ፣ ለዓላማው ነው። ለጠንካራ ቤተሰብ ግንባታ ከመነሻው ጥሩ ንድፍ ወይም ራዕይ ያስፈልጋል።

ይስሃቅም አባቱ አብርሃም ካረፈ በኋላ ብዙ ሃብት ወረሰ፤ በዘመኑ ጦርነት አልነበረበትም፤ የሰላምን ኑሮ ነበር የኖረው። ይስሃቅ በአባቱ ሃብትና በረከት ተዝናንቶ መኖር ሲጀምር እግዚአብሔር

እንደ አባትህ ሁሉ ከአንተም ጋር ጉዳይ አለኝና ንቃ አለው። እግዚአብሔር ይስሃቅን ለማንቃት በምድር ላይ ርሃብን ጠራ። ርሃቡ ሲመጣም ይስሃቅ ወደ ግብጽ እወርዳለሁ ብሎ ተነሳ። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር ተገለጠለትና *"እኔ በምነግርህ ምድር ተቀመጥ እንጂ ወደ ግብጽ አትውረድ፤ ለጥቂት ጊዜ እዚሁ አገር ተቀመጥ፤ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፣ እባርክሃለሁም"* አለው *(ዘፍጥረት 26፡2-3)*።

ሰው እግዚአብሔርን ይሰማ ዘንድ አንዳንድ ጊዜ ችግሮች፣ ድርቆች ወደ ህይወቱ መምጣት አለባቸው። እግዚአብሔር ልክ ለአባቱ ለአብርሃም የነገረውን የተስፋ ቃል እንዳለ ቃል በቃል ደገመለት። ለይስሃቅም በኑሮህ፣ በትዳርህ፣ በቤትህ ጉዳይ ነገር አለኝ ብሎ አጀንዳውን ገለጠለት። ይስሃቅም ከእግዚአብሔር ራዕይ ተቀብያለሁ ብሎ መኖር ጀመረ። ራዕይ ያለው ሰው መቼም አርፎ የሚቀመጥ አይደለምና ዝም ብዬ ከምቀመጥ ጥንት አባቶቼ የቆፈሩትንና በጓላ ላይ ፍልስጤማውያን የደፈኗቸውን ጉድጓዶች ለምን አልከፍትም አለ። ሰው ራዕይ ሲኖረው የተዘጋውን ለምን አልከፍትም ነው የሚለው። እናም የተደፈኑትን ጉድጓዶች ሄዶ ሲከፍት የከተማዋ ሰዎች የእኛ ነው ብለው ተጣሉት። ይሁንላችሁ ብሎ ለቀቀላቸውና ወደ ሁለተኛ ጉድጓድ በመሄድ እንደገና ቢከፍት፤ አሁንም እንደ በፊቱ ይህም የእኛ ነው ብለው ተጨቃጨቁት። በመቀጠልም ወደ ሌላው ጉድጓድ ሄደ። እንዲህ፣ እንዲህ እያለ ከርከር ወደሌለበት ቤርሳቤህ እስኪደርስ ድረስ እግዚአብሔር ከአንድ ጉድጓድ በረከት ወደ ሌላው እያዞረ ባረከው። ለምን? ስንል

እግዚአብሔር ይስሃቅ ራዕይ ያለው ሰው ሆኖ ስላገኘው ለጉዳዩ፣ ለዓላማው፣ ማለት ነው። ወገኖቼ! እግዚአብሔር በራዕይ፣ በዓላማ ይባርካችሁ!

ምናልባት ብሉይ ኪዳን ውስጥ ባሉት ምሳሌዎች ብቻ እንዳልይዛችሁ ከአዲስ ኪዳን ደግሞ የዮሴፍ እና የኢየሱስን እናት የማርያምን ታሪክ ምሳሌ ማንሳት እወዳለሁ።

የጌታችን እናት ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ በነበረችበት ወቅት ላይ በድንግልናዋ ወራት ድንገት በህይወቷ የእግዚአብሔር ነገር ጣልቃ ገባና በመጀመሪያ መልዓኩ ማርያምን "ትጸንሻለሽ" አላት። እርሷም መልሳ "እኔ ወንድ አላውቅም እንዴት ይሆናል?" አለችው። መልዓኩ መልሶ "የእግዚአብሔር መንፈስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ ይጸልልሻል፤ ታረግዣለሽ ከአንቺ የሚወለደውም የልዑል የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" አላት። እርሷም "እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" ብላ ነገሩን ተቀብላ ዘጋችው።

እግዚአብሔር ይህንን ጸጋ ለእኛም ይስጠን። እግዚአብሔርን የምንከተለው ሁሉን ነገር አብራርተን አውቀን ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው። እናም የኢየሱስ እናት ማርያም ገና ያልተመለሰ ጥያቄዋ እያለ፤ ለዮሴፍ ምን ብላ እንደምትነግረው ባታውቅም ይህንን ራዕይ የህይወቷ ትልቅ ጉዳይ አድርጋ ተቀበለችው። ዮሴፍም ነገሩ በደረሰው ጊዜ የተባለው ነገር በእርሱ የትዳር ዕቅድ ውስጥ የሌለ ነገር ነው። እርሱ እንደ ማንኛውም ሰው ትዳር ይዞ፣ ቤት ሰርቶ፣ ልጆች የመውለድ ዕቅድ ነው የነበረው። ይሁን እንጂ ማርያምን በስውር

ሊተዋት አሰበ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ግን የልቡን ሃሳብ አውቆ በመልዓኩ በኩል እንዲህ አለው። *"የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! ከእርሷ የተጸነሰው በመንፈስ ቅዱስ ነውና፤ እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅን ትወልዳለች፤ እርሱ ህዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ" (ማቴዎስ 1:20-21)*። ከዚያ በኋላ የማርያምና ዮሴፍ ህይወት ይህንን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይ ይህንን ህጻን እግዚአብሔር ለፈለገው ዓላማ ብቁ እስከሚሆን ድረስ መንከባከብ ጀመሩ። ይሄ ቀላል ነገር እንዳይመስላችሁ። ይህ ራዕይ ወደ እርሷ ከመጣና ህጻኑም ተወልዶ አድጎ ወደ ቤተ መቅደስ በወሰደችው ጊዜ *"እነሆ የብዙዎች ልብ ሳጣብ ይገለጥ ዘንድ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎች ለመውደቃቸውና ለመነሳታቸው፤ ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሟል፤ በእንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል" (ሉቃስ 2:33)* አላት። ምን ዓይነት ራዕይ ነው!

አንዳንድ ጊዜ ራዕይ ብለን የምንለው ነገር ዋጋ የማያስከፍል ይመስለናል። "ጌታ ሆይ ተናገረኝ! አንተ ብቻ የምትለውን በለኝ እንጂ፤ በእኔ በኩል ምንም ችግር የለም፤ ያልከኝን አደርጋለሁ" እንላለን። እርሱ ካለን ሁሉ ነገር ትክክል ሆኖ እንደሚሄድ አድርገን እናስባለን። ነገር ግን እንደዚያ አይደለም። እግዚአብሔር በህይወታችን ሊሰራው የሚወደው አንዳንዱ ነገር ዋጋው ውድ ነው። ትልቅን መስዋዕትነትም ነው የሚያስከፍለው። ዮሴፍ እና ማርያም በፍጻሜያቸው በእግዚአብሔር ተባርከው፣ ብእርሱም ዘንድ ሞገስን

አግኝተዋል። የተሰጣቸውን ራዕይ በመከተል ተባርከው ለበረከት ሆነው አለፉ እንጂ አልከሰሩም።

ታሪካቸውን የዘረዘርኩላችሁ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥበቃ አግኝተዋል። ራዕያቸውን ይዘው በጽናት በመቆማቸውም የእግዚአብሔርን ቸርነት ቀምሰዋል። እንደ ቤተሰብ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ራዕይ ጋር ስለ ጸኑ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ከእጃቸው ለማስጣል ሰይጣን ስንት ጊዜ ነው ለነገር የቆሰቆሳቸው። ሰይጣን የአብርሃምን ቤት ለመፍታት ያላመጣው ነገር አልነበረም። እግዚአብሔር ግን አብርሃምን ጠበቀው። ቢያረጅም፣ ርሃብ ከአገር አሳድዶ ቢያወጣውም ልጁንና የልጅ ልጆቹን ፍጻሜ አይቶ እንዲሄድ አደረገው።

አንዳንድ እየተቀጣጠሉ የሚሰሩ ቤቶች አይታችኋል? ባለቤቶቹ አንድ ክፍል ይሰራሉ፣ ከወራት ወይም ከዓመታት በኋላ ደግሞ አንድ ሃሳብ ብልጭ ሲልላቸው ሌላ ክፍል ይቀጥሉበታል። እንዲህ፣ እንዲህ እያሉ ከፊት፣ ከኋላ፣ ከግራ እና ከቀኝም ክፍሎችን እየጨመሩ ይሰራሉ። ባገኙት ክፍት ቦታ ሁሉ እንዱን ለማከራየት፣ ሌላውን ለዕቃ ማከማቻ፣ ያኛውን ደግሞ ለልጆች መኝታ ቤት እያሉ ገንዘብ ባገኙ ቁጥር እንግዳ በሆነ ዕቅድ ተቀጣጥለው የተሰሩ ቤቶች በአንድ ወጥ ራዕይ የተሰሩ ቤቶች ባለመሆናቸውና ተያያዥነት ስለሌላቸው ሁልጊዜ የመለያየት፣ የመከፋፈልና የመውደቅ አደጋ የተጋረጠባቸው ናቸው። ከዚያም በላይ ደግሞ የመጠጥ ውሃ፣ የፍሳሽ ቱቦ እና የኤሌክትሪክ መስመሮችን ለመዘርጋት ምቹ አይደሉም።

አንድ ወጥ የሆነ ራዕይ ሳይኖረን የምንጀምረው ጉዞም እንዲህ ያለ ችግር ነው የሚገጥመው።

እግዚአብሔር ስንት ጊዜ ነው ማርያምን እና ዮሴፍን ያዳናቸው። ህጻኑን ሊነጥቃቸው ከተነሳ፣ ነፍሳቸውን ከሚፈልጉ የአመጸኞች ቁጣ ስንት ጊዜ ነው ያስጣላቸው። እነዚህ ቤተሰቦች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይ ይዘው ጸንተዋልና የእርሱን ጥበቃ አግኝተዋል፣ ቸርነቱን ቀምሰዋል፣ በጎነቱንም አብዝቶላቸዋል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 29፡18 *"ራዕይ በሌለበት ህዝብ መረን ይሆናል፤ ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው"* (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) እንደሚል፤ እግዚአብሔር እናንተንም በራዕይ ይባርካችሁ!

ለ. ራዕይ ምንድነው?

ራዕይ የሚለውን ቃል አቅጣጫ፣ ምሪት፣ ግብ ብላችሁ ልትተረጉሙት ትችላላችሁ፤ መሪ ሃሳቡ የመንገድ አቅጣጫ ጠቋሚ የሚለውን ሃሳብ የሚያመለክት ነው። ካርታ ከየት እንደተነሳችሁ፣ ወዴት እንደምትሂዱ እና መድረሻችሁም የት እንደሆነ ያሳያችኋል። ራዕይ ከሌለ ህዝብ መረን ነው የሚሆነው። መረን ማለት ዝም ብሎ መበተን ወይም ልቅ መሆን ብቻ ሳይሆን መጥፋት የሚል ፍቺም አለው። ራዕይ ከሌለ ህዝብ ይጠፋል።

ይህንን ሃሳብ የሚያጸና ቃል በ1ኛ ቆሮንቶስ 9፡26 ላይ ታነኛላችሁ። ጳውሎስ ስለ ራሱ አገልግሎት ሲናገር *"ስለዚህ እኔ ግብ*

እንደ ሌለው ሰው በክንቱ አልሮጥም፣ ደግሞም ንፋሰን እንደሚነሰም ሰው እንዲያው አልታገልም" (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) እንዳለው ሰው ቀኑን ሙሉ ከነፋስ ጋር ቡጢ ቢገጥም ምን የሚያተርፍ ይመስላችኋልን? ምንም የሚያተርፈው ነገር እኮ የለውም። በቃ ልክ እንደዚሁ ጳውሎስም ራዕይ፣ ዓላማ፣ ግብ የሌለው ሰው የሚሮጠው ሩጫ፣ የሚኖረው ኑሮ እንዲህ ከነፋስ ጋር ቡጢ እንደ መግጠም ነው ይላል።

እዚህ ላይ እየተናገርኩ ያለሁት ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ አገር ራዕይ ሳይሆን፣ ቤተሰብ ራዕይ ነውና፤ እንደ ቤተሰብ ይህን እግዚአብሔር የሰጠንን ቤትና ቤተሰብ የምንመራው በምን ዓይነት ራዕይ ነው? በቀን ውሏችን አጋጣሚዎች ነው? ወይንስ ከእግዚአብሔር በተቀበልነው ራዕይ?

ራዕይ ያለው ቤተሰብ እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበት አያባክንም። ልክ በወታደር እጅ እንዳለ ፍላጻ ነው። ፍላጻውን በቀስቱ ደጋን ለጥጦ ሲለቀው ሂዶ የሚወጋው ዒላማ አለው። ልክ እንደዚሁ ኑሯችንም ዓላማ፣ ግብ ሲኖረው ግቡን እንደሚመታው ፍላጻ ነው የሚሆነው። ታዲያ ይሄ የእኛን፣ የልጆቻችንን ህይወት እና እግዚአብሔር የሰጠንን አደራም ይመለከታል። ራዕይ ያለው፣ ዓርማውን ይዞ እንደሚከተል ወታደር ያደርጋል። ወታደሮች ወደ ጦር ሜዳ ሲሄዱ ዓርማቸውን ይዘው ነው እንደሚሄዱት ልክ እንደዚያ ዓርማውን እንደሚከተል ወታደር ያደርገናል።

ሐ. ራዕይ እንዴት ይገኛል?

በመቀጠል ለቤተሰብ የሚሆን ራዕይ እንዴት እንደሚገኝ እንመልከት። ራዕይ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ ላይና ያለ ራዕይ መሆን ጉዳት፣ መጥፋት ብቻ እንደሆነ ከተስማማን፤ አሁን ደግሞ ራዕይ እንዴት እንደሚገኝ፣ የምናገኝበትን መንገድ ማየቱ አስፈላጊ ነው። በቅድሚያ በግልም ሆነ በቤተሰባዊ ህይወታችን ውስጥ ሊኖር የሚችል መሠረታዊ ነገር የራዕዮች ሁሉ የበላይ ራዕይ "የዚህ ቤተሰብ የመኖር ትርጉሙ እግዚአብሔርን ለማክበር ነው" የሚለው ነው።

በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 24፡15 ላይ *"እናንተ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፣ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመለካለን"* የሚለው ቃል የሁሉም ነገር መሠረት ነው። ሌላው ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣ ነው። የሁሉም ነገር መሠረት የሆነው ራዕይ የሚጀምረው ግን እግዚአብሔርን ለማክበር ነው።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ የተጠቀሱ የመጥምቁ ዮሐንስ እናትና አባት ዘካርያስ እና ኤልሳቤጥ የተባሉ ባል እና ሚስት ነበሩ። ካህኑ ዘካርያስ አንድ ቀን ምድብ ተራው ደርሶ ለአገልግሎት ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ እያገለገለ ሳለ የጌታ መልዓክ ተገለጠና "ዘካርያስ ሆይ አትፍራ ጸሎትህ ተሰምቷል" ሲል አንድ የእግዚአብሔርን ምስጢር ነገረው። ወገኖች ሆይ! ራዕዩ ወደ እነርሱ ይመጣ ዘንድ ዘካርያስ እና ሚስቱ ኤልሳቤጥ ግን እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ያደረጉት መሠረታዊ ነገር አለ። ራዕዩ እንዲሁ ዝም ብሎ እንደ ሎተሪ የመጣ አይደለም። ይህ ያደረጉት መሠረታዊ ነገር

ምንድነው? ስንል ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 1፡6-7 ላይ እንደምናነበው "*ሁለቱም በጌታ ትዕዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። ኤልሳቤጥ መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው ነበር*" ይላል።

እነኚህ ባልና ሚስት ልጅ ወለድንም አልወለድንም፣ የጸለይነው ጸሎት ተመለሰም፣ አልተመለሰምም የህይወታችን መመሪያ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ እግዚአብሔርን ማክበር፣ ለእግዚአብሔር ሃሳብ መገዛት ነው ብለው ለጽድቅ የወሰኑ ሰዎች ነበሩ። እኛ ለእግዚአብሔር ነገር እየተጠነቀቅን ስንኖር ከእግዚአብሔር የሆነው ራዕይ ወደ እኛ ይመጣል። የእግዚአብሔር እጅንዳ ወደ እነዚህ ሰዎች የመጣው በዚህ የህይወት መርህ መሠረት ነውና ራዕይን ለመቀበል የመጀመሪያው ውሳኔያችን መሆን ያለበት በጽድቅ መኖር ነው። እኔም ሆንኩ ቤተሰቤ የምንኖረው እግዚአብሔርን ለማምለክ፣ ለማክበር ነው የሚል ቀዳሚና ቁርጠኛ ውሳኔ መወሰንና ውሳኔያችንንም በተግባር ማሳየት አለብን።

እግዚአብሔር የሚወደው እና የሚፈልገው ይህንን የጽድቅ ፍሬ ነው። ትንቢት ቢሆን መገለጥ፣ ራዕይ ቢሆን ወይም ሌሎች ተዓምራትን ማድረግ እግዚአብሔር የሰጠን ማናቸውም ዓይነት አገልግሎቶች እና ሩጫዎች በሙሉ የሚሰሩት በጽድቅ ስንኖር ነውና በቅድሚያ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማክበር ቁርጠኛ ውሳኔ ልንወስን ያስፈልገናል።

ሰው ራዕይን የሚቀበልበት ሁለተኛው መንገድ ከእግዚአብሔር ከአምላኩ ጋር በጥሞና በቃል ጥናትና በጸሎት ሲጠመድ ነው። የብርሃን አምላክ ምስጢሩን የሚገልጥልን፣ አንተን እና ቤትህን ለዚህ ጉዳይ እፈልጋችኋለሁ ብሎ የሚናገረን በጸሎት ቦታ ላይ ነው። ወደ አዕምሯችን የመጣውን ሃሳብ እና ስሜት የምንመዝንበት መመዘኛ የሚገኝበት ስፍራ የእግዚአብሔርን ቃል የምናጠናበትና የጸሎት ቦታ ነው። ለዚህ እነሆኝ አንድ ምሳሌ!

በመጽሐፈ መሳፍንት 13፡2 ላይ ማኑሄ የሚባል አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር ይኖር ነበር። ሁለቱ ልጅ አልነበራቸውም። እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ጨቋኝ ሰምቶ መሳፍንት አስነስቶ ሊቤዣቸው በወደደ ጊዜ በወቅቱ ለዚህ ተልዕኮ የሚመጥን ሰው ስላልነበረ፤ ገና ወደፊት ከምትወልዱት ልጅ ጋር ጉዳይ አለኝ ብሎ ነገራቸው። ብዙጊዜ እግዚአብሔር ከሰማይ ራዕይን የሚልከው በውጭ በኩል ያለው ነገር ሁሉ ዝግትግት ብሎ ሲጨልም ነው። እግዚአብሔር ጉዳይ ካለው ጽንሱ ገና ባይጸነስም ጉዳዩን ይዞ ይመጣል። እናም ወደ እናቲቱ መጣና "*እነሆ አንቺ መካን ነሽ፣ ልጅም አልወለድሽም፣ ነገር ግን ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። አሁንም ተጠንቀቂ! የወይን ጠጅን፣ የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፤ . . . ልጁም ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና፤ በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፤ እርሱም እስራኤልንም ከፍልስጤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል*" (መሳፍንት 13፡3-5) አላት።

ብዙ ጊዜ እህቶች በጸሎት መሰዊያዎቻቸው ላይ ሲገኙ ባሎች ግን አንገኝም። ይህቺ ሴት በዚህ ሰዓት ባሏ አጠገቧ አልነበረም። እናም የቤቱ መሪ እና ራስ ባሏ በመሆኑ ይህን ባሌ ማወቅ አለበት ብላ በማሰብ ወደ ባሏ ሄዳ እንዲህ ስትል ነገረችው።

"የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፣ የእግዚአብሔር መልዓክ የሚመስልና እጅግ የሚያስደንግጥ ነበር። ከየት እንደመጣ አልጠየቅሁትም፣ እርሱም ሰሙን አልነገረኝም፣ ነገር ግን መጥቶ "እነሆ አንቺ መካን ነሽ፣ ልጅም አልወለድሽም፣ ነገር ግን ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። አሁንም ተጠንቀቂ! የወይን ጠጅን፣ የሚያሰክርም ነገር አትጠጪ፣ . . . ልጁም ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናልና፣ በራሱ ላይ ምላጭ አይድረስበት፣ እርሱም እስራኤልን ከፍልስጤማውያን እጅ ማዳን ይጀምራል" አለኝ ብላ አለችው።

ከዚያም ማኑሄ "መቼም ጌታ ሆይ! ይሄ የአንተ ሥራ፣ የአንተ ስጠታ፣ ነውና የሚወለደውን ልጅ እንዴት አድርገን ማሳደግ እንዳለብን እንዲያስተምረን ያ ወደ እኛ የላከው የእግዚአብሔር ሰው እንደገና እንዲመጣ ታደርግ ዘንድ እለምንሃለሁ" ብሎ ስለ ራዕዩ ዝርዝር ወደ እግዚብሔር ጸለየ።

"እግዚአብሔርም የማኑሄን ጸሎት ሰማ፣ የእግዚአብሔርም መልዓክ ሴቲቷ በእርሻ ሳለች ተገለጠላት፣ በዚህ ጊዜ ግን ባሏ ማኑሄ አብሯት አልነበረም። እርሷም ለባሏ ለመንገር ፈጥና በመሄድ፣

ባለፈው ጊዜ የተገለጠልኝ ሰው ዛሬም ተገለጠልኝ አለችው (መሳፍንት 16:6-10)።

"ማኑሄም ተነስቶ ሚስቱን ተከተላት፣ ሰውዬው እንደ ደረሰም፣ ከሚስቴ ጋር ተነጋግረህ የነበርኸው አንተ ነህ? ሲል ጠየቀው። እርሱም አዎን እኔ ነኝ አለው። ማኑሄም ያልኸው በሚፈጸምበት ጊዜ የልጁ ሕይወት የሚመራው እንዴት ነው? እኛስ ምን ማድረግ አለብን? ሲል ጠየቀው። የእግዚአብሔርም መልዓክ እንዲህ አለው፣ ሚስትህ የነገርኳትን ሁሉ ታድርግ፣ ከወይን ተክል የሚገኝ ማንኛውንም ነገር አትብላ፣ የወይን ጠጅም ሆነ ሌላ የሚያሰክር መጠጥ አትጠጣ፣ ርኩስ ነገር አትብላ፣ ያዘዝኋትንም ነገር ታድርግ አለው"።

ባለ ትዳሮች የሆንን ያለን ቀሪው የትዳር ዘመናችን ሥርዓት እንዴት ቢሆን ነው አንተ የምትወደው? ምናልባት ገና ለማግባት የምታስቡ ካላችሁም "አንተ የተናገርከኝ ቃል ፍጻሜን ባገኝ፣ ወደ ህይወቴ የላከው ሰው ወይም የላካት ልጅ ስትመጣ ከዚያ በኋላ ያለው የኑሮዬ ስርዓት ምንድነው?" ብለን እግዚአብሔርን መጠየቁ መልካምና ተገቢም ነው።

ወገኖቼ ሆይ! በጸሎት ቦታችን ስንሆን እግዚአብሔር የሚሰጠን፣ የሚናገረን ነገር አለውና እግዚአብሔር ሆይ! ቤተሰብ ስለሚባለው ስለዚህ ትልቅ ተቋም ያለህ ዝርዝር መመሪያ ምንድነው? ብለን ለመጠየቅ ወደ ጸሎት መሰዊያችን እና ወደ እግዚአብሔር ቃል

ጥናት ቦታችን መመለስ አለብን። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ጌታ ሆይ! እባክህን እንደ ባል እና ሚስት ለኑሯችን የሚሆን ራዕይን ስጠን ማለቱ መልካም እንደሆነ ነው የማስበው።

ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ባለ አጀንዳው እኔ ነኝ፣ ባለ ጉዳዩና ማለዳ ተነስቼ የዛሬው ጉዳዬ ይሄ ነው አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት ብዬ በጸሎት ለእግዚአብሔር የምነግረው እኔ ነኝ። ይሁንና እግዚአብሔር የሚፈልገው ግን እኔ እና ባለቤቴ ሁለታችንም አብረን አንድ ላይ ወደ እርሱ ተያይዘን በመቅረብ ለህይወታችን፣ ለኑሯችን፣ ለልጆቻችን፣ ወዘተ. ያለህ አጀንዳ ምንድነው? ብለን እግሩ ስር በርከክ ብለን እንድንጠይቀውና ከእርሱ እንድንሰማ ሃሳቡን እንድንቀበለው ነው። ልንሰንቀው የሚገባን የእግዚአብሔርን ራዕይ ነው።

እንደ ቤተሰብ ባልና ሚስት ሁነን አሁን ስለምንሄድበት የሥራ፣ የአገልግሎት መንገድ አንተ የምትለን ነገር ምንድነው? ብለን በጸሎት ቦታችን ሆነን ነው ራዕይን የምንቀበለው። መወያየቱ ጥሩ ነው፤ ቀደም ባለው ምዕራፍ ላይ ስለ ተግባቦት ብዙ ተነጋግረናል። ይሁንና ሁሉም ነገር ግን በውይይት አይወለድም። ሁሉ ነገር በእኔ እና በባለቤቴ አዕምሮ አይወለድም። እግዚአብሔር ብቻ የሚገልጣቸው ነገሮች አሉ። ጨለማውን አይቶ የሚናገር እግዚአብሔር ነው። የነገን፣ የከነገ ወዲያን የልጆችን፣ የልጅ ልጆችን ነገ አይቶ የሚናገር እግዚአብሔር ብቻ ነውና፤ ሰው ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለበት። እኛ ሁልጊዜ ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ነው የምንሮጠው። ሆኖም ሁሉ ነገር ግን ከጠረጴዛ ዙሪያ

ውይይት አይገኝም። አሁን ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ እና ልብ መመለስ ነው የሚያስፈልገን።

ራዕይ የሚገኝበት ሌላው ሦስተኛው መንገድ ችግራችን ራሱ ነው። ችግር እንዲደርስበት የሚፈልግ ማንም ሰው የለም፣ ችግር አይወደድምም። ነገር ግን መከራ ሲመጣ፣ ተራራው ከፊታችን ሲቆም፣ የችግር ወንዝ ሞልቶ ሲፈስ፣ የልቅሶ እና የእንባ ማዕበል ሲያጥለቀልቀን ብቻ ቀኑ እንደ አከንባሎ በላያችን ላይ የተደፋብን ሲመስለን በዚያን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ብንጮህ ቃሉ *"ይህ ችግረኛ ጮኸ፣ እግዚአብሔርም ሰማው፣ ከመከራውም ሁሉ አዳነው" (መዝሙር 34:6)* እንደሚል ከዚያ መከራ ማዳን ብቻም ሳይሆን ራዕይንም ይሰጠናል። ራዕይ በምጥ ውስጥ ይወለዳል። ራዕይ ከድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንደ አጥቢያ ኮከብ ተግ ብሎ ይወጣል።

ጉልበት በተንበረከከ፣ ልብ በራደ፣ ተስፋ ሁሉ ክሽክሽ እንደ በላው ቲማቲም በወደመ ጊዜ ወደ እርሱ ከጮኽን እግዚአብሔር ራዕይ የሚሰጥበትና ሕይወታችንን ዳግም እንደ ንጋት ወግታ በብርሃን የሚያጥለቀልቅበት ሁኔታ ይፈጠራል።

አንድ ዘመን ላይ በእስራኤል ምድር የእግዚአብሔር ቃል እልም ብሎ ጠፋ። ህልም አየሁኝ፣ ራዕይ ተገለጠልኝ፣ የሚል ሰው አልነበረም። ሁሉ ነገር ዝግትግት ያለበት ወቅት ነበር። ሰማይ ብቻ አይደለም ሁሉ ነገር እግዚአብሔር ከዘጋው ይዘጋል። እገራቱን መንፈሳዊ ድርቅ ክፉኛ መትቷት ስለነበር፤ ሰው ሁሉ በፊቱ

የመሰለውን ያደርግ ነበር። በዚህ ሁሉ ውስጥ የልጅ ያለህ እያለች የምትመረር አንዲት ሐና የምትባል መካን ሴት ነበረች። ሐና ልጅ መውለድና ማቀፍ በመፈለግ በእግዚአብሔር ፊት ብዙ ዓመት አለቀሰች። መጽሐፈ ምሳሌ ልጅ መውለድ ስለምትፈልግና ኃይለኛ መሻት ስላላት ማህጸን እንደሚናገረው ማለት ነው። ታዲያ ይህቺ ሴት ሐና ልጅ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት የመረረ ልቅሶ ስታለቅስ በሰማይም እግዚአብሔር ደግሞ ምድሪቱን የሚያሳርፍ ሰው ይፈልግ ነበርና የተናገረው ቃል ሳይፈጸም በምድር ላይ ጠብ የማይልን ነቢይ ለእስራኤል ለመስጠት ፈለገ።

ሐና ይህ ችግሯ ወደ እግዚአብሔር ወስዶ አናገራት። ልጅ ብትሰጠኝ አንተኑ እንዲያገለግል መልሼ እሰጥሃለሁ አለችው። በልጁ ምንም ትርፍ ላታገኝበት፣ በስሟ ላይጠራ፣ ላትኩራራበት፣ ሰርጉን ደግሳ ዓለሟን ላታይበት ቃል እየገባች ብቻ ልጅ ስጠኝ እያለች ተማጠነችው ደጉን እግዚአብሔርን። ጌታም እንዲህ የመሰለው ጸሎት ደስ ያሰኘዋልና ከአምስት ወንድ ልጆች የሚበልጥን ልጅ ሰጣት። ቃሉ መሬት ጠብ የማይልን ነቢይ ሳሙኤልን ሰጣት።

ችግራችን ትልቅን ነገር ያሰጠናል። ታሪካቸውን በ2 ነገሥት ምዕራፍ ሰባት ላይ የምታገኙት ከእስራኤል ጉባኤ የተገለሉ እነዚያ አራት ለምጻሞች በሰማሪያ ታላቅ ርሃብ በተከሰተበት ወቅት በከተማይቱ መግቢያ በር አጠገብ ተቀምጠው ነበር። በከተማዋ የሚኖረው ህብረተሰብ በርሃብ እያለቀ ባለበት ሰዓት ከህብረተሰቡ ተገልለው እንዲቀመጡ የተደረጉት እነርሱማ ርሃቡ እንዴት

አይጠናባቸው? ርሃቡ ከመከሰቱ በፊት የሚኖሩት ከከተማ በሚመጣላቸው ቸርነት ነበር። አሁን ግን ከተማውም ቸርነቱ ስላለቀበት ርሃቡ ግራ አጋብቷቸው ሁሉም ተደናግጠው ባሉበት ጊዜ ወደ ልባቸው በመመለስ እንዲህ ተባባሉ። *"እሰከንሞት ድረስ በዚህ የምንቆየው ለምንድነው? ታዲያ ወደ ከተማይቱ እንግባ ብንል በዚያም ርሃብ ስላለ እንሞታለን፣ በዚሁም ብንሆን ያው መሞታችን እንደሁ አልቀረም፣ ስለዚህ ወደ ሶርያውያኑ ሰፈር ዝም ብለን እንሂድ፣ ዝም ካሉን ሕይወታችን ትተርፋለች፣ ከገደሉንም ያው ሞቶ መገላገል ነው"* (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)።

ከዚያም መሸትሸት ሲል ተነስተው ወደ ሶርያውያኑ ሰፈር ሄዱ፣ ወደ ሰፈሩ ጥግ ሲደርሱም አንድም ሰው በዚያ አላገኙም። ለካስ እግዚአብሔር ሶርያውያኑ ፈርተው እንዲሸሹ ለማድረግ የሠረገሎችንና የፈረሶችን ድምጽ እንዲሰሙ አድርጎ ስለነበር እርስ በርሳቸው "እነሆ የእስራኤል ንጉሥ በእኛ ላይ አደጋ ለመጣል የኬጢያውያንን፣ የግብጻውያንን ነገሥታት ቀጥሮ አምጥቶብናል" ተባባሉ። ከዚያም ነፍሳቸውን ለማዳን ሲሉ ስንቃቸውን ሳይቀር የያዙትን አንዳች ነገራቸውን ሳይዙ እዚያው ጥለውት ተነስተው እግሬ አውጪኝ በማለት ሸሹ።

እነዚያም የእስራኤል ለምጻሞች በስፍራው ሲደርሱ የሚበላ አገኙና በልተው ጠገቡ፣ የሚጠጣውንም ጠጥተው ረኩ። ወደ ሶሪያውያኑ ድንኳኖች በመግባትም ያገኙትን ወርቅና ብር ሁሉ እየሰበሰቡ ደበቁ። በመጨረሻም ወደ ልባቸው ሲመለሱ በሰማርያ

የሚኖሩት ወገኖቻቸው ትዝ አሏቸውና እንዲህ ተባባሉ፡፡ ያደረግነው ትክክል አይደለም ዕለቱ የምሥራች ቀን ነው፤ እኛ ግን የራሳችን ብቻ አደረግነው፤ እስኪነጋም ከቆየን በደለኞች እንሆናለን፤ ስለዚህ ወደ ቤተ መንግሥት በፍጥነት ሄደን እንንገር፡፡ ከዚያም ሄደው የከተማይቱን መግቢያ በር ጠባቂዎች ጮኸው በመጥራት ወደ ሶርያውያን ሰፈር ገባን፤ እዚያም ከታሰሩ ፈረሶችና አህዮች በቀር አንድም ሰው አልነበረም፤ የማንም ድምጽ አልተሰማም፤ ድንኳኖቹም እንዳሉ ናቸው ብለው ነገሯቸው፡፡ የበሩ ጠባቂዎችም ይህንኑ አስተጋቡ፤ ዜናው በቤተ መንግስቱም ተሰማ፡፡

ንጉሡም በሌሊት ተነስቶ ለጦር አለቆቹ እንዲህ አላቸው፤ ሶርያውያን ያደረጉብንን እነግራችኋለሁ፤ መራባችንን ስለሚያውቁ መቼም መውጣታቸው አይቀርም፤ ከዚያም ከነሕይወታቸው እንማርካቸዋለን፤ እኛም ሰተት ብለን ወደ ከተማዪቱ እንገባለን በማለት በገጠር ለመደበቅ ከሰፈራቸው ወጥተዋል፡፡ ስለዚህ አሁን ነገሩን የሚያጣራ ሰላይ እንላክ ብሎ ጉዳዩን አስጠና፡፡ ሆኖም እንዳሰበው አለመሆኑን ሲረዳ ሕዝቡን ይዞ በመውጣት የሶርያውያኑን ሰፈር በዘበዘ፡፡

ብዙ ሰዎች ችግራቸውን እነርሱ አልቅሰውበት፣ ቤተሰባቸውም አልቅሶበት፣ ቤተ ክርስቲያንም አልቅሳበት እነርሱ ግን የሙጥኝ ብለው ይዘውት ይዞራሉ፡፡ በአገራችን በብዙ ቦታዎች ሰው ሲሞት የሚቹን ልብስ እና በሕይወት ሳለ ይገለገልባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ ያህል ጦሩን፣ ጠመንጃውን፣ ይዘው ለለቀስተኛው እያሳዩ

ህዝቡን ማስለቀስ፣ እንባ ማራጨት፣ ሙሾ ማውረድ እና ማስደርደር የተለመደ ነው፡፡ እነዚህ የሚቹ ቁሳቁሶች ሰውን ከማስለቀስ ያለፈ ተግባር የላቸውም፡፡ ሚቹን ሕያው አያደርጉትም፡፡ ጌታ እግዚአብሔር ችግሮቻችንን ማልቀሻ፣ ማስለቀሻ ሳይሆኑ መፍትሄ ማፈላለጊያና ወደ አዲስ ራዕይ መሸጋገሪያ እንድናደርጋቸው ይፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር በውሃ ላይ አንድንራመድ፣ በእሳት ውስጥ እንድንመላለስ፣ ይፈልጋል፡፡ ዝቅተኛ ክፍያ እየተከፈለው የሚኖር ሰው መቸገሬ ካልቀረ በከተማ አውቶቡስም ቢሆን ተመላልሼ እየተማርኩ ጎበዝ ተማሪ እሆናለሁ፤ ከሁለት ዓመት በኋላ የአሁኑ ኑሮዬ ይለወጣል ብሎ ያስባል፡፡

አንዲት ታሪኳን የማውቃት ሴት አለች፡፡ ይህች ሴት የማትሪክ ፈተና አልሆን ብሏት ተማርራ እንዲህ አለች፡፡ "አባቴ ይሙት ከአሁን በኋላ ማትሪክን የምታገሰው ለሁለት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ተፈትኜ ነጥብ አልመጣ ካለኝ ባል አግብቼ እኖራለሁ"፡፡ እንግዲህ ለዚህች ሴት ትዳር የሚለው ራዕይ የፈለቀው ማትሪክ ከሚባለው ችግር ውስጥ ነው፡፡

ጆኒ ኤሪክሰን የምትባል ሴት አለች፡፡ ጆኒ በደረሰባት የአካል ጉዳት ቀሪ የሕይወት ዘመኗን እግሮቿ የማይራመዱ፣ እጆቿም የማይንቀሳቀሱ ሽባ ለመሆን ተገደደች፡፡ ጆኒ አካል ጉዳተኛ ሆኖለሁና የእኔ ነገር አብቅቶለታል ብላ ተስፋ ቆርጣ አልተቀመጠችም፡፡ በአካል ጉዳተኛነቷም ቁጭ ብላ ተቀምጣ ርዳታ

መውሰዱን አልፈለገችም። ከዚህ ይልቅ እርሳስ በአፏ በመያዝ ስዕሎችን መሳል ጀመረች። በዚህም ህይወቷ መቀየር ጀመረ። ዛሬ ጆኒ "ጆኒ እና ጓደኞቿ" የተባለ አንድ በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚሰራ ግብረ ሰናይ ድርጅት በስሟ አቋቁማ በዓለም ላይ እንደ እርሷ ተመሳሳይ የአካል ችግር የደረሰባቸውን ጉዳተኞች በመርዳት ላይ ትገኛለች። እንደዚህ ያሉ ችግሮች ለትልቅ ነገር የሚያበቁን ይሆናሉ።

በአንድ ሥፍራ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ባልዬው ሥራ ያለው ሲሆን ሚስቱ ደግሞ የቤት እመቤት ናት። እነዚህ ሰዎች ልጅ ወለዱ። ሆኖም ልጁ እያደገ ሲሄድ መስማት የተሳነው ልጅ መሆኑ እየታወቀ መጣ። እንዲህ ዓይነቱ ነገር የወላጅን ቅስም የሚሰብር ክስተት ነው። ይሁንና እነዚህ ወላጆች ግን ላጋጠማቸው ሃዘን ስፍራ ባለመስጠት እናት ከልጇ ጋር መግባባት የምትችልበትን የምልክት ቋንቋ ለመማር ትምህርት ቤት ገባች። ከዚያም ትምህርቱ አጠናቃ ጨረሰች። ይሄ አስቀድማ ከልጇ ጋር ለመግባባት ይረዳኛል ብላ የተማረችው ትምህርት በኋላ ላይ እዚያው የተማረችበት ትምህርት ቤት ውስጥ በአስተማሪነት እንድትቀጠር የሥራ በርን ከፈተላት። ቀጥሎም ወደ ቤተ ክርስቲያኗ በመውሰድ የምልክት ቋንቋውን በመጠቀም መስማት የተሳናቸውን ህጻናት የወንጌል አገልግሎቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ አንድ የአገልግሎት ክፍል አስከፍታ ማስተማር ጀመረች። ከዚያም በምትኖርበት ከተማ ውስጥ መስማት የተሳናቸው ልጆች ያሏቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደዚያች ቤተ

ክርስቲያን ይዘው እንዲመጡና የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማስታወቂያ አስነገረች። በዚህም ምክንያት ብዙ የከተማይቱ መስማት የተሳናቸው ልጆች የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የመስማት ዕድል አገኙ። እኛ አገር "ይሄ የወላጆቼ ጣጣ ነው፤ የዘር እሮግማን ነው፤ እግዚአብሔርን ምን ብበድለው ነው ይህን ያመጣብኝ?" የምንለውን ችግር ጌታ ለዚህች ሴት የምትከበርበት የአገልግሎት በር አደረገላት። አንድ ቀን ወደ መንግስተ ሰማያት ስትሄድ እነዚህ ወንጌልን በምልክት ቋንቋ ያበሰረቻቸው ልጆች የደስታ አክሊሎች ይሆኗታል።

ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ቀን ዓርብ ምሽት ላይ በቤተ ክርስቲያናችን መድረክ ላይ ወጥታ አንዲት እህት ወንዶ ገነት ለሽርሽር ሂጂ በዚያ በኤች. አይ. ቪ. ኤድስ የተጎዱ ወገኖቻችን መንገድ ላይ ወድቀው በማየቴ እንቅልፍ ስለነሳኝ የሽርሽር ፕሮግራሜን አቋርጬ ተመለስኩ ብላ መስክራልናለች። ያን ዕለት ወንዶ ገነት ውስጥ ያየችው ነገር ዛሬ መላውን ሰሜን አሜሪካን እየዞረች ለእነዚህ የችግሩ ተጠቂ ለሆኑ ወገኖቻችን ርዳታ ለማሰባሰብ የነገሥታቱን ቢሮ እንድታንኳኳ እያደረጋት ነው ያለው። ለራሷ ሳይሆን ለሌሎች መትረፊያ መንገድ ራዕይ ሆነላት። ይሄ እንዴት ያለ ትልቅ ነገር ነው! ሰው የደረሰበት ችግር ወይ ለማኝ ያደርገዋል፤ አሊያም ለችግሩ እጅ አልሰጥም ብሎ ከችግሩ በላይ በመሆን ባለ ራዕይ ይሆንበታል።

ራዕይ ለመቀበል ምክንያት የሚሆነን የደረሰብን ችግር ብቻም ሳይሆን ያለን መልካም ነገርም ነው። መልካሙን ነገራችንን ትንሽ ነው ብለን ሳንንቀው ዛሬ ልናገለግልበት ብንነሳ ትልቅ ራዕይ ይወልድልናል። በአንድ ወቅት አንድ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ "ብዙ ሰዎች ለማገልገል ይፈልጋሉ፤ የሚፈልጉት ግን አማካሪዎች ቦርድ ውስጥ ገብተው ለማገልገል ነው" የሚል ጥቅስ ተሰቅሎ አይቻለሁ። እግዚአብሔር ስለ ሥራው አማካሪ ቦርድ አያስፈልገውም። ከሃሳብ መስጠት ያለፈ ራዕይ ያስፈልገናል። እጃችን ላይ እግር ማበሻ ፎጣ እና ውሃ ካለ ያ በቂ ነው።

ብዙ ሰዎች በጣም ትላልቅ ሃሳቦች አሏቸው። ትላልቅ ሃሳብ ማሰብ ቦራሱ ምንም ክፋት የለውም። ትልቅ ሃሳብ ከያዝን በኋላ ግን ለዚያ ሃሳብ የሚሆን፣ የሚመች ሌላ ሃሳብ ደግሞ ሊኖረን ይገባል። እግዚአብሔር እኔ እኮ እንዲህ አስቤ፣ አቅጄ ነበር፤ ይህንን እየጠበኩ ነበር እንድንል አይፈልግም። የእግዚአብሔር ድምጽ ሁልጊዜ ትልቅ ሃሳብ አለህ፤ ነገር ግን በእጅህ ምን ይዘሃል? ነው የሚለን። ሙሴ ግብጻዊውን ሰው እስክ መግደል ያደረሰው ለእስራኤላውያን ወገኖቹ የነበረው ትልቅ ቅንዓት ነበር። እግዚአብሔር ግን ሙሴን በግል መንገዱ ሳይሆን በራሱ መንገድ ወስዶ ካስተማረው በኋላ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ ነው ያለው።

ሙሴ ጥሪውን በቀላሉ አልተቀበለም ነበር። ለምን? ይህ ትልቅ ነገር ነው። መጀመሪያ እንኳን ቢሆን ለመደራደር ያመች ነበር። ሰው ከገደልኩ በኋላ!? አሁን ግን ሰው ገድዬ ጠፍቼ ከሸሸሁ በኋላ የት ሄደህ ነበርክ እባላለሁ የሚል ስጋት ይመስላል። ታዲያ ጌታ ምን አለው? ምንም ችግር የለም በእጅህ ምን ይዘሃል? አለው። በትር ይሆለሁ አለው። እሱን ይዘህ ወደ ፈርዖን ትሄዳለህ አለው።

በኋላም ህዝቡን ከግብጽ የባርነት ቤት ነጻ ካወጣቸው በኋላ ወደ ባህሩ ጥግ አመጣቸው። ሙሴም ባህሩን አይቶ ሲጮህ እግዚአብሔር አሁንም እንደገና በእጅህ ምን ይዘሃል? አለው። በትር ይዣለሁ ሲለው፤ ታዲያ ለምን ትጮሃለህ? በያዝከው በትር ባህሩን ምታው አለው። ሙሴም እግዚአብሔር እንደ ተናገረው ባህሩን በያዘው በትር ሲመታው ባህሩ ለሁለት ተከፈለ።

የእግዚአብሔር ልጆች ሆይ! እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከዚያች ትንሽ ነገር ጋር አብሮ ይቆማል። ምናልባት በልተን እንዳንሞት ብለን በእጃችን ያለችው በጣም ትንሽ ነገር ትኖረን ይሆናል። ይሁንና በዚያች ነገር ውስጥ የእግዚአብሔር እጅንዳ፣ ጉዳይ ካለበት እግዚአብሔር ከዚያ ነገር ጋር ይቆማል። ታዲያ እናንተስ በእጃችሁ ያለው ነገር ምንድነው? የእግዚአብሔር ጉዳይ ትልቅ ስለሆነ ትልቅ ነገር ስንጠብቅ ዕድሜያችን ሳንሰራው እንዳያልፍ። ምክንያቱም መጽሐፈ መክብብ 11፡4 ላይ *"ነፋሰን የሚጠባበቅ አይዘራም፣ ደመናትንም የሚያይ አያጭድም"* ይላልና። ይሄ ምን ማለት ነው? ብዙ የሚዘራው ዘር አለው፤ ነገር ግን የሚመችውን ጊዜ በመጠበቅ ጊዜው የሚያልፍበት ሰው ማለት ነው።

በውጪ ያሉት ሰዎች እንኳን "ዓለም ዘጠኝ ናት" ይላሉ። ምን ማለታቸው ነው? መቼም ቢሆን አስር አትሞላም ነው። እናም ምንጊዜም የተሳካ ነገር አይመጣም። የሚሳካ ነገር የሚመጣው እግዚአብሔርን አምነን እግዚአብሔር በሰጠን ራዕይ እንደ እግዚአብሔር ቃል ስንራመድ ነው። ያድነኛል፤ ባያድነኝም እንኳን ብለን ሊያጠፉን በሚችለው ነገር ውስጥ ታምነን ስንገባ ያንጊዜ የእግዚአብሔር ማዳን ይመጣል። የእግዚአብሔር አሰራር እንደዚህ ነውና እጃችሁ ላይ ምን አለ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለት ላይ ሠርግ ቤት ተገኝቶ እያለ እናቱ ማርያም ሰዎቹ ያዘጋጁት ወይን ጠጅ እንዳለቀባቸው ነገረችው። ይህን ጊዜ ጌታም "ባዶዎቹን ጋኖች ውሃ ሙሏቸው" አላቸው። እንደ ቃሉም ጋኖቹን ውሃ ሞሏቸው። ከዚያም መጫላታቸውን ሲነግሩት አሁን ቀድታችሁ ስጡ አላቸው። ጋኖቹ ውስጥ የተሞላው ውሃ እየተቀዳ ሲሰጥ ወይን ጠጅ ሆነ። ይህ እውነት ምንድነው የሚያስተምረን? ለትልቅ ራዕይ የምንወጣው እግዚአብሔር በእጃችን፣ በህይወታችን፣ በቤተሰባችን ውስጥ ያስቀመጠውን ትንሽ ነገር ከጌታ ጋር ይዘን እንጂ ትላልቅ ነገሮችን በመጠበቅ አይደለም። ስለዚህ ራዕይ የሌለው ቤተሰብ ደካማ፣ ግብ የሌለው፤ አቅሙን፣ ገንዘቡን፣ ጉልበቱን እየበተነ የሚኖር እና እየጠፋ የሚሄድ ቤተሰብ ነው የሚሆነው።

ይሁንና በቤተሰባችን ራዕይ ካለን ግን በጥሩ እጅ እንዳለ ፍላጻ ነን። እንዲህ ያለው ቤተሰብ ልጆቹ፣ የልጅ ልጆቹ በእግዚአብሔር ሃሳብ፣ ዓላማ ውስጥ የሚሄዱ ይሆናሉ። አንተ ከዚህ ዓለም ካለፍክ በኋላ ከአንተ በኋላ በሚመጣው በአንተ ዘር፣ በአንተ ትውልድ ውስጥ ለእግዚአብሔር ሥራ የሚጨክኑ ሰዎች የሚያድጉት በዚያ ራዕይ ውስጥ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሥራ የሚጀምረው ግን ዛሬ ከአንተ ነው። ዛሬ በትዳር ህይወታችን ውስጥ ባለ ራዕዮች፣ ባለ ጉዳዮች መሆን ስንጀምር፤ ነገ ያ እየተመነዘረ የሚታይ ይሆናል።

ምዕራፍ 7

ራዕይ ያለው ቤተሰብ ምሳሌነት

ምዕራፍ ሰባት

ራዕይ ያለው ቤተሰብ ምሳሌነት

የእግዚአብሔር ቃል በዕንባቆም ምዕራፍ ሁለት ከቁጥር አንድ ጀምሮ እንዲህ ይላል፡፡

“በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፤ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ እቆያለሁ፤ ምን እንደሚለኝ፤ ለክርክሩም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ፡፡ እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰ፤ በቀላሉ እንዲነበብ፣ ራዕዩን ጻፈው፤ በሰሌዳም ላይ ቅረጸው፡፡ ራዕዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፤ ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤ እርሱም አይዋሽም፤ የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤ በእርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም”፡፡ (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ቤተ ክርስቲያናችን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴት እንዳሏት ሁሉ በቤተሰባችንም እንዲሁ ሊኖረን ያስፈልገናል፡፡ ቤተሰብ እንደ ቤተሰብ ለሚቀጥለው አምስት ዓመታት ራዕይ ሊኖረው ይገባል፡፡ ባል፣ ሚስት፣ ልጆች ተቀምጠው ምንድነው መሆን የምንፈልገው? ያን መሆን የምንፈልገውን ማግኘት እንድንችል ደግሞ ምን ማድረግ ይገባናል? እንዴትስ ነው ወደዚያ የምንደርሰው? ተባብለው እንደ ቤተሰብ ሊይዙት የሚገባቸው ራዕይ መኖር አለበት፡፡ የቤተሰብ አባላት ተቀምጠው መነጋገራቸው በጣም ትልቅ ለውጥ ነው

የሚያመጣው፡፡ ለምን የሰባት ዓመት ልጅ አይሆንም ወደፊት እንዲህና እንዲያ እናደርጋለን ብለን በምንነጋገርበት ጊዜ፣ በልጆቹ ልብ ውስጥ ትልቅ ተጽዕኖና ጉጉት ነው የምናሳድረው፡፡ እነርሱም በአብሮነት ከጎናችን መሰለፍ ይችላሉ፡፡ ይህንን የምንሰራው ቤተሰቡ ወደፊት መሆን የሚፈልገውን ነገር እንዲሆን ለማገዝ ስለሆነ ልጆቹ ይገባቸዋል፡፡

ልጆች ስንቀጣቸው ለምን እንደምንቀጣቸው፤ ስናበረታታቸው ደግሞ ለምን እንደምናበረታታቸው ይገባቸዋል፡፡ የጋራ ምክክር ነውና የጸና ነገር ይሆናል፤ እግዚአብሔርም በመካከላችን ያንን መባረክ ይቀለዋል፡፡

ወደ አንድ የቤተሰብ ታሪክ እወስዳችሁና ከዚያ ላይ የቤተሰብ ራዕይ እንዲኖረን እናንተን ማደፋፈርና ማነሳሳት እፈልጋለሁ፡፡ በመጀመሪያ ነገሩ ስለሆነበት ዘመን ላስታውሳችሁ፡፡

ታሪኩ የተከሰተው ቀዳማዊው አርጤክስስ ከሕንድ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በመቶ ሃያ ሰባት አገሮች ውስጥ ገዥ ሆኖ በሚያስተዳድርበት ዘመን ነው፡፡ ይህ ታሪክ የተፈጸመበት ትክክለኛ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች የሚናገሩት በመጽሐፈ ዕዝራ ምዕራፍ ስድስት እና ምዕራፍ ሰባት መካከል ባለው ሰባት ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የነበረው አባቱ ዳርዮስም ሆነ አሁን ስሙን የጠራነው አርጤክሲስ ብዙ ጊዜ አገሮችን በወረራ እየያዙ ሲገዙና ሲያስገብሩ የሚያደርጉት ምንድነው? የአገሬውን ሰዎች ከትውልድ ቀያቸው አፈናቅለው በስደት ወደ ሌላ አገር አግዘው ወስደው ያሰፍሯቸው ነበር፡፡ በዚሁ መሠረትም ከእይሁድ ምድር ተማርከው ሱሳ ወደምትባል የፋርስ መንግስት ግዛት ከተማ ውስጥ እንዲሰፍሩ የተወሰዱ አይሁዳውያን ነበሩ፡፡ በዚያ ብዙ

አይሁዳውያን ይኖሩ እንደ ነበር የዓለም ታሪክ ሳይቀር ይመሰክራል። እንዲህ በምርኮ ፈልሰው ከሄዱ ቤተሰቦች መካከል መርዶክዮስ የተባለ ከብንያም ነገድ የሆነው የቂስ የልጅ ልጅ አንዱ እንደነበር መጽሐፈ አስቴር ይነግረናል።

መርዶክዮስ በምርኮ በሚኖርበት በዚህ ጊዜ ቤተሰቡን ልክ ዛሬ ብዙ ሰዎች በልዩ ልዩ ምክንያት ከትውልድ አገራቸው ወጥተው በባዕድ ምድር እንደሚኖሩት ዓይነት ኑሮ እርሱም እንደዚህ ተማርኮ በሰው አገርና ምድር በማያውቀው ባህልና ቋንቋ ውስጥ ለመኖር ተገዶ ነበር። ፍልሰት ጥንትም የነበረ ታሪክ ቢሆንም፤ ይሁንና የእነዚህን አይሁዳውያን ፍልሰት ልዩ የሚያደርገው ነገር ምን እንደሆነ እንድንመለከት ግን እፈልጋለሁ።

መርዶክዮስ አባትና እናቷ ከሞቱባት በኋላ እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ ሊያሳድጋት የወሰዳት ሀዳሳ ወይም አስቴር የተባለች የአጎቱ የአቢካኢል ልጅ ነበረች። መርዶክዮስ ይህችን ልጅ ይዞ በሚኖርበት ጊዜ እንደ አንድ ቤተሰብ የተለየ የሚያደርጋቸው ነገር ነበራቸው። ይህ ቤተሰብ በግዞት ተማርኮ ስለተወሰደ ብቻ ዝም ብሎ ለመኖር ያህል የሚኖር አልነበረም። ቤተሰቡ እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ ለጌታ ብቻ የሚሰግድ ቤተሰብ ነበር። ይህ ደግሞ የጠንካራ ቤተሰብ ባህርይ አንዱ ምልክት ነው።

አገሩ ሁሉ ለሐማ በሚሰግድለት ሰዓት መርዶክዮስ ግን "በህጹም አልሰግድም!" እንዳለ ታስታውሳለችሁ። ለምንድነው አልሰግድም ያለው? ስንል ገና ከልጅነት ዕድሜው አንስቶ "ለጌታ ለአምላክህ ብቻ ስገድ" የሚለውን እና ስግደት እና አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በልቡናው የሰረጸ ትምህርት ስለነበርና ቤተሰቡም ለእግዚአብሔር የተለየ ቤተሰብ ስለነበረ ነው። ሌላው ይህ

ቤተሰብ እርስ በእርሱ የተያያዘ ቤተሰብም ነበር። ይህች ልጅ እናት አባቷ በሞቱባት ጊዜ እርሷን ማሳደጉ የእኔ ኃላፊነት ነው ብሎ ወስዶ እንደ ራሱ ልጅ በመልካም ስርዓት እንዳሳደጋት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (መጽሐፈ አስቴር 2፡7)። ከዚያ በኋላ ደግሞ የእግዚአብሔርን ዓላማና ሃሳብ ሲነግራት መቀበሏ ስለ ህዘቧ ሽክም እንዲኖራት ማድረጉ ስለ ጾም ጸሎት ማወቋ ልዩ ልዩ ነገሮች ስትወስዱ እንደ አንድ ቤተሰብ የተባበረ ቤተሰብ እንደነበር ነው መረዳት የምንችለው። ይሄ ደግሞ የጠንካራ ቤተሰብ ሁለተኛው ባህርይ ነው።

እግዚአብሔርን የሚያመለክ፣ እርስ በርሱ የተያያዘ፣ ደግሞም ለመኖር ብቻ ብሎ የማይኖር፣ ነግር ግን በልባቸው ውስጥ የሚጠባበቁት አንድ ተስፋ ያለው ይህ ቤተሰብ አይሁዶች እንዲጠፉ የሞት አዋጅ በታወጀባቸው ጊዜ መርዶክዮስ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ላለችው ለአስቴር የላከባት መልዕክት ምን ነበር? እግዚአብሔር ለአይሁድ መዳንን ከሌላ ስፍራ እንደሚያመጣላቸው ነበር የነገራት። መርዶክዮስ ይህ መልዕክቱ የሚያመለክተን የአይሁድን መዳን የሚጠባበቅ ሰው እንደነበር ነው። በመቀጠልም "እንቺስ ደግሞ እግዚአብሔር ወደ መንግስሥት ያወጣሽ ለእንዲህ ዓይነቱ ቀን አስቦሽ እንደሆነ ማን ይውቃል?" ነበር ያላት። መርዶክዮስ አስቴርን ለትልቅ ነገር ነበር የሚጠብቃት። በሌላ አነጋገር አስቴርም ሆነች መርዶክዮስ ወይም ያ ቤተሰብ በልባቸው ውስጥ የነበረው ራዕይ በልቶ ከመኖር ያለፈ እንደ ነበር እንመለከታለን።

ዘመኑ ምንም የከፋ ቢሆን፣ ምንም የማይመች ሕይወት ብንኖርምና በብዙ በማይመቹ ሁኔታዎች ውስጥ ብናልፍም እንኳን፣ በልባችን ውስጥ ላቅ ያሉ ራዕዮችን ለማሳብ ግን ምንም የሚከለክለን ነገር አይኖርም። በእኛ ከሚኖረው ከእግዚአብሔር መንፈስ የተነሳም

በእግዚአብሔር ሃሳብ፣ በእርሱ አጀንዳ መጠመድ እንችላለን። እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠን ሕይወትና መንፈስ የተነሳ ግን እግዚአብሔርን ለማምለክ የመረጠና የቆረጠ ቤተሰብ መሆን እንችላለን። የእግዚአብሔር ሰው ኢያሱ "እኔ እና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን" እንዳለው እኛም ይህንን ከማለት የሚከለክለን ነገር አይኖርም። እያንዳንዳችን በነፍስ ወከፍ ያለንን ቤተሰባዊ ሀብረትና አንድነት ከመያዝ የሚከለክለን ነገር የለም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ሆኖ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ትልቅ ነገር ማሰብ ይቻላል። ወሳኙ የምርጫ፣ የውሳኔ ጉዳይ እንጂ፣ የምንኖርበት ስፍራ አይደለም። እግዚአብሔር ኢትዮጵያም ሆነ ጃፓን ቢያኖረኝ እርሱን ለማምለክ ምርጫውና ውሳኔው የእኔ ነው። ቤተሰቤን በሀብረት ለመያዝ ምርጫው የእኔ ነው። የእግዚአብሔርን ትላልቅ ራዕይ ማሰብ፣ ለእግዚአብሔር የሚጠቅም ዕቃ ለመሆን መመኘቴና በውስጤ ያንን ነገር ማርገዙ የእኔ ምርጫ ነው።

እነ መርዶክዮስ ዝም ብለው ተራ ቤተሰብ ብቻ አልነበሩም፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፣ ተስማምተውና ተደጋግፈው በሀብረትና በአንድነት የሚኖሩ፣ ደግሞም ለየት ያለ ራዕይና ባህርይ የነበራቸው ነበሩ።

ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነት ሕይወት ይኖር የነበረው ይህ ቤተሰብ ግን ድንገት አንድ ችግር ገጠመው። ታሪክ አዋቂዎች እንደሚሉት ንጉሥ አርጤክሲስ ከአባቱ ከዳርዮስ የሚለይበት አንዱ ባህርይው ዳርዮስ ሌላውን አገር በወረራ መያዝና ማስገበር፣ የግዛት ድንበሩን በማስፋት አገሮችን ጠቅልሎ መያዝን የሚወድ ዓይነት አባት ሲሆን፣ ልጅዬው አርጤክስስ ግን እኔ ግዛት ማስፋፋት ምን

ያደርግልኛል ዓለሙን በሙሉ ከምገዛ ያለኝን ከተማዬን ይባርክልኝ ብሎ ሱሳንና ሌሎች ከተሞችን ማሰማመርና ማስዋብ ራዕዩ የነበረ ሰው ነበር።

ይህን የታዘቡ የንጉሥ አርጤክስስ የጦር አዛዦች ግን "ግሪክን ብቻ ወርረን እንያዝና ከዚያ በኋላ ትቀመጣለህ" እያሉ ይጎተጉቱት እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ። አርጤክሲስ የጦር አዛዦችን ምክር ትቶ ግሪክን ለመውረር ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ የጦር አበጋዞቹ ግን ግድ አሉት። በዚህን ጊዜ የልባቸውን ፈቃድ ለመሙላት ሲል እሺታውን ገለጸላቸው። በመጨረሻም ግሪክን ብቻ ለመውረር ዝግጅት ከተደረገ በኋላ ኃይለኛነቱን ለማሳየትና የጦር ሠራዊቱን ልብ ለውጊያ ለማነሳሳት መቶ ሰማንያ ቀን የሚፈጅ ትልቅ ግብዣ አደረገላቸው። መቶ ሰማንያ ቀን ሙሉ እየበሉ እና እየጠጡ ቤተ መንግስት ውስጥ ተቀመጡ። መቶ ሰማኒያ ቀን ሙሉ ዝም ተብሎ ሲበላና ሲጠጣ የህክምናው ሳይንስ ይሄንን ምን እንደሚለው አላውቅም። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ግን *"የመንግስቱን ሰፊ ሃብት፣ የግርማውን ታላቅነትና ክብር አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ሙሉ አሳያቸው"* ይላል *(አስቴር 1:4)*።

ከዚያም ለሹማምንቱ፣ ለመኳንንቱ እና ለጦር አዛዦቹ መቶ ሰማንያው ቀን ይህን ድግስ ካደረገ በኋላ ደግሞ በሱሳ ግንብ ለነበሩት ከትንሽ እስከ ትልቅ ላለው ሕዝብ ሁሉ በቤተ መንግስቱ ውስጥ ዙሪያውን በአትክልት በተከበበው አደባባይ ሰባት ቀን የፈጀ ግብዣ አደረገ። ንጉሡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ያህል እንዲያቀርቡለት አዝዞ ስለነበር ሁሉም ሰው እንደፈለገው ይበላ እና የወይን ጠጅም ይጠጣ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ግብዣ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ በሚደረገው የአሜሪካ ፕሬዘዳንቶች ምርጫ እንኳን ተደርጎ አይታወቅም። በሌላ በኩል ደግሞ ንግስቲቷም በበኩሏ ግሪክን

ለመያዝ ለጦርነት ልወጣ ነውና ለዚያ ፈሽታ እንዲሆን በሴቶች እልፍኝ አዳራሽ ውስጥ ሴቶች እየመጡ እንደፈለጉ ይብሉ፣ ይጠጡ ብላ ድግስ ደገሰች።

መቼም ወይን ጠጅ ከተጠጣ ሞቅታ አይቀርምና ንጉሡ ሞቅ ሲለው ቆንጆይቱ ንግሥት አምራ ደምቃ እንድትመጣ ብሎ ላከባት። ሆኖም ንግሥቲቷ የንጉሣን ጥሪ እንደ ሰማች ቁርጥ ባለ ቃል "አልመጣም!" ብላ ላከችበት። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማነብበት ጊዜ ሁልጊዜ ጥያቄያቸው ትዝ የሚለኝ ሰዎች አሉ። አንደኛው ጥያቄ "ንጉሡስ ቢሆን መቶ ሰማንያ ቀን ሙሉ ሲበላ፣ ሲጠጣና ሲሰክር ከርሞ ነይ ማለቱ ምንድነው? ስካሩን ተቆጣጥሮ አይቀመጥም ነበር እንዴ?" የሚል ሲሆን፤ ሌላው ጥያቄ ደግሞ "እንዴ እርሷ እኮ ሚስቱ ነች ነይ ባላት ቁጥር "እቤት! ብላ መሄድ ነው እንጂ፤ እምቢ ማለትን ምን አመጣው?" የሚል ነው። ይሁንና ስለ ጥያቄ ካነሳን እኔም አንድ ጥያቄ ላንሳ። እስቲ ንገሩኝ የመጀመሪያው መሆን ያለበት ነገር የትኛው ነው፤ ይውደዳት የሚለው ነው ወይስ ትታዘዘው? አንዳንዶች "እርሷ መታዘዝ ነው ያለባት"፤ ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ "እንዴ እርሱስ ቢሆን ለምን አላከበራትም? ባሻው ጊዜ ለባብሰሽ እንደ ጥሩ ሞዴል በህዝብ ፊት ቅረቢ የሚላት?" እንደዚሁ ሦስተኞቹ ደግሞ "የቤቱ ራስ እርሱ ነውና ባሻው ሰዓት ነይ ሊላት ይችላል። መብቱ ነው"። "ለምን? ንግሥቲቱስ በተጠራች ቁጥር በሰካራም ፊት የመቆም ግዴታ አለባት እንዴ?" (ይህንን የሚሉት ሴቶች ናቸው) እያሉ ይከራከራሉ።

እዚህ ላይ ማስተዋልንና ጥበብን የሚጠይቅ ነገር ይመስለኛል። እንዴ ወንድሞች ሞቅ ስላለን እኮ መወሰን የለብንም! ሰውዬው ሞቅ ባለው ጊዜ ለምን ይወስናል? ምናለበት ያንን የስካሩን

ጊዜ ቢያሳልፈው? እርሷስ ደግሞ ግትር ከምትል ለጊዜው እሺ ብላ ታዝዛ ስካሩ ከለቀቀው በኋላ ለብቻው ስህተቱን በጥበብ ብትነግረው?

ችግሩ እርሱም የባልነት መብቱን ያለ አግባብ ተጠቀመበት እርሷም እንደዚያው የሴትነቷን። ስለዚህም ነገሮች ከመስመር ወጡና ችግር ተፈጠረ። እርሱ የሚስትነቷን ክብር ቢጠብቅላት፤ እርሷም የአገርና የቤተሰቧ መሪ ነውና እንደሚገባው ብትንከባከበው ሁለቱ ሚዛናዊ በሆነ ነበር። ሰላምና ደስታ ያለው በመቀባበል ውስጥ ነበርና።

ሆኖም የንግሥቲቱ ምላሽ ንጉሡንም ሆነ መኳንንቱንና ሹማምንቱን አበሳጨ። ስለዚህም ንግስት አስጢን ከእቴጌነቷ ትውረድ ተባለና ወረደች። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ታሪክ የመጨረሻ ክፍል በሌላ የታሪክ መጽሐፍ እንጂ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ አታገኙትም። ንጉሡም ወደ ጦርነቱ አመራ። ያ ሁሉ በልቶና ጠጥቶ እየፎከረ ወደ ጦርነት የሄደ ሹማምንትና መኳንንት ከግሪክ ጦር ጋር ተዋግቶ ተሸንፎ ተመለሰ። ንጉሥ ከሚስቱ ጋር በጠብ ተለያይቶ ወጥቶ ምን ማሸነፍ ይኖራል?

ሰው በቤቱ ውስጥ ራዕይ ካጣ፣ በእግዚአብሔር መንፈስና ሃሳብ መመራት ካልቻለና ጽድቅ ከሌለበት፤ እነዚህ ጥንካሬዎች በውስጡ ከሌሉ ጓዳው መፍረስ ጀምሯልና ውጪ በሚኖረው ጦርነት ተሸንፎ መምጣቱ አይቀሬ ነው።

መጽሐፈ አስቴር ምዕራፍ ሁለት እንደሚነግረንም ንጉሡ ቁጣው ከበረደለት ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ ብቸኝነቱ ስለከበደው በንግስት አስጢን ላይ የወሰደውን እርምጃ መለስ ብሎ ሲያስበው አጥፍቻለሁ አለ። እናም ምን ማድረግ እንደሚሻል አማካሪዎቹን

ሲያማክራቸው አሁንማ በቃ እርሷ ሂዳለች፣ ከተማ ውስጥ ካሉት ቆንጃጅት ይፈለጉና ለንጉሥ ጠባቂ ይሰጡ። ለተወሰነ ጊዜ ያህልም ሲዋቡ ይቆዩ። ከዚያም ከእነዚያ ቆንጃጅት መካከል ደስ ያለችህን መርጠህ ትወስዳለህ አሉት። ንጉሡም በሃሳቡ ተስማማ። ከዚያም የአርጤክስስ መንግስት ቆንጆይቱን ሴት ለመምረጥ መመሪያ አውጥቶ ቆንጆ በየሰፈሩ እየተፈለገ ይለቀም ጀመር።

በምድር ያለው መንግስት ቆንጆ ፍለጋ በየሰፈሩ ሲሄድ በሰማይ ያለው እግዚአብሔርም በእርሱ መለኪያ ለዚያ ቦታ የምትመጥነዋን ሴት መርጦ አዘጋጀ። ሁለቱም ፍለጋዎች በአንድ ጊዜ የሆኑ ቢሆኑም፣ የእግዚአብሔርን ነገር ግን ማንም ያስተዋለው አልነበረም። በምድር የተፈለገችው ቆንጆ ሴት ስለነበር ብዙ ራሳቸውን እየሰጡ፣ ለውድድር የገቡ፣ በዘመድ አዝማድ የተመረጡ የተዋቡ ሴቶች ለአስራ ሁለት ወራት እየተቀባቡ ለመዘጋጀት ወደ ንጉሡ ቤት ገቡ።

በሰማይ የነበረው የንግስትነት መለኪያው ግን ከዚህ የተለየ ነበር። 2 ዜና 16:9 ላይ *“. . .ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ላይ ይመለከታሉና”* የሚል ቃል አለ። አያችሁ! እግዚአብሔር ከላይ ሆኖ ያያል። የሚያየው ግን ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ነው። እግዚአብሔር የሚያየው ውጪኛውን ነገራችንን ሳይሆን የውስጣችንን ነው። እግዚአብሔር በውስጥ ልቡ፣ በመንፈሱ፣ በሃሳቡ ከእርሱ ጋር ትክክል የሆነውንና በእርሱ መንገድ የሚመላለሰውን ሰው ሊያድነው፣ ሊተክለው፣ ሊጠቀምበት እና ሊባርከው ዓይኖቹ እንዲህ ዓይነቱን ሰው ሊያዩ ወደ ምድር ይመለከታሉ።

ለካስ እግዚአብሔርን በቤቷ ውስጥ ማምለክ የተማረችው አስቴር ከሞት በኋላ ላለው ደህንነት ብቻ ሳይሆን አሁን በምድር

የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ማዳን ለህዝቡ እንዲትሰጥ ነው። ለካንስ ያ ቤተሰብ እርስ በእርሱ ይደጋገፍ፣ ይያያዝ እግዚአብሔርን የሙጥኝ ብሎ ሕጉን ይከተል የነበረው እንዲህ ለአይሁድ ትልቅ ረድኤት ሊሆን ነው!

እንዲህ ላለ ትልቅ ቀን መተባበር እና መቆም እንዲችል ነው ለካስ ቁንጅናው የተሰጣት። እግዚአብሔር ቁንጅናውን የሰጣት ለፎቶግራፍ መነሻ ሳይሆን እርሷን ተጠቅሞ ህዝቡን ለማዳን ነው።

እናም አስቴር ለጠባቂዋ ለሄጌ ከመሰጠቷ በፊት መርዶክዮስ አትቸኩይ፣ ልባምና አስተዋይ ሴት ሁኚ። ንጉሡም ሆነ ሌላ ሰው ማንነትሽን ቢጠይቁሽ እንኳን የማን ወገን መሆንሽን እንዳትነግሪ ብሎ ነገራት። እግዚአብሔር ለዚህ ነገር አድሎሻልና ያንን ለመያዝ ተዘርጊ አላት።

ለእኛ ጥቅም፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጡ መልካም አጋጣሚዎች በደጃችን ሲያልፉ አፈፍ አድርጎ መያዝ የሚቻለው እኮ እግዚአብሔር ዓይናችንን ሲከፍት ነው። ስንት እና ስንት የበረከት ከረጢቶች ሸው እያሉ በአጠገባችን ሲያልፉ ሳናያቸው ቀርተን አምልጠውናል! እንደ አስቴር አፋችንን መቆለፍ አቅቶን የማይመለከተን ጉዳይ ውስጥ እየገባን ስንለፈልፍ፣ ያልተጠየቅነውን ስናወራ ምስጢርን የባቄላ ወፍጮ አድርገን ስንዘከዝክ ብቻ ብዙ ዕድሎች አምልጠውናል።

እንደ ቤተሰብ ስንመካከር፣ ስንጸልይ ልባችንን በእግዚአብሔር ሃሳብ አሳርፈን እርሱን እያመለክን በየቀኑ ጌታ ሆይ እያልን የእርሱን አጀንዳ አንድ ልብ አንድ ሃሳብ ሆነን ለማገልገል እግዚአብሔርን እየጠበቅን ሳለ እግዚአብሔር መታሰቢያ ያለባቸውን ዕድሎችን

በአጠገባችን የሚያሳልፍበት ቀንና ጊዜ አለው። እነዚያን ዕድሎች የሚያገኛቸው ግን አስተዋይ የሆነና ዓይናቹ የተከፈቱለት ሰው ነው።

መርዶክዮስ ዓይናቹ የተከፈቱለት ሰው ነበር። ንጉሡ ቆንጆ ሚስት ይፈልግ በነበረበት ወቅት አስቴርን ወደ ውድድሩ ላለማስገባት ደንቃራ የሚሆኑ ብዙ ጥሩ፣ ጥሩ ምክንያቶች ነበሩት። የአገሩ ዜጋ ሳይሆን ከምድሩ ላይ በግዞት ተነቅሎ በውርደት የመጣ ህዝብ ወገን ነው። ቋንቋው፣ ባህሉና እምነቱ ቢሆን ከአገሬው ህዝብ ይልቁንም ከንጉሡ ጋር የሚገጥም አልነበረም። ደረጃውም ቢሆን ለዚያ የሚመጥን አልነበረም። ለዚያውስ ለቤተ መንግሥት ወግ የሚያበቃ ማንነት የት አለውና? መርዶኪዮስ ግን ውስጡ እነዚህን ሁሉ መመዘኛዎችን አላስተናገደም። ብቻ ለንጉሡ ቆንጆ ይፈለጋል ሲባል ፈጥኖ ያንን ዕድል የራሱ ለማድረግ አስቴርን "እግዚአብሔር ይህን ዕድል ለምን እንዳመጣው ማን ያውቃል? ሂጂ ግቢ! ቀጣይ ዓላማው ምን እንደሆነ እርሱን ራሱን እንጠይቀዋለን" ብሎ ላካት።

አስቴርም የመርዶክዮስን ምክር እንደ ዋሣ ሳትመከተው አጋጣሚውን ተጠቀመችበት። ራሷን መግዛት የቻለች ሴት ነበረችና የማን ወገን መሆኗን ሳትገልጥ አስተውላ ተራመደች።

ከአስራ ሁለት ወራት ቆይታ በኋላም በንጉሥ ፊት ለመቅረብ ተጠርታ ወጣች። አስቴር ብዙ ነገሯ ተለውጧል። ከአገሯ ስትወጣ የነበራት ስም ሐደሳ ነበር፤ አሁን ግን በዚያ አገር ስም አስቴር ተብላለች። የአገሬውን ቋንቋ እና ባህል ተምራለች፤ የዚያን አገር የውበት ማጋጌጫዎችን ሁሉ ለብሳ ተውባለች። ልቧ ግን እንደ ተጠበቀ ነው።

አስቴር ከእርሷ በፊት ብዙ ቆነጃጅት ተጠርተው ሄደዋል፤ ነገር ግን አንዳቸውም ወደ ንጉሡ ዘንድ ዳግመኛ አልተጠሩም። እርሷም ተራዋ ደርሶ እስከምትጠራ ሰዓት ድረስ በልቧ ስንቱ ሃሳብ ይመላለስ እንደነበር ማን ባወቀ። ይህች ልጅ ምርኮኛ፣ የአይሁድ ወገን፣ የሙት ልጅ እንደሆነች ማን ባወቀ። ይሁንና እግዚአብሔር ያለው ስለሚሆንና እርሱ ሊያደርግ በልቡ ያሰበውን ሊከለክል የሚችል ማንም ስለሌለ ይህች ልጅ ተራዋ ደርሶ ስትጠራ የእግዚአብሔርን ስም፣ ጸጋና ምህረት ለብሳ ልክ የዚያው አገር ሰው፣ ከመኳንንት ቤት፣ እንዳች የጎደላት ነገር እንደሌላት ሴት ሆና ቀጥ ብላ ወደ ንጉሡ አደባባይ ወጣች። ንጉሡም ሲያያት ወደዳት። መረጣትም።

ከእርሷ በፊት የነበሩት ቆነጃጅት በሙሉ በልጠው ለመገኘትና ለመጠራት ሲሉ ግምጃ ቤት ውስጥ ገብተው ያለ የሌለ ወርቅ ሲጭኑ፤ አስቴር ግን ያ የሴቶቹ ቤት ጠባቂ ከሰጣት በቀር ሌላ ምንም አልተጠቀመችም። በመጨረሻም ከእርሷ በቀር ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራች ሴት የለችም። ወገኖቼ! እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ያለችን ትንሿ ነገር ትበቃናለች።

ሰው እግዚአብሔር ከመረጠው የትም ይደርሳል። ሰው በልቡ የእግዚአብሔር ራዕይ ካለው፤ አሜን የሚልበት ሃሳብ ውስጥ ካለ፤ እግዚአብሔርም እሰይ የሚልበትን ነገር በውስጡ ካረገዘ የትም ይደርሳል። ከልካይ አይኖርም። የእግዚአብሔር የአምላካችን ስም ብሩክ ይሁን!

ታዲያ ንጉሡ ለሁለተኛ ጊዜ ጠርቷት ንግስት አድርጎ ሹሟት ከፍ ብላ ስትቀመጥ አጎቷ፣ ቤተሰቧ እንዴት ደስ ይለው! አብረው እንደ ጸለዩት፤ እርሱ ሲያስተምራት እርሷ እህ! ብላ እንደ ሰማችውና ሲያዛትም እንደ ታዘዘችው፤ ስትጠየቅ እንደ መለሰችለት

በመጨረሻም "እቴጌ" ተብላ ንጉሡ አጠገብ በዙፋን ላይ ስትቀመጥ አብረው ከበሩ። ራዕዩ እውን ሲሆንም በጋራ ሐሴት አደረጉ።

ሰው እግዚአብሔር ራዕይ ሲሰጠው፤ ይህንን ሥራ፣ ስራ ብሎ ሲነግረው ከእግዚአብሔር ከሰማ አይቆምም። ይሁንና ይህን ከማይወደው ከክፉው ተቃውሞ አለበት። አስቴር በዙፋን ላይ ስትቀመጥ ያየ ጠላት ተናደደ፣ ተበሳጨ፣ መንግስቱም ተናወጠ። ስለዚህም ከእግዚአብሔር ሰምተናል፣ ራዕይ አለን፣ ጌታ ነግሮናል የሚሉትን አጎቷንና አስቴርን እንዲሁም ወገናቸው የሆነውን ህዝብ ለማዋረድ ሰይጣን ሁለት ወጥመዶችን አዘጋጀና ከአንዱ ቢያመልጡ ከሌላው አያመልጡኝም ብሎ እርግጠኛ ሆነ።

የመጀመሪያው ወጥመዱ እቴጌይቱን ለንግሥና የመረጣትን ንጉሥ መግደልና እርሱን ከገደለ በኋላም ቀጥሎ እርሷን ማስወገድ ነበር። ስለዚህም ንጉሡን ለመግደል የራሱን ሰዎች አስነሳ። እነዚህ ሰዎችም ንጉሡን ለመግደል ተመካክረው ከጨረሱ በኋላ ይህ ሴራቸው ንጉሡ ደጅ በሚቀመጥ አንድ ሰው ጆሮ ገባ። ነበዝ ንጉሥን የሚያከል ሰው ለመግደል ስታስቡና ስትዶልቱ እንዲያው ግድግዳውን ሁሉ በብረት አትገደግዱትም! ይህንን ሴራ ግን ሁልጊዜ ከንጉሡ ደጃፍ የማይጠፋ አንድ ሰው እንደ ዋዛ ሰማውና ነገራቸው ተገለጠባቸው፤ ሴራቸውም ከሸፈ። ይህንን ያደረገው እግዚአብሔር ይመስለኛል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የላካቸውን፣ በስፍራው ላይ ያስቀመጣቸውን ሰዎች ይጠብቃቸዋልና ነው።

እግዚአብሔር ወደ አብርሃም በእርጅና ዕድሜው ላይ መጥቶ "ዘርህን አበዛዋለሁ ካለው በኋላ፤ . . .በእኔና በአንተ፣ ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር ከትውልድ እስከ ትውልድ የዘላለም ኪዳኔን

እመሠርታለሁ" (ዘፍጥረት 17፡2,7) ስላለው ልጅ እስኪወልድ ድረስ ርሃብ ቢነሳ፣ ጦርነት እና ችግር ውስጥ ቢገባም የተናገረውን ቃሉን በመጠበቅ ጥበቃ አድርጎለታል። አብርሃም ወደ እግዚአብሔር የተሰበሰበው በመቶ ሰባ አምስት ዓመት ዕድሜው ነው። እግዚአብሔር ቃሉን ብቻ ሳይሆን እኛንም ይጠብቀናል። እግዚአብሔር ሁሉን መጠበቅ የሚችል አምላክ ነውና ይህንን ባለ ራዕይ ቤተሰብ ከፍ አድርጎ ባስቀመጠበት ቦታ መጠበቅ ስለፈለገ ንጉሡ ለመግደል የተዶለተው ሴራ ይፋ እንዲወጣ አደረገ። ከዚህ የተነሳ ንጉሡም ሆነ ንግስቲቱ ከመጀመሪያው ወጥመድ ተረፉ።

ሰይጣን ይህ ሴራው እንዳልተሳካለት ባወቀ ጊዜ ደግሞ ሁለተኛውን ወጥመድ አዘጋጀ። ይህም ንጉሡ ሳያውቅ፤ ለንግስቲቱ ጠላት የሆነውን እና ሐማ የተባለውን ሰው ከሌሎች መኳንንቶቹ ሁሉ ከፍተኛውን ሥልጣን በመስጠት አከበረው። መቼም ሰይጣን መልካም እና በጎ በሚመስል ሃሳብ የሰዎችን ልብ ማነሳሳት ይችላልና፤ የንግስቲቱን ጠላት ከፍ፣ ከፍ አደረገው። ሐማም ልክ የሥልጣን ቦታውን ሲይዝ ሰይጣን ያነሳሳውንና የተላከበትን ተልዕኮ ለመፈጸም በመላው የንጉሡ ግዛት የሚገኙ አይሁዳውያንን በሙሉ ለማስጨረስ አዋጅ አስወጣ። ሁሉን ነገር ጨርሶ ፉር የሚባል ዕጣ እንዲወጣ ጣሉ። ዕጣውም አዳር በተባለው በአስራ ሁለተኛው ወር ላይ ወደቀ።

ይህ ወር እስራኤላውያን በሙሉ የሚታረዱበት የቀጠሮ ቀን ነበር። ሐማ በዚያን ቀን ላይ የንጉሡ አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የአስቴርን አጎት መርዶክዮስን የሚሰቅልበት ግንድ አዘጋጅቶ ተዝናንቶ ሲጠባበቅ ሳለ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሴራ እንዳከሸፈ ይህ ታሪክ የእርሱ ታሪክ ነውና አስቴርንም ሆነ አጎቷን

እንዲሁም ወገናቸውን የአይሁድ ህዝብን ሁሉ ያድን ዘንድ ጣልቃ ገባ። ቀላል ጊዜ አልነበረም። እግዚአብሔር ተናግሯችሁ ከተነሳችሁ የሚነሳው ውጊያና ሰልፍ ብርቱ ነው። ራዕይ ብላችሁ ተነስታችሁ እንዴት ይቀላል?

መርዶክዮስ አስቴር ወደ ንጉሡ ገብታ ጉዳዩን ታስረዳ ዘንድ ተማጠናት። የእርሷ ጭንቀት የነበረው ደግሞ ተራዬ ካልደረሰ በቀር ወደ ንጉሡ ዘንድ መግባት አልችልም የሚል ነበር። እርሱም እንዲህ የሚል መልዕክት ላከባት። ከልጅነት ጀምረን እንደ ቤተሰብ እግዚአብሔርን አምልከናል። ጸመናል፣ ጸልየናል። እርስ በርሳችን እየተደጋገፍንም ዛሬ ላይ ደርሰናል። እንደ ቤተሰብ እንደ አገር ራዕይ ያለን ሕዝብ ነን። እግዚአብሔር ዛሬ አንቺን እዚህ ከፍታ ላይ ያስቀመጠሽ ለዚህ ቀን እንደሆነስ? ግና አንድ ነገር ልንገርሽ ዛሬ ለነፍስሽ ሳስተሽ እምቢ ብትይ ለአይሁድ ሕዝብ መዳን ከሌላ ስፍራ ይሆናል። አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ አላት። አስቴርም ይህን ስትሰማ ምንም እንኳን የንጉሡን ሕግ መተላለፍ የሚያስከፍላትን መስዋዕትነት ስታስበው ቢከብዳትም "ብሞትም ልሙት" ብላ ያለ ንጉሡ ፈቃድ ገባች።

ሰው እግዚአብሔርን ካመለከ፣ በቤቱ ውስጥ ያለውን ህብረት እና አንድነት ጠብቆ ጠንካራ ቤተሰብ ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘነውን ራዕይ፣ ሃሳብ እና ምክር ለመፈጸም እንዲህ ዓይነት ጭካኔ ካለው፣ ምን የማይሆን ነገር አለ?

አስቴር ብሞትም ልሙት ብላ ቆርጣ ብትገባም እግዚአብሔር ግን ለደህንነት አደረገው። አርጤክስስ በትረ መንግስቱን ሳይዘረጋላት በፊት የነገሥታትን ልብ እንደ ውሃ ፈሳሾች ወደ ፈቀደበት ቦታ የሚያዞር እግዚአብሔር ከንጉሡ ቀድሞ የመንግሥቱን በትር

የዘረጋላት ነው የሚመስለኝ። የነገሥታቱ ንጉሥ እግዚአብሔር ከላይ በትሩን ስለዘረጋላትም፣ ምድራዊው ንጉሥ ሌላ ምርጫ አልነበረውምና እርሱም በትረ ሥልጣኑን ዘረጋላት።

ልባችሁ በእግዚአብሔር ይጽና፣ ዓይኖቻችሁ እግዚአብሔር ለሰጣችሁ ራዕይ ወደ እግዚአብሔር ይነሱ፣ እግዚአብሔር በቤታችሁ ይመለክ። እናንተ በቤታችሁ አንድ ልብ፣ አንድ ሃሳብ ስትሆኑ፣ እግዚአብሔር የረድኤት እጁን ይዘረጋል፣ ያንጊዜ በምድር ያለው ሁሉ ለእናንተ ይዘረጋል።

ያ በግዞት ያለ ህዝብ ለሞቱ በተቀጠረበት የእልቂት ቀን እግዚአብሔር የደስታ ስጦታን የሚለዋወጥበት ቀን አደረገለት። አይሁዶች ስጦታ የመለዋወጥ በዓል ነበራቸው። ስጦታቸውን የሚለዋወጡበት ቀን ደግሞ ያ የሞት አዋጅ ሊፈጸምባቸው ያለው ቀን ነበረ። የልቅሷቸው ቀን በነበረው በዚህ ቀን ላይ እግዚአብሔር ይህን እርሱን የሚያመልክ፣ እርሱን የሚያዳምጥ፣ እርስ በርሱ የሚተባበርና ራዕይ ያለውን ቤተሰብ ተጠቅሞ በመቶ ሃያ ሰባት አገራት በሚኖሩ አይሁድ ላይ የታወጀውን የሞት አዋጅ ወደ ሕይወት በመቀየር ለመዳን ምክንያት አደረገው። ድነው ሌላውን ወገናቸውን የሚያድኑ ሰዎች አደረጋቸው።

ከዚህ ቤተሰብ የምንማረው ትምህርት እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያሳየንን ራዕይ ሁልጊዜ ማሰብ፣ ማሰላሰል እንደሚገባን ነው። ይህን ማድረግ እንችል ዘንድ የሚረዳን ደግሞ በወረቀት ላይ ጽፎ መያዙን ብንለማመድ ጥሩ ነው። ሁላችንም ራዕይ አለን፣ ይሁንና ያንን ራዕይ በጽሁፍ ጽፎ የመያዙ ልማድ ግን የለንም።

ትንቢተ ዕንባቆም ምዕራፍ ሁለት፣ ቁጥር ሁለት ላይ እንዲህ ይላል። *"በመጠበቂያ ላይ እቆማለሁ፣ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ*

እቆያለሁ፤ ምን እንደሚለኝ፣ ለክርክሩም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰ፤ በቀላሉ እንዲነበብ፣ ራዕዩን ጻፈው፤ በሰሌዳም ላይ ቅረጸው። ራዕዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና፤ ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤ እርሱም አይዋሸም፤ የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤ በእርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም"። (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ምን ማድረግ ነው የምትፈልገው? ያን ማድረግ የምትፈልገውስ ነገር እንዴት ነው ማድረግ የምትፈልገው? ያን ማድረግ የምትፈልገውን ነገርስ ለምንድር ነው የምታደርገው? ለእነዚህ ሦስት ጥያቄዎች መልስ መስጠት አለብን።

እነዚህን ሦስት ነገሮችን በማቀናጀት መጻፍ ይገባኛል። ቤተሰቡም ሁሉ እንዲሁ ሊያውቀው ይገባል። እኔ፣ ባለቤቴና ልጆቼ እንደ እግዚአብሔር ቃል እና ሃሳብ የተስማማንበት ሁላችንም የተመካከርንበት ምክር ሊኖረን ይገባል። የእግዚአብሔር ቃል ልጆች በወታደር እጅ እንዳሉ ፍላጻዎች ናቸው ብሎ የሚናገረው ዓላማ ያላቸው ልጆች፣ ዓላማ ያለው ቤተሰብ ማለቱ ነው። ቤተሰቡ በማዕድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠ እየበላና እየጠጣ እየተጫወትን የእግዚአብሔርን ቃል ከፍቶ ከዛሬ አስር ዓመት በኋላ በህይወትሽ እንዲሆንልሽ የምትፈልጊው ነገር ምንድነው? ይህ ነገር ይሆንልሽም ዘንድ እንዴት ነው የእግዚአብሔርን ሃሳብ ማገልገል የምንችለው? ብሎ መመካከር ያስፈልጋል።

ሁለተኛው እግዚአብሔር የሚሰጠንን ዕድል ፈጽሞ አናሳልፈው። አንድ ከተማ ውስጥ አስር እና አስራ አምስት ዓመት ኖረን ምንም ዕድል አላገኘሁም ብዬ ለማለት ይቸግረኛል። ስለ አንተ፣ ስለ እንቺ የሚያስበው መልካም መልካሙን ነው። ስለ አንተ

የሚያስበው "ምን አድርጌ ወደ ሃሳቤ ላስገባው?" "ወደ ጠራሁት ጥሪ እንዴት አድርጌ ላስገባው?" ብሎ ነው። እግዚአብሔር ለአንተ ህይወት የሚያስበው መልካሙን ነው። በሳትን፣ በተሸነፍን ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር በምክሩ፣ በሃሳቡ እና በእቅዱ መልካም ነው። ወጣቶችን፣ ጎልማሶችን የምመክራችሁ ምክር አንድ ነገር ከጌታ ጋር ተስማምታችሁ አንድ መሆን የምትፈልጉትን ነገር በእግዚአብሔር ፊት ጸልያችሁ ያለውን በጌታ በአጠገባችሁ የሚያልፈውን ዕድል ተከታተሉት።

ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ የወጣትነት ልብ ዛሬ ይህንን፣ ነገ ያንን፣ ከነገ ወዲያ ደግሞ ሌላውን ይሞክራል። በመካከል ግራ መጋባት ውስጥ ነው የሚገቡት። ነገር ግን እግዚአብሔር ዕድል ይሰጣል። አንባቢ ሆይ እግዚአብሔር ይህን ዕድል እንዲሰጠን እንጸልይ። ይህን ዕድል እንደሚሰጠንም እንመን። እግዚአብሔር ያንን ዕድል አጠገባችሁ ሲያመጣው ግን ልትይዙት ይገባል። ይሁንና ይህ ዕድል የሚያመጣው አደጋ እንዳለው አንርሳ። አስቴር ወደ ንግሥና ለመውጣት ቁንጅናዋ ውድድር ውስጥ ስትገባ ጓዳ እኩ መደበቅ ትችል ነበር። በደርግ ዘመነ መንግስት ለብሔራዊ ውትድርና ሲመርጡን ከእነሱ ለማምለጥ ገብተን ያልተደበቅንበት ጉድጓድ አልነበረም። እርሷም እንደዚያ አምልጣ መደበቅ መቻል ነበረባት። ምክንያቱም የዚያ አገር ዜጋ አይደለችም፣ ስደተኛ ነች፣ ከአይሁድ ወገን ነች፣ የሙት ልጅ፣ ብዙ የግል የሚባል ታሪክ የሌላት ሴት ናት። ሆኖም የሚመጣባትን ለመቀበል ኃላፊነትን ወሰደች። ልቡ በእግዚአብሔር ነገር የተሞላ ሰው የማይቻል ነገር ቢሆን እንኳን እግዚአብሔርን አይቶ እግዚአብሔር አዋቂ ነው፣ ይችላል፣ ያደርገዋል፣ ጌታ ለዚህ ፈልጎኝ ከሆነ ምን ችግር አለ? ይህንን ኃላፊነት እኔ እወስዳለሁ ይላል። እንዲህ ዓይነቱን የሞት ወይም

የሕይወት ርምጃ የሚወስድ በእምነት የሚራመድ ሰው ነው። ከእግዚአብሔር ጋር የምንሰራው ሥራ በሙሉ እኮ እምነትን የሚጠይቅ ነው።

ለምሳሌ እንደ ስልክ፣ መብራት፣ ውሃ እና የቤት ኪራይ የመሳሰሉ አንዳንድ አገልግሎቶችን ለማግኘት ገና ያልተጠቀምነውን ነው በቅድሚያ የምንከፍለው። ልክ እንደዚሁ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በገባው ውል መሠረት ወደፊት ነው የሚታዘዘኝ ብሎ አሁን የሚባርክ አምላክ አይደለም። እርሱ የሚፈልገው ልክ አብርሃምን እንዳለው አገርህን፣ ወገንህንና የአባትህን ቤት ትተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ። ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፤ ደግሞም እባርክሃለሁ ነበር ያለው። ስለዚህ አብርሃም በኋላ ላይ ለመባረክ ማድረግ የነበረበት የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ መታዘዝ ነበር።

ጌታ ከሃያ አምስት ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ አብርሃም ተመልሶ መጥቶ የዛሬ ዓመት ሚስትህ ወንድ ልጅ ትወልዳለች አለው። የእግዚአብሔር ነገር እንዲህ ነው። እግዚአብሔር ራዕይ ከሰጠ አሁን የሚሆን ነገር የለም። አሁን የሚሆነው የአንተ በእምነት ተወራርደህ መግባት ነው። ያንጊዜ እግዚአብሔርን የምትሰማ ነፍስ በፍጹም አትከስርም።

እግዚአብሔር በለሰለሰ ድምጽ ወይም መከራ ውስጥ ሆነን ይናገረን ይሆናል። እግዚአብሔር ሲናገረን ደግሞ የነቃ አእምሮ ኑሮን ይህማ የጌታ ድምጽ ነው ብለን አፈፍ አድርገን እንቀበል ዘንድ የነቃ አዕምሮ ሊኖረን ይገባል።

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሊያድናቸው ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ ሙሴ እግዚአብሔር ነጻ አወጣቸው ዘንድ መጥቻለሁ

ብሏል ሲላቸው ከተጫነባቸው ከባድ ሥራ የተነሳ አልሰሙትም። ጌታ እኛንም ከእንዲህ ዓይነቱ አለመስማት ነጻ ያውጣን! የቀረን ጥቂት ዘመን ነው። በቀረን በዚህ ጥቂት ዘመን ውስጥ ጌታን አገልግሎ ለማለፍ እግዚአብሔር የነቃ አዕምሮ ያድርግልን፣ የሚያስተውል ልቦና ይስጠን። የቀረን ጥቂት ዘመን እንደሆነ አውቀን የነቃ ልቦና ኑሮን ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ ልንገባ ይገባል።

ሦስተኛውና የመጨረሻው ሃሳቤ ተግዳሮት የሚለው ነው። ተግዳሮት ሲገጥመህ አትሸሽ። እግዚአብሔር ስለተናገረን መከራ አያገኘንም፣ ሐዘን አይደርስብንም፣ መሰናክል ሲያልፍም አይነካንም ማለት አይደለም። የክርስትና መንገድ አልጋ በአልጋ አይደለም። እንዲያውም ጌታ ወደ ማዶ እንሻገር ካለ እርሱ ተናግሮኛል ቃልም ሰጥቶኛል ብለን ታንኳዋ ውስጥ ገብተን መቅዘፍ ስንጀምር እምነታችን የሚፈተሽበት ወጀብ እና ማዕበል ይመጣል። እውነት እስቲ አሁን ቃሌን በእምነት ይዞ ነው የወጣው? የሚል ጥያቄን የያዘ ነው የሚመስለው። እግዚአብሔር ለምን ይሆን እንዲህ የሚያደርገው? አንድ ልጄንስ ባርኮ፣ መርቆ ሸኝቶት የጠበቀው መስቀል አይደለ?

ዓለም እኮ ለጌታም አልተመቸችውም። ለእርሱ ካልተመቸው ደግሞ ለእኛ እንዴት ይመቸናል? እርሱን እነዚያ ከእጁ የበሉ፣ የጠጡ፣ ተዓምራትን እያደረገ የፈወሰላቸው፣ ከሞት ያስነሳቸው ብዙ የረዳቸው ሰዎች "ስቀለው! ስቀለው!" እያሉ ከሰቀሉት እኛንማ እንዴት? ወገኖቼ ሆይ! ጌታን ስትከተሉማ፤ እግዚአብሔር እንደ ቤተሰብ ለሰጣችሁ ነገር የማይመች በጣም ብዙ ተግዳሮት ይመጣል። ከዚያ በኋላ ግን በተለያየ መልኩ ሳንካ ይገጥመናል። ደንቃራው ይደነቀራል፣ ተግዳሮሪው በመንገዳችን ላይ ይቆማል። በወራት፣ በሳምንታት እንዲያውም አንዳንድ ጊዜማ በቀናትም እጃችን ላይ

ያለውን ገንዘብ ጥርግርግ አድርጎ የሚወስድ እክል ይገጥመናል። ከየትኛውም አቅጣጫ ተስፋ የሚያስቆርጥ ክስተት ይመጣል።

ዛሬ ግን በእግዚአብሔር ቃል ለልባችሁ ልናገር ተግዳሮትን አትሸሹት። ራዕዩን የሰጣችሁ እግዚአብሔር እናንተንም ሆነ ራዕዩን ይጠብቃል፣ ይፈጽመዋልም። መርዶክዮስ በሐማ ፊት ዝቅ እንዳይል ከስፍራው እንዳይነሳ የጠበቀው እግዚአብሔር ይህ ብቻም አይደለም ለአንተ የተደገሰውን የሞት ድግስ ለእርሱ አደርገዋለሁ ማለት የሚችል፤ አምላክ በሰማይ አለ።

እግዚአብሔር ኤርምያስን *"በማህፀን ሳልሠራህ አወቅሁህ፤ ከመወለድህም በፊት ለየሁህ፤ ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን ሾምሁህ"* (ትንቢተ ኤርምያስ 1:4) ብሎ ለአገልግሎት ሲጠራው፤ ኤርምያስ ፍርሃት ስለያዘው *"ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እንዴት እንደምናገር አላውቅም፤ ገና ሕጻን ልጅ ነኝና አለው።* እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለው። *"ገና ሕጻን ልጅ ነኝ አትበል፤ ወደምልክህ ሁሉ ሂደህ፣ ያዘዝሁን ሁሉ ትናገራለህ፤ እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራቸው፤ . . .አንተ ግን ወገብህንታጠቅ፣ ተነሥተህም ያዘዝሁህን ሁሉ ንገራቸው፤ አትፍራቸውም፤ አለዚያ በፊታቸው አሰፈራሃለሁ። እነሆ ዛሬ በመላዪቱ ምድር ላይ አስነሣሃለሁ ይኸውም የይሁዳን ነገሥታት፤ አለቆቿን፣ ካህናቷንና የምድሪቱን ሕዝብ ሁሉ መቋቋም እንድትችል የተመሸገ ከተማ፣ የብረት ምሰሶና የናስ ቅጥር አድርጌሃለሁ። ይዋጉሃል፤ ዳሩ ግን አድንህ ዘንድ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አያሸንፉህም"* አለው (ኤርምያስ 1:16-19 አዲሱ መደበኛ ትርጉም)።

እግዚአብሔርን ስለተከተልን እርሱን ስላገለገልንና በመንገዱ ስለምንሄድ እግዚአብሔር ራዕይ ስለሰጠን ይዋጉናል። ሆኖም ግን እርሱ ከእኛ ጋር ስለሆነ አያሸንፉንምና ተነስተን የእምነት ርምጃ እንራመድ እንጂ ፈርተን አንቀመጥ። ፈርተን የትም አንደርስም። እግዚአብሔር ለልባችን፣ ለመንፈሳችን፣ ለውስጣችን ከተናገረንና ይህንንም በቃሉ ካረጋገጥን እግዚአብሔርን መታዘዝ ይገባናል። ፈርተን ከተጣራንበት ጥሪ የትም መሸሽ አንችልም፤ ይልቁንስ የሚሻለው የመጣልንን የእግዚአብሔርን ቃል ትዕዛዝ ይዘን መውጣትና መራመድ ነው።

እግዚአብሔር ይዋጉሃል እንጂ አይዋጉህም አላለም። ቁርጡን ነው የሚናገረው። እውነትን ነው የሚነግረን። ይዋጉሃል ሆኖም እኔ ከአንተ ጋር ስለሆንኩ ግን አያሸንፉህም። አስቴር "ብሞትም ልሙት" ብላ በእምነት በመራመዷ እግዚአብሔር ታሪክን ለወጠ። ወገኖች ሆይ! አንድ እውነት ልንገራችሁ። ብዙ ነገር ልንሰራ የምንችልበት ረጅም ዕድሜ ያለን እየመሰለን እንራወጣለን። አስተዋይና ብልህ ሰው ግን ጥቂት ጊዜ እንደ ቀረው አውቆ የሚኖር ሰው ነው። ሩጫዬን ልጨርስ ጥቂት ጊዜ ነው የቀረኝ ብሎ የሚል ሰው ተዘጋጅቶ ይኖራል። ቶሎ ቶሎ እየሰራ ይኖራል። ከአምላኩ ጋር ልቡን አጠጋግቶ ይሮጣል። ረጅም ዘመን ያለን እየመሰለን እንዘናጋ።

ዛሬ ልጆቻችሁንና የትዳር ጓደኞቻችሁን በእግዚአብሔር ፊት ይዛችሁ ጌታን ምን እንድናደርግ ነው የምትሻው? ብላችሁ ጠይቁት። ያንን የተስማማችሁበትን ነገር በእግዚአብሔር ፊት በጸሎት ይዛችሁ ቅረቡ። በእግዚአብሔር ፊት ርምጃ ውሰዱ። እግዚአብሔር ይረዳችኋል። ዛሬ በእግዚአብሔር ቃል የምንግራችሁ ያ ሰው ኢያሪኮን ሰባት ጊዜ ዞራችሁ ስትጨርሱ ጩሁ ባላቸው ጊዜ

ልክ ሲጮሁ ግንቡ እንደ ወደቀ፣ ቅጥሩ እንደፈረሰና እነሱም ድል እንዳደረጉ እኛም እንዲሁ በመጨረሻው ዘመን ላይ ያለን ነው የሚመስለኝና ያንን ጩኸት እንጩህ። እሺ ብትሉ በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጣችሁ ኑሯችሁን፣ ስለ ህይወታችሁ አስባችሁ ጌታ ሆይ ህይወቴ፣ ቤቴ፣ ኑሮዬ የአንተ ነውና ምን እንድሆን ነው የምትሻው? ብለን ጥቂት ዕድሜ እንደ ቀረው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ልብ ለልብ ብትገናኙ ቅጥሩ ይወድቅላችኋል። እግዚአብሔር ስለ እናንተ እንደተናገረው ተሻግራችሁ ከተማይቱን ትወርሳላችሁ።

ምዕራፍ 8

የቤተሰብ አባላት ግንኙነት እና የባል ድርሻ

ምዕራፍ ስምንት

የቤተሰብ አባላት ግንኙነት እና የባል ድርሻ

በዚህ ምዕራፍ ላይ የምንመለከተው በቤተሰብ ውስጥ ስላለው የቤተሰቡ አባላት ተግባርና የኃላፊነት ክፍፍል ነው። በቤተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ያወቁ የቤተሰቡ አባላት ፍሬያማ ይሆናሉ። የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ድርሻ ተሰብስቦ ሲደመር ነው አንድ ሙሉ ውጤት የሚመጣው። አለበለዚያ ጎደሎ ነው የሚሆነው። በዚህ ምዕራፍ ይህንን ነው የምናየው።

"እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል። የዕለት ጉርስ ለማግኘት በመጣር ማልዳችሁ መነሣታችሁ፤ አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤ እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና። እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፤ የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው። በወጣትነት የተገኙ ወንዶች ልጆች፤ በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጻች ናቸው። ኮሮጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ፤ የተባረከ ሰው ነው፤ ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟገቱበት ጊዜ አይዋረዱም" *(መዝሙረ ዳዊት 127፡1-5)*።

"እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፤ በመንገዱም የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው። የድካምህን ፍሬ ትበላለህ፤ ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም። ሚስትህ በቤትህ፣ እንደሚያፈራ ወይን ናት፤ ወንዶች ልጆችህ በማእድህ ዙሪያ፣ እንደ ወይራ ተክል ናቸው። እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፤ እንዲህ ይባረካል። እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ፤ የልጅ ልጅም ለማየት ያብቃህ። በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ" *(መዝሙረ ዳዊት 128፡1-6)* ይላል። አሜን!

ከላይ ባነበብነው የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ የጠንካራ ቤተሰብ ባርኮት ከጌታ ዘንድ እንደሆነ ነው የሚናገረው። ይህ ደግሞ መዝሙር 127፡1 እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኛ በከንቱ ይደክማል፤ እንደሚለው አንድ መኖሪያ ቤት ከመነሻው አንስቶ ተሰርቶ እስከሚጠናቀቅበት ድረስ ያለው ባርኮት በሙሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኝ በረከት እንደሆነ ነው የሚናገረው። የልጆችን ነገር በማንሳትም "የድካምህን ፍሬ ትበላለህ፤ ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም። ሚስትህ በቤትህ፣ እንደሚያፈራ ወይን ናት፤ ወንዶች ልጆችህ በማእድህ ዙሪያ፣ እንደ ወይራ ተክል ናቸው። እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፤ እንዲህ ይባረካል። እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ፤ የልጅ ልጅም ለማየት ያብቃህ" እያለ ስለ ተባረከ ፍሬያማ ቤተሰብ ይናገራል።

እነዚህ ሁሉ መልካም የሆኑ በረከቶች ናቸው። ነገር ግን የሚገኙበትን መንገድ ማወቅ ይኖርብናል። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ "እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው፤ እንዲህ ይባረካል፣ . . .ምስጉን ነው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በመንገዱም የሚሄድ ሰው የተባረከ ነው" ይላል።

እንዲህ የተባረከ ጠንካራ ቤተሰብ የተመሰረተው በውጫዊ ነገሩ አይደለም። ቤተሰቡ እግዚአብሔር የሚመለክበት፣ ህብረቱና አንድነቱ የተጠበቀ፣ የጋራ ራዕይና ዓላማ ያለውና እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል የሚጠበቅበትን የሥራ ድርሻውን ጠብቆ ከእግዚአብሔር ትልቅ ራዕይ ጋር ተስማምቶ የሚጓዝ ከሆነ እነዚህ ሁሉ በረከቶች ያገኙታል። ሁላችንም ቁጥራችን ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ባሉበት ምንም ዓይነት ሥራ ለማከናወን ግንኙነታችን ግልጽ መሆን አለበት። ለምሳሌ ወደ ሚኒባስ ታክሲ ወይንም አውቶብስ ውስጥ የምንገባ ተሳፋሪዎች ግንኙነታችን ግልጽ ነው። ምንድነው ግልጽነቱ? አውቶብሱ ላይ እንሳፈራለን፤ ከዚያም ለቲኬት ቆራጩ ገንዘብ አውጥተን እንከፍላለን፤ የምንወርድበት ፌርማታ እስክንደርስ ድረስ ክፍት ወንበር ካለ እንቀመጣለን። ይሁን እንጂ ከአንድ ሰው ቦታ በላይ የመያዝ መብት ግን የለንም። ልክ እንደ እነዚህ ያሉ በግልጽ የተቀመጡ የምናውቃቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ።

ልክ እንደዚሁ ነው። ከአንድ በላይ ሰው በሚኖርበት ቦታ ትርምስን ለማስቀረት፣ ጤናማ ግንኙነትና መደጋገፍ እንዲኖር የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት በግልጽ መቀመጥ አለበት። ለዚህ እኮ ነው በየትኛውም መስሪያ ቤት ውስጥ የተዋረድ መዋቅርና ዝርዝር የሥራ ድርሻ፣ ማን ለማን ተጠሪ እንደሆነና ከእርሱ ወይም ከእርሷ ምን እንደሚጠበቅ፣ ወዘተ. በግልጽ የሚሰፍረው። ይሄ ግሮትንና ብክነትን ያስቀራል። ጠንካራ ጎብረትና የሰመረ ተግባቦት እንዲኖር ያስችላል።

የእግዚአብሔር ቃል ባል እና ሚስት ብሎ ሲጠቅስ አብሮ የሚያነሳው ነገር አለ። ሁለቱ እርስ በርስ በቃል ኪዳን የተሳሰሩና ሁልጊዜ የሚታይ የቃል ኪዳን ግንኙነት ያላቸው፤ በመካከላቸው

ቀዳሚ እና ተከታይ መሪ ባልንጀራነትና የአብሮ ሠራተኝነት ያለበት መሆኑን ሁልጊዜ ይናገራል። እርስ በእርሳቸው አንዱ ለሌላው ተገዢ እንደሆኑ ነው የሚናገረው። ዝም ብለው አብረው የሚኖሩ ሳይሆኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል በቃል ኪዳን የተጣመሩ፣ የአንድ ሥጋ ውህደት ያላቸው፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ አንድነትና የጋራ ዓላማ ያላቸው የትዳር ባልንጀራሞች ናቸው።

የሰውነታችንን ብልቶች ነጣጥለን አንድ ቅርጫት ውስጥ ብናስቀምጣቸው የብልት ስብስብ እንጂ ሙሉ የሆነ ሰውን ሊያስገኝልን አይችልም። እንደ ቅርጫ ሥጋ ዝም ብሎ የተቀመጠ ነው የሚሆነው።

እግዚአብሔር ሲፈጥረን ብልቶች እርስ በርስ ተያይዘው ጎያዋን ብልቶች ለአንድ ዓላማ የተፈጠሩ አድርጎ ነው የደነገገው። 1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ይህንን እውነት ነው የሚነግረን። እያንዳንዱ ብልት በራሱ ነጻ፣ ለተለየ ዓላማ የተፈጠረ ሆኖ ነገር ግን ደግሞ የራሱን ተግባር ለመፈጸም የሌላው ብልት ጥገኛ ሆኖ ተፈጥሯል። እያንዳንዱ ብልት ድርሻ አለው። የሚናቅ ተግባር የለም። አንዱ ብልት በሌላው ሥራ ተጠቃሚ በመሆን አብረው ያድጋሉ፣ ይለመልማሉ።

ሳይንስ እየቆየ እየመረመረ ይደርስበት እንደሆነ ነው እንጂ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ብልት ሥራዬ ብሎ በዓላማ በዕቅድ ነው በአካሉ ውስጥ የገጣጠማቸው። ይህ ከሰውነት ክፍላችን የምንረዳው ምስጢር ለቤተሰብም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ሲፈጥር በቃል ኪዳን ባልንጀራሞች ሆነው ቤተሰብ የሚባልን ተቋም ሲመሠርት ሁለቱም በቤተሰቡ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው አድርጎ ነው የሰራቸው።

ቀጥለን የምንመለከተው ይህን በቤተሰብ አባላት መካከል ያለውን ድርሻና ኃላፊነት ይሆናል። ባል፣ ሚስትና ልጆች በቤተሰብ ውስጥ ያላቸው ተግባርና ኃላፊነት ምንድነው? በመጀመሪያ የምናየው የባሎችን ድርሻ ይሆናል። ለመሆኑ ባል በቤተሰብ ውስጥ ያለው ድርሻ ምንድነው? የመጀመሪያ ድርሻው ሚስቱን መውደድ ነው። አፍቃሪ ባል መሆን ነው። የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን ምዕራፍ 5፡25-33 ላይ የባል የመጀመሪያው ትልቁ ሥራው ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በወደደበት ፍቅር ሚስቱን መውደድ እንደሆነ ነው የሚናገረው።

መውደድ ብዙ የተለያዩ አተገባበር እና ትርጉሞች አሉት። ሆኖም በዛሬው ዘመን የተዛባ እና የተበላሸ ቃል ሆኗል። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ያለውን ፍቅሩን የገለጠው ነፍሱን ለወዳጆቹ እስከመስጠት በደረሰ የከበረ ፍቅር ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ለባል ሚስቱን እንዲወዳት ትዕዛዝ ሲሰጠው የሚወዳት እኮ አጋፔ በሚለው የፍቅር ዓይነት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 5 ላይ ሲናገር ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በወደደበት ፍቅር ሚስቶቻችሁን ውደዱ ነው ያለው። ባል ሚስቱን የሚወድበት ፍቅር ከሰማይ ፍቅር ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። ለመሆኑ ቤተ ክርስቲያን የምትወደድ ዓይነት ናት ወይ? ቤተ ክርስቲያን ስንል እኮ ከአዳም ነው የምንጀምረው። ጥንት አባታችን አዳም እና እናታችን ሔዋን አንዲት ሕግ ብቻ በነበራቸው ዘመን ያውም በገነት ውስጥ እንኳን ሕግን መጠበቅ አልቻሉም። እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ እስቲ የሰው ልጅ የት ነው እግዚአብሔርን እንደሚወደው ዓይነት የራሱ የሆነ ጥሩነት ወይም ብቃትና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነገር ይዞ

የታየው? ሰው በራሱ አንዳች የሚወደድ ነገር የለውም። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደዳት የሚወደድ ነገር በሌላት ጊዜ ነው።

አያችሁ የዚህ ዓለም ሰው ሰውን እወዳለሁ የሚለው በስስታም ፍቅር ነው። ስጠኝ ብቻ የሚል እንጂ ስለ ሌላው ወገን ጥቅም እና ደስታ ግድ አይለውም። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደደበት ፍቅር ግን የራሱን መስጠት ብቻም ሳይሆን ራሱን አሳልፎ የሰጠበትም ፍቅር ነው። ስለዚህ ባል የመውደድ ድርሻውን የሚወጣበት ፍቅር የክርስቶስ ዓይነት ምላሽን የማይጠብቅ ፍቅር ነው። ጥሩ ነገር ካደረግችልኝ ጥሩ ጥሩ ነገር ከሰጠችኝ የምትወደድ ዓይነት ከሆነች ብሎ አይጀምርም።

እግዚአብሔር እኛን ሲወደን የጀመረው በምንድነው? በዮሐንስ 3፡16 ላይ ነግሮናል። አንዱ ወንድማችን የጌታ ፍቅር በጣም ከአዕምሮው በላይ ሆኖበት ሦስት ቀን ጸም ጸሎት ገባና "ጌታ ሆይ እኔን ለምን ወደድከኝ?" እያለ ሲጸልይ ቆየ። ጌታም በጾም ጸሎቱ ማብቂያ ቀን ላይ በዮሐንስ 3፡16 ላይ ያለውን "እንዲሁ" የሚለውን ቃል ሰጠው። እግዚአብሔር የወደደን እንዲሁ ነው። ልክ እንደዚሁ እኛም የክርስቶስን ዓይነት ፍቅር በምናሳይበት ጊዜ እንዲሁ ወደሚለው ነገር ነው የምንሄደው። ኤፌሶን ምዕራፍ 5፡28 ላይ እንዲህ ይላል። *"ባሎችም እንደዚሁ ሚስቶቻቸውን እንደ ገዛ ሥጋቸው መውደድ ይገባቸዋል። ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል። የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ማንም የለም፤ ይመግበዋል፤ ይንከባከበዋል፤ ክርስቶስም ለቤተ ክርስቲያን ያደረገው ልክ እንደዚሁ ነው፤ እኛ የክርስቶስ አካል ብልቶች ነንና"*። (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ይሁንና ሚስቶቻችንን እንዲሁ በዜሮ እንደማንወዳቸው ግን ልቦናችን ያውቀዋል።

አንዳንድ ሰዎች "እኔ እኮ ሚስቴን ከራሴ አስበልጬ ነው የምወዳት" ሲሉ ይደመጣሉ። ይሁንና እግዚአብሔር ግን እንደዚያ እንድናደርግ አልጠየቀንም። ከራስህ በላይ ማንንም ሰው ውደድ አልተባልኩም። አሁን ትግሉ እና ጦርነቱ ያለው እንደ ራሴ አድርጌ መውደዱ ላይ ነው። አስቀድመን እንዳልነው ቃለ እግዚአብሔር ባል ሚስቱን መውደድ ማፍቀር አለበት እያለ ሚስት ግን የምትወደድ ወይም የምትፈቀር ዓይነት ሰው ሆና ባትገኝስ?

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚሁ በኤፌሶን ምዕራፍ 5:28 ላይ "ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ባልም እንዲሁ ሚስቱን እንደ ገዛ ሥጋው ይውደድ" *ነው የሚለው*። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች በጥምረት ተገልጸዋል። አንዱ "ይውደዳት" የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "እንደ ገዛ ስጋው" የሚለው ነው። ይሄ ምን ማለት ነው?

ተመልከቱ በራሳችሁ ተበሳጭታችሁ አታውቁምን? አንዲት ልጅ "ጌታ ሆይ ካዚህ የበሰበሰ ሥጋ አውጣኝ" እያለች እንደ ጸለየችው ጸልያችሁስ አታውቁምን? ስጋችን በራሱ ትልቁ ፈተናችን ነው። አውጥተን ልንጥለው የማንችለው አስቸጋሪ ነገር ነው። ጧት ላይ ቁርሱን በደንብ አብልታችሁት፤ ምሳ ሰዓት ሲደርስ አይ ቀድም በደንብ በልቻለሁ ብሎ አይታገስም። ሰዓቱን ጠብቆ ነው አምጣ የሚለን። ምሳውን ጥርግ አድርጎ በልቶ ደግሞ እራቴን አብላኝ ይለናል። ምነው ምሳህን በደንብ አብልቼህ የለም ወይ? አንለውም የጠየቀንን እንሰጠዋለን። አመሻሽ ላይ ደግሞ የመኝታ ሰዓት ሲደርስ "የማጠናው ጥናት አለብኝና አጥንቼ ልጨርስ ወይስ ትተኛለህ ስንለው"፤ "የለም ደክሞኛልና ልተኛበት" ይለናል። ትግል ነው።

ይሁንና ስጋችን ስለሆነ አንዴ ተማሪ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሠራተኛ እያደረግነው እንታገሰዋለን። እሁድ ቀን ደግሞ ሽማዝ

አልብሰነው፣ ክራባት አስረንለት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንወስደዋለን። ይህን የምናደርገው ሥጋችን ስለሆነ ስለማንጠላው እኮ ነው! በብዙ እንታገሰዋለን፣ እንንከባከበዋለን። ጳውሎስ በመልዕክቱ እያለን ያለው ለሚስትህም እንዲሁ አድርግላት ነው። ሕግ ሁሉ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ በሚለው ተጠቃሏል (ሮሜ 13:9)። አንዳንድ ሰዎች እንደ ራስ አድርጎ መውደድ ድሮ ቀረ ይላሉ። አልቀረም፤ አሁንም አለ!

እኛ በጌታ አዲስ ፍጥረት ነን፤ ያ ዳግም ሳንወለድ፣ የክርስቶስ ብርሃን ሳያበራልን፣ የጌታ መንፈስ በላያችን ላይ ሳይፈስና ሳንታተም፣ የልጁን መንፈስ ሳንቀበል በፊት የነበረው የቀድሞው አሮጌው ህይወታችን ቀርቷል። አሁን የምንነጋገረውም በእግዚአብሔር ቃል በታደሰው አዕምሯችን ማለትም በአዲሱ ማንነታችን ስላለንበት ሕይወት ነው። ያ የድሮው አሮጌው ማንነታችንማ እኮ አቅም የለውም ሙት ነው። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ነገር ግን አሁን በክርስቶስ ሕያው ከሆንኩ፣ አዲስ መንፈስ፣ አዲስ ልብ፣ አዲስ ሰውነት ካገኘሁ የባልነት ድርሻዬ የሆነውን ሚስቴን እንደ ራሴ አድርጌ መውደድ እችላለሁ።

ሁለተኛው የመሪነት ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በፈጠረው ጊዜ ሥነ ሥርዓት እንዲኖረው አደርጎ ነው የፈጠረው። ይህ ሥነ ሥርዓት እንዲኖር ደግሞ እግዚአብሔር የገለጠበት መንገድ አለ። የመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ቀድሞ የተፈጠረው አዳም ነው። የፍጥረት ቅደም ተከተል የእግዚአብሔርን ሃሳብ ይነግረናል። መጽሐፍ "እግዚአብሔር አምላክም አለ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት" እንደሚል እግዚአብሔር ሰውን

ሲፈጥር ቀድሞ የተፈጠረው አዳም ነው።

አዳም ለከብቶች፣ ለእንስሳቱ ሁሉ ስም ካወጣላቸው በኋላ እግዚአብሔር ብቻውን እንደሆነ አየና ራራለት። ያንጊዜ ረዳት እንድትሆነው ሴትን ፈጠረ። እግዚአብሔር "የምትረዳውን ረዳት እንፍጠርለት" ብሎ ሴትን መፍጠሩ የእግዚአብሔርን የቅደም ተከተል ሥርዓት ነው የሚያሳየን። ዛሬ በየቤቱ፣ በየቤተሰቡ፣ በብዙ ትዳር ውስጥ ያፈጠጠው ችግር የመሪነት መጥፋት ነው። በቤት ውስጥ ያለው አመራር ክፍተት ተፈጥሮበት የቤተሰቡ መሪ ማን እንደሆነ ተለይቶ ባልታወቀበት ሁኔታ ቤት እንዴት ጸንቶ መቆም ይችላል?

ዛሬ በየቤቱ በ1966 ዓ.ም ላይ ተከስቶ የነበረውን የአገራችንን አብዮት የሚመስል ሁኔታ ይታያል። ደርግ ከህዝባዊው አመጽ በኋላ ወደ ስልጣን የወጣው አስቀድሞ አስቦበት እና ተዘጋጅቶበት አልነበረም። ሥልጣን ባለቤት አጥታ "የመሪ ያለህ! የባለቤት ያለህ!" እያለች ተማጸን ባነበረበት ወቅት የወታደራዊው ክፍል ባልደረቦች አገር የመምራት በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ ሜዳ ላይ ያገኙዋትን ሥልጣን ድንገት ለቀም አደረጓት። ከዚያ በኋላ የሆነውን ታሪክ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ልክ እንደዚሁ ስልጣን ዛሬም በአንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ ባለቤቷን አጥታለች። ባልም ሆነ ሚስት ባሻቸው ጊዜ በቁጥጥራቸው ስር እያዋሉ ይጠቀሙባታል። የልባቸውንም ፍላጎት ይፈጽሙባታል።

ልጆች አባት የከለከላቸውን በእናታቸው ማስፈቀድ፣ እናት የለም አይሆንም ብላ የወሰነችውን ውሳኔ በአባት ማስፈረስ የተመለደ ሆኗል። በቤተሰቡ ውስጥ የሚደመጥ ሃይ ባይ መሪ የለም። ይሄ በፍጹም መለወጥና እግዚአብሔር በቤተሰብ ውስጥ ይኖር ዘንድ የደነገገው ስርዓት መስፈን አለበት።

እግዚአብሔር ግን በ1 ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11፡7 ላይ እንዲህ ሲል ሥርዓትን ደንግጓል። *"ወንድ ራሱን መከናነብ የለበትም፤ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ነውና፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት፤ ምክንያቱም ሴት ከወንድ ተገኘች እንጂ ወንድ ከሴት አልተገኘም። ደግሞም ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ለሴት አልተፈጠረም። ነገር ግን ይህን እንድታውቁ እወዳለሁ፤ የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ ነው፤ የሴትም ራስ ወንድ ነው፤ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር ነው"* ብሎ ይናገራል።

አንዳንድ ሰዎች ሲቀልዱ ወንድ ራስ ቢሆንም ሴት ግን አንገት ናትና ራስን ወደፈለገው እቅጣጫ የምታዞረው አንገት ናት። ከዚህ የተነሳ ራስ መሆን ምን ያደርጋል? አንገትን ሆኖ መገኘት ነው ይላሉ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ግን ይህንን አያረጋግጥልንም። እንዲህም ተብሎ አልተጻፈም። የተጻፈልንን በተገቢው መንገድ ከተረዳነው ያ በቂያችን ነው። ቃሉ "ወንድ የሴት ራስ ነው" ይላልና።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌ እና ክብር ነውና፤ ሴት ግን የወንድ ክብር ናት፤ ምክንያቱም ሴት ከወንድ ተገኘች እንጂ ወንድ ከሴት አልተገኘም። ደግሞም ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ለሴት አልተፈጠረም ብሎናል።

ጳውሎስ እያለን ያለው እግዚአብሔር አስቀድሞ በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥር የፈጠረው አዳምን ነው። ሴት ከዚያ በኋላ ነው የተፈጠረችው። ሴትን የፈጠራትም ለአዳም ረዳት እንድትሆነው ነው። በዚህም እግዚአብሔር ወንድን በፍጥረት ሁሉ ላይ ሾመው፣ የክብሩ ምሳሌም አደረገው። ሴትን ደግሞ ለወንድ ክብር እንድትሆን አደረጋት። ደግሞም ሴት የተፈጠረችው ለወንድ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል በቤተሰብ ውስጥ፤ በባል እና ሚስት፣ መካከል ቅደም ተከተል እንዳለ ያለ ምንም ማባበል ነው የነገረን። ጳውሎስ በዚሁ ክፍል ቁጥር አስራ ስድስት ላይ "እንግዲህ ማንም በዚህ ጉዳይ መከራከር ቢፈልግ፤ እኛም ሆን አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ የተለየ ልማድ የለንም" ብሎ ነው የሚዘጋው። ይህንን ማለቱ መከራከር የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ እኛ የክርክር ልማዱ ስለሌለን፤ በሚያውቁት መንገድ መሄድ ይችላሉ ማለቱ ነው።

ዘጉልቁ መጽሐፍ ምዕራፍ 30፡2-8 ለእግዚአብሔር ስእለት ስለ መሳል ሕግ ይናገራል። ሕጉ ሲናገር *"በአባቷ ቤት የምትኖር ሴት ልጅ ለእግዚአብሔር ስእለት ብትሳል ወይም አንድ ነገር ለማድረግ በመሐላ ራሷን ግዴታ ውስጥ ብታስገባ፣ አባቷም መሳቷን ወይም ራሷን ግዴታ ውስጥ ማስገባቷን ሰምቶ ምንም ነገር ሳይላት ቢቀር፣ ስእለቶቿ በሙሉ፣ ራሷንም ግዴታ ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች ሁሉ መፈጸም ይኖርባቸዋል። አባቷ ይህንኑ ሰምቶ ከከለከላት ግን የትኛውም ስእለቷ ወይም ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችበት መሐላ አይያዝባትም፤ የከለከላት አባቷ (መሪዋ) ስለሆነ እግዚአብሔር ነጻ ያደርጋታል።*

"እንዲሁም ከተሳለች ወይም አምልጧት ተናግራ ራሷን ግዴታ ውስጥ ካስገባች በኋላ ባል ብታገባ፣ ባሏም ሰምቶ ምንም ነገር ሳይላት ቢቀር፤ ስእለቶቿ ወይም ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችባቸው ነገሮች መፈጸም ይኖርባቸዋል። ሆኖም ባሏ ይህንኑ ሰምቶ ከከለከላት ግን ለመፈጸም የተሳለችውንም ሆነ አምልጧት ተናግራ ራሷን ግዴታ ውስጥ ያስገባችባቸውን ነገር ስለሚያስቀር እግዚአብሔር ከዚህ ነጻ ያደርጋታል" ይላል።

እኛ ነገሮቻችን በሙሉ በአብዮትና በሴቶች መብት ንቅናቄ አስተሳሰብ ስለተባለሸብን ነው እንጂ ውበቱ ያለው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሴቶች መብት ተሟጋች ከሚቴ ከሚሰጠን ይበልጣል።

የግሪኩን ቃል ብንመለከት ራስ የሚለው ቃል ከፍ ያለ ስልጣን ማለት ነው ይለዋል። ኤፌሶን ምዕራፍ 5፡23 እንደሚናገረው ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንን ራስ ሲሆን፤ የወንድ ድርሻ ደግሞ መሪነት ነው። ወንድ የተፈጠረውም ለዚህ ነው። መሪነት ሲባል የቤቱ ቄስ፣ መንፈሳዊ ካህን፣ ጦርነት በቤተሰቡ ላይ ቢነሳ፤ ተነሱ፣ ታጠቁ፣ እንዝመት በማለት የጦርነቱን ስልት የሚነድፍ የጦር መሪ፣ አዝማች፣ ለሚስቱና ለልጆቹ እንዲሁም ለንብረቱ ጥበቃ የሚያደርግ ማለት ነው። የቤተሰቡ ዐቃቤ ንዋይና የምጣኔ ሃብት ባለሙያ የሆነውም እርሱ ነው። መሪነት እነዚህን ነገሮች አጠቃሎ የያዘ ነው። ነገር ግን ቀደም ሲል ስለ ፍቅር ብዙ የተሳሳተ አስተሳሰብ አለ እንዳልኳችሁ ሁሉ መሪነትን በተመለከተም የተሳሳተ አመለካከት አለ።

ብዙ ሰዎች መሪነትን የሚገምቱት ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ብቻ ነው። ሰው የሚሾመው ጥቅም ለማግኘት፣ በሌላው ሰው ላይ ከፍ ሊልበት ነው። በእኛ በአበሾች ዘንድ እንኳን "በመስከረም ሲሾም በሰኔ አጃቢው ብዙ ነው" የሚባል አባባል አለ አይደል እንዴ? ሌላው የአገራችን አባባል "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል" የሚለው ነው። እነዚህ አባባሎች መሪነትን ከግል ጥቅም ማጋበሻነት ጋር ያያያዙ ናቸው። ጌታ ግን ደቀ መዛሙርቱን በአንድነት ሰብስቦ እንዲህ *"... ያሕዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው፣ ሹሞቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን እንደሚያሳዩ*

ታውቃላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፤ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ የሰው ልጅ ሊያገለግልና ሕይወቱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ መጣ እንጂ ሊገለገል አልመጣምና" (ማርቆስ 10:42) ነው ያላቸው። (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ራት በልተው እንደተነሱ ጌታ ኢየሱስ መሪነትንና አገልግሎትን በማገናኘት መጎናጸፊያውን አስቀመጠና ወገቡን በፎጣ ታጠቀ። ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ ያብስ ጀመር። እግራቸውን አጥቦ ካበቃም በኋላም፤ ልብሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠና *"ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤ እንደምትሉኝም እንዲሁ ነኝና። እንግዲህ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ እግራችሁን ካጠብሁ፤ እናንተም እንደዚሁ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ ይገባችኋል። እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም እንደዚሁ እንድታደርጉ ምሳሌ ትቼላችኋለሁ። እውነት እላችኋለሁ አገልጋይ ከጌታው፤ አይበልጥም፤ መላክተኛም ከላከው አይበልጥም። እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አውቃችሁ ብትፈጽሙ ትባረካላችሁ"* አላቸው (ዮሐንስ 13:12-17)። (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ይህን ምሳሌነቱን የተመለከቱት ደቀ መዛሙርቱ "ጌታ ሆይ እኛ የምናውቀው ደቀ መዝሙር የመምህሩን እግር ሲያጥብ እንጂ፤ ጌታ የባሪያውን እግር ሲያጥብ አይደለም" ያሉት ይመስለኛል።

ባል ቤተሰቡን የመምራት ድርሻ አለበት ሲባል፤ ወንድነቱን የሚያሳይበት መንገድ ቀበቶውን መፍታትና ጡንቻውን ማሳየት

አይደለም። ይሄ በጌታ ትምህርት ውስጥ የለም። ባልን ብቁና ጠንካራ መሪ የሚያደርገው በውስጡ ያለው የልቡ ጥንካሬ እንጂ ውጫዊ የጉልበት ጥንካሬው አይደለም። ባል ብቃት ያለው የቤተሰቡ መሪ የሚሆነው እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ ፍቅር ያለው፣ የባለቤቱንና የራሱን ድርሻ የሚያውቅ እና የሚገነዘብ፣ ራዕይ ያለው ባልና አባት ሲሆን ነው። ሰውን ጥንካሬ መሪ የሚያደርጉት እነዚህ አራት ውስጣዊ ባህርያት ናቸው።

እንግዲህ ቀደም ብለን ባል ሚስቱን የሚወድ፣ አፍቃሪ ሆኖ መገኘት አለበት አልን። ቀጥለን ቤተሰቡን መምራት ይኖርበታል የሚለውን ተመለከትን። እህቶች አንድ ወንድ ለጋብቻ ሲጠይቃችሁ ቀዳሚው ጥያቄያችሁ መሆን ያለበት ለእኔ ፍቅር አለው ወይ? የሚል ይሆናል። እናም ፍቅር እንዳለው እና እንደ ሌለው ለማረጋገጥ በተለያየ መንገድ ፍተሻ ይደረጋል። ለነገሩ የትኛው ዓይነት ፍቅር ነው? ዛሬ ሳይሆን ድሮ፣ ድሮ "ተልካሻ የጃፓን ዕቃ!" ይባል ነበር። እንደዚያ ዓይነት ተልካሻ ፍቅር ይኖር ይሆን? ወይንስ እውነተኛ መሰጠት ያለበት? ጥሩ የቤተሰቡ መሪ ይወጣዋል? የመሪነት ነገር የሚታይበት ሰው ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ራሳችሁን መላልሳችሁ መጠየቅና ምላሽ ለማግኘት ጥረት ማድረጉ ተገቢ ነው።

ሦስተኛው እና የመጨረሻው ሃሳብ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1 ተሰሎንቄ 2:12 ላይ *"አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁና"* ብሎ ራሱን ምሳሌ አድርጎ እንዳቀረበው ወንዱ ወይም ባልዬው ለቤተሰቡ መልካም የሕይወት ምሳሌ ወይም ሞዴል መሆን ይኖርበታል።

አንድ ወቅት ላይ መጋቢ መርዕድ ለማ ቤተ ክርስቲያናችን መጥተው ሲያገለግሉን ያስተማሩንን ስለ ሞዴልነት ሳስብ መርካቶ

ውስጥ ያሉት የጫማ ሱቆች ትዝ ይሉኛል። እነዚያ ሱቆች በመስታወት በተሰሩ መስኮቶች ውስጥ በተለያየ ዲዛይን የተሰሩ ጫማዎችን ደርድረው ያስቀመጣሉ። እነዚያ ጫማዎች እዚያ ቦታ የተቀመጡት የገዢውን ቀልብ እንዲስቡና ገበያ እንዲያመጡ ነው። ለሚገዛው ሰው የሚሸጡት መጋዘን ውስጥ በካርቶን የተቀመጡት ናቸው። ለማሳያነት እንደ ሞዴል የሚቀመጡት ግን ገበያ የሚስቡ ናቸው። ይሄ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ጫማዎች ስላሉን ወደ ሱቃችን ጎራ ይበሉ የሚል የንግድ ማስታወቂያ ማለት ነው።

ልክ እንደዚሁ ባልም በህይወቱ የሚታይ ሞዴል መሆን ይጠበቅበታል። በአምሳሉ ያፈራቸው ልጆቹ የሚሆኑት እርሱ የሆነውን ነው። ይገርማችኋል! በአምሳላችን የምንወልዳቸው በባህሪይም ጭምር እንጂ የእኛን አፍንጫና ጆሮ የመሳሰለ አፍንጫና ጆሮ ያላቸውን ልጆች ብቻም አይደለም።

ባል አታላይ ከሆነ የሚያፈራው አታላይ ልጅን ነው። የሚሰርቅ ከሆነ የሚወልደውም ሌባ የሚሆነው ልጅ እንጂ፣ ሌላ ሊመጣ አይችልም። የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ሕግ አድርጎ የደነገገው የተዘራው እንዲበቅል ነው። ብዙ የማወራ ለፍላፊ ዓይነት ከሆንኩኝ የምወልደውም ልጅ እንደዚያ ለፍላፊ ነው የሚሆነው።

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎችን በ1 ተሰሎንቄ 2፡7-12 ላይ *"ነገር ግን እናት ልጅዋን እንደምትንከባከብ እኛም በመካከላችሁ በየዋህነት ተመላለስን። የእግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንን ጭምር ልናካፍላችሁ ደስ እስከሚለን ድረስ ወደድናችሁ፤ ምክንያቱም እናንተ በእኛ ዘንድ ተወዳጆች ነበራችሁ። ወንድሞች ሆይ! ጥረታችንን እና ድካማችንን ታስታውሳላችሁ፤ በማንም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እየሠራን ወንጌል ሰበክንላችሁ። በእናንተ*

በምታምኑት መካከል ሳለን እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅ እንዲሁም ያለ ነቀፋ ሆነን እንደኖርን እናንተም እግዚአብሔርም ምስክሮች ናችሁ። አባት ለገዛ ልጆቹ እንደሚሆን እኛም ለእያንዳንዳችሁ የቱን ያህል እንደ ሆንን ታውቃላችሁና፣ ወደ መንግስቱና ወደ ክብሩ ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትኖሩ ዘንድ አበረታታናችሁ፣ አጽናናናችሁ፣ አጥብቀንም ለመንናችሁ" ይላቸዋል።

ይህን የጳውሎስን መልዕክት ስናጠቃልለው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ያካፈላቸው ወንጌልን ብቻም ሳይሆን ህይወቱንም ጭምር ነበር። ይሄ እንዴት ያለ የፍቅር ህይወት ነው። ባሎች ለቤተሰቦቻቸው ምሳሌ የሚሆኑት እንዴት ነው? በቤታችን ውስጥ ለልጆቻችን ሞዴል የምንሆነው አንዱ የፍቅርን ህይወት በማሳየት ነው። ጳውሎስ ከእናንተ የቆጠብነው ነገር የለንም ብሎ ነው የተናገረው። ቁጥር ዘጠኝ ላይ ደግሞ ወንድሞች ሆይ! ጥረታችንንና ድካማችንን ታስታውሳላችሁ፤ በማንም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊት እና ቀን እየሠራን ወንጌል ሰበክንላችሁ ብሎ እንደ ተናገረው ለሁሉም ሰው የሚታይ የሥራ ህይወት የነበረው ትጉ ሠራተኛ ስለነበር ያንን ነው የሚያስታውሳቸው። እኛስ ልጆቻችን ስለ እኛ ያላቸው ትዝብት ምንድነው? አንድ ቀን ከዚህ ምድር ስንሄድ ልጆቻችን ቁጭ ብለው ስለ አባቶቻቸው አስታውሰው የሚነጋገሩት ነገር ምን ይሆን? ይገርማችኋል! ሁሌ የሚያስጨንቀኝ ነገር ቢኖር ይሄ ነው።

እኔ ልጆቼ ካስታወሱኝ እንዲያስታውሱኝ የምፈልገው በሥራ ወዳድነት ነው። ምንም ዓይነት ሥራ ይሁን ሥራ ክቡር መሆኑን እንዲገነዘቡ፣ ሥራዬን ጥንቅቅ አድርጌ ሰርቼ ስጨርስ እንዲያዩኝና በኃላፊነት ለተሰጠኝ አደራም ብቁ ሆኜ እንዲያገኙኝ ነው።

ጳውሎስ “በእናንተ በምታምኑት መካከል ሳለን እንዴት በቅድስና፣ በጽድቅ እንዲሁም ያለ ነቀፋ ሆነን እንደኖርን እናንተም እግዚአብሔርም ምስክሮች ናችሁ” እንዳለው በጽድቅና በቅድስና በመመላለስ የሥነ ምግባር ጥራት ያለው የምሳሌነት ህይወትም ነበረው። የሚከሰስበት ነቀፋ አልነበረውም።

ይሄ ጉዳይ እንዴት አሳሳቢ ነው መሰላችሁ። አባቶች፣ ባሎች፣ የቤተሰብ መሪዎች ልጆቻቸውን መጠጥ ቤት በር ላይ አቁመው “አንተ እዚህ ሆነህ ጠብቀኝ፤ የሚያውቀኝ ሰው ወይም የቤተ ክርስቲያናችን መጋቢ ከመጣ ቶሎ ንገረኝ” ብለው ውስጥ ገብተው መጠጣቸውን የሚለጉ ከሆነ በኋላ ላይ ችግር የሚፈጥርባቸው ያ ልጅ ራሱ ነው። እንዴት አድርገው ነው የሚያሳድጉት? ምንስ ዓይነት ልጅ ነው የሚያፈሩት? ልጆቻችን እውነትን ተናግረው እንዲሞቱ ከሆነ የምንፈልገው ያንን እውነት እኛ ኖረን እናሳያቸው።

ነጻ ወይም የቅናሽ ክፍያ የትምህርት ዕድል ለማግኘት በማሰብ ከትምህርት ቤት የመመዝገቢያ ፎርም አምጥቼ ድሃ መሆኔን ለልጄ ነግሬው ፎርሙን ሞልቼ እልከዋለሁ። ልጄ ግን ድሃ እንዳልሆንኩ ልቦናው ያውቃል። ይሄ የሞራልም ጥያቄ ነው።

ልጆቻችንን በእግዚአብሔር እውነት ማሳደግ ከፈለግን ምሳሌ ሁነን መቆም መቻል አለብን። ከተሳሳትን፤ ልጄ ተሳስቻለሁ ይቅርታ አድርግልኝ፣ ልክ አይደለሁም፤ ጥሩ ምሳሌ አልሆንኩህም ብለን መመለስ መቻል አለብን።

ባል በቤተሰቡ ውስጥ ያለው ድርሻ እና ኃላፊነት ሚስቱን እና ልጆቹን መውደድ፣ ቤተሰቡን መምራት እና መልካም ምሳሌ መሆን ነው ብለን እንደ ተነጋገርነው፤ እነዚህን ሦስት ነገሮች ተግባራዊ

ለማድረግ መቁረጥ አለብን። ሚስቴን በተግባር መውደድ ከፈለግሁ “በእኔ ህይወት ውስጥ አንቺ የማትወጅውና እንድተወው የምትፈልጊውን አንድ ነገር ንገሪኝ” ብዬ መጠየቅ አለብኝ። እርግጠኛ ነኝ አስባበት ትነግረኛለች። ይህን ማድረግ ከቻልን ብዙ ፈውስ አለ። “ምን እንዳደርግልሽ ትወጃለሽ?” ብለንም እንጠይቃቸው። ለትዳር ጓድህ መልካሙን ነገር ስታደርግላት ለውጥ ይኖራል።

ቤታችን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይመራ። ፍቅራችን የምላስ ብቻ አይሁን። “ተከተል አለቃህን፤ ተመልከት ዓላማህን ነውና” ልጆቻችን እኛን ያያሉ፤ ይከተሉናልም። ስለዚህ እኛ የምናደርገውን ተከታትለው ጠብቀው ያደርጉታል። ህጻናት ልጆች ወንዶቹ በአባታቸው፣ ሴቶቹ ደግሞ በእናታቸው ጫማ ውስጥ እግራቸውን አስገብተው እየጎተቱ ሲሄዱ አይታችሁ አታውቁም? ልክ እንደዚያው ልጆች ወላጆቻቸው ሲያደርጉ ያዩትን ነገር ለማድረግ ይነሳሳሉና በምናደርገው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ እናድርግ።

የባል ድርሻ ሚስቱን መውደድ፣ ቤተሰቡን መምራት እና ለቤተሰቡ መልካም ምሳሌ መሆን ነው።

ምዕራፍ 9

የቤተሰብ አባላት ግንኙነት እና የሚስት ድርሻ

ምዕራፍ ዘጠኝ

የቤተሰብ አባላት ግንኙነት እና የሚስት ድርሻ

በመቀጠል ደግሞ የምንመለከተው በቤተሰብ ውስጥ ያለውን የሚስትን ድርሻ ይሆናል። የሴቶች ጉዳይ ብዙ ኮሚቴዎች የተቋቋሙበት፣ በፖለቲካውም ዓለም ሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙ የሚያነጋግር ጉዳይ ስለሆነ ቀላል እንዳልሆነ ይታወቃል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥም በጣም ትልቅ የሴቶች ድርሻ አለ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የሴቶች ድርሻ ምንድነው? ከእነርሱ ጋር ያለን ግንኙነትስ እንዴት ነው የሚታየው? የሚለው ሃሳብ በጣም ብዙ የሚያነጋግሩን ነገሮች ስላሉት ዋና ሃሳብ ነው ብዬ ወስጀዋለሁኝ።

መጽሐፈ ምሳሌ 24፡3-4 *"ቤት በጥበብ ይሠራል፥ በማስተዋልም ይጸናል፤ በዕውቀትም ከከበረውና ካማረው ሃብት ሁሉ ጓዳዎች ይሞላሉ"* ብሎ ይናገራል።

ይኸ የጥበብ መጽሐፍ ስለ ሴቶች ብዙ የሚናገረው ነገር አለው። እኔም ከበጎ ንግግሩ ስጀምር በምዕራፍ 11፡16 ላይ *"ሞገስ ያላት ሴት ክብርን ታገኛለች"*። በምዕራፍ 12፡4 ላይ *"ልባም ሴት ደግሞ ለባሏ ዘውድ ናት"*። በምዕራፍ 14፡1 ላይ *"ብልሃተኛ ሴት ቤቷን ትሰራለች፤ . . ."*። በምዕራፍ 18፡22 ላይ ደግሞ *"ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ"* ብሎ ይናገራል።

ሚስትን ከጥሩ ደሞዝ፣ ሃብት፣ ዲቪ ሎተሪ እና ከሌሎችም ነገሮች ሁሉ ጋር አወዳድሯት። ከእነዚህ ሁሉ እርሷ ትበልጣለች። በእውነት ምንም ነገር ባይደርስህ የትኛውንም ዓይነት ቪዛ ባታገኝ ሚስት ካገኘህ በረከትን አገኘህ። በእግዚአብሔር ዘንድ የተጻፈው እንደዚህ ነው።

ይኼው የመጽሐፈ ምሳሌ ሲናገር ቤትና ባለጠግነት ከእግዚአብሔር ይወረሳል፤ አስተዋይ የሆነች ሚስት ከእግዚአብሔር ዘንድ ስጦታ ናት ይላል። የእግዚአብሔር ቃል ልባም፣ አስተዋይ፣ ብልሃተኛ፣ ሞገስ የጠገበች ሴት እያለ የሚጠራት ሴት አለችው። እንደ እነዚህ ያሉ ነገሮች ያሏት ሴት በውስጧ ዕምቅ ኃይል ያላት ናት። እንዲህ ዓይነት ልባም፣ ብልሃተኛ፣ በረከትና የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነች ጠንካራ ሴት የምትገኘው ደግሞ እግዚአብሔር መካከለኛ በሆነበት፣ ራዕይ ባለው፣ የሁሉም የቤተሰቡ አባል ድርሻ በውል በሚታወቅበት እና እርስ በርሱ በህብረት በተያያዘበት ጠንካራ ቤተሰብ ውስጥ ነው።

ያንጊዜ የሴቲቱ የሥራ ድርሻ በጎብረ ቀለማት ያሸበረቀ ሆኖ ይወጣል ማለት ነው። ታዲያ ይኸውም መጽሐፍ ስለ ሴት ደግ ደጉን እንደነገረን ሁሉ አሉታዊ ጎኗንም እንዲህ ሲል በሚከተሉት ክፍሎቹ ነግሮናል። በምሳሌ መጽሐፍ ምዕራፍ 12፡4 ላይ *"አሳፋሪ ሴት ግን በአጥንቱ ውስጥ እንደ ቅንቅን ናት"*። በምዕራፍ 27፡15 ላይ *"ባዘናብ ቀን የሚያንጠባጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው"*። በምዕራፍ 21፡9 ላይ *"ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ውስጥ ከመቀመጥ በውጭ በቤት ማዕዘን ላይ መቀመጥ ይሻላል"* ብሎ ይናገራል።

ምን እና ምን አድርጎ እንደሚያወዳድረው ማየት ትችላለችሁ። ምዕራፍ 21፡19 ደግሞ ይኸው የምሳሌ መጽሐፍ

"ከጠበኛ እና ከቁጡ ሴት ጋር ከመቀመጥ፤ በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል" ይላል። የእግዚአብሔር ቃል ሴትን የሚገልጻት እንዲህ አድርጎ ነው። ልክ ብልሃተኛ፣ ልባም፣ ሞገስ የጠገበች፣ ለባሏ ዘውድ ናት ብሎ የሚናገራትን ያችኑ ሴት መልሶ በዚህ በኩል ደግሞ ጠበኛ፣ አሳፋሪ፣ ቁጡ ሴት ይላታል። ይሁንና ክፉ፣ ክፉውን ትተን ደግ ደጉን ለመያዝ ጠንካራ ቤት ያስፈልጋል።

ይህች ሴት በዚያ ጠንካራ ቤት ውስጥ በትክክለኛዋ ስፍራዋ ከተቀመጠች ትክክለኛ የሥራ ድርሻዋን ካገኘች ደጉ ነገሯ ነው ጎልቶ የሚወጣው። በራሱ ሙሉ፣ ፍጹም እና ስህተት የማይገኝበት ሰው እንደሌለ እናውቃለን። ወንዱ ያለውን ዓይነት ጉድለት እርሷም ይኖራታል። ነገር ግን በጎ ነገሯ የሚወጣው እነዚህ መልካሞቹ ነገሮቿ ማለትም ብልህነቷ፣ አስተዋይነቷ፣ ሞገሳምነቷ፣ ዘውድነቷ በረከትነቷ እና የእግዚአብሔር ስጦታነቷ የሚወጣው በትክክለኛ የሥራ ድርሻዋ በትክክለኛ ቤታ በጠንካራ ቤተሰብ ውስጥ ከተቀመጠች ነው።

ወንድን መሪ ነው ብለን የምንል ከሆነ ሴቷን ደግሞ እንደ ረዳትነቷ ተጣማጇ አድርገን መውሰድ እንችላለን። *"መሪነት ተጽዕኖ መፍጠር ነው"* ብለው የሚያስተምሩ ወገኖች እንደሚሉት በሌላ አነጋገር የሁለቱም ድርሻ አንድ ዓይነት ነው። ነገር ግን የተለያዩ ዓይነት መገለጫዎች አሉት። ወንዱ በግልጽ ከፊት ለፊት ሆኖ የመምራቱ ነገር ቢታይበትም ወንዱም ሆነ ሌሎቹ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ከሴቷ ተጽዕኖ ውጪ ግን አይደሉም።

ሴቷ ተጽዕኖ የምታደርግበትን መንገድ ላሳያችሁ። የእግዚአብሔር ቃል *"እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት"*

(ዘፍጥረት 2፡18) ብሎ እንደሚናገር መጀመሪያ እርሷ ጥሩ ተጽዕኖ እንዲኖራት ቁጥር አንድ ረዳት መሆኗን እንቀበል።

ብዙ ሰዎች ረዳት ስለሚለው ቃል ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው። ረዳት የሚለውን ቃል ሴቷ ከወንዱ ጋር ተወዳድራ ልትስተካከልበት ያልቻለችው አንድ ብቃት እንዳጣች አድርገው በአሉታዊነቱ ነው የሚተረጉሙት። እንዲያውም ረዳት ስለ ሚለው ጽንሠ ሃሳብ የሚከተለውን ዓይነት ስዕል ነው ያላቸው። በአገራችን በቤት ውስጥ ሥራ የሚያገለግሉ ሁለት ሠራተኞች ይቀጥሩና አንደኛዋ ዋናውን ትላልቁን የቤቱን ሥራ የምትሰራ ሁለተኛዋን ደግሞ በመጀመሪያዋ ስር ረዳቷ ሆና ህጻን ልጅን በመሸከም በማጫወት ረዳቷ አድርገው ይሰይሟታል። እናም ያችኛዋ ምንም ምርጫ ስለሌላት አድርጊ ያለቻትን ሁሉ ነው የምታደርገው። ትልቋን ሠራተኛ ጨምሮ በቤቱ ውስጥ ሁሉም ሰው ያዛታል። ሁሉ ነገር ሄዶ ሄዶ እዚህች ትንሿ ሞግዚት ላይ ነው የሚያልቀው። ያች ትንሿ ልጅ እዚህ ቤት የተቀጠረችው ለትልቋ ሠራተኛ ረዳት ተብላ ነው። እናም ረዳት የሚለውን ቃል እንደዚህች ትንሿ ረዳት ልጅ አድርገው ነው የሚወስዱት። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ ረዳት የሚለውን ቃል በዚህ ትርጓሜ አይደለም የሚገልጸው። ሴት ለወንዱ በፍጹም እንደዚያ አይደለችም።

ረዳት የሚለውን ቃል በሁለት መንገድ ነው የምገልጸው። ጌታ አምላካችን ዘፍጥረት 2፡20 ላይ *"አዳም ሕይወት ላላቸው ፍጡራን ሁሉ ያወጣላቸው ስም መጠሪያቸው ሆነ። ስለዚህ አዳም ለከብቶች፣ ለሰማይ ወፎች፣ ለዱር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው። ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር"* ብሏል። "እንደ እርሱ ያለ ረዳት"። ከእርሱ የማታንስ፣ የማትበልጥም፣ ነገር ግን እንደ እርሱ ያለች ረዳት።

እግዚአብሔር አምላክም ከአፈር ካበጀው ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ምንም ያልጎደላት ሴት አድርጎ ሰራት። ሔዋን የማንነት ጉድለት ሳይኖራት ሙሉ ሆና የተሰራች ናት። ሸክላ ሰሪ ቤት ብትሄዱ ሸክላ ሰሪው በሸክላው ለንግድ፣ ለነገሥታት ቤት አገልግሎት የሚውሉ የሸክላ ሥራዎችን ሲሰራ ይውልና መጨረሻ ላይ የተረፈችውን ትንሽ ጭቃ ያድቦለቡልና ለወንድ ልጁ የሚጫወትበት የጭቃ ብይ ሰርቶ ይሰጠዋል።

እግዚአብሔር ሴትን እንደዚያ አድርጎ አይደለም የሰራት። በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ጥሎበት፤ ከአዳም ከራሱ በወሰደው ሥጋ ነው የሰራት። ከሰራት በኋላም ወደ አዳም ሲያመጣት አዳም "እነሆ፤ ይህች አጥንት ከአጥንቴ፤ ሥጋም ከሥጋዬ ናት" ብሎ ደስ እያለው ተቀበላት። እግዚአብሔርም ያንጊዜ አዳም የምትስማማው ረዳት አግኝቷል አለ። ሔዋን የይዘት ችግር፣ የንጥረ ነገር ልዩነት የለባትም። በእግዚአብሔር ዘንድ ረዳት ተብላ ተጠርታለች።

በትንቢተ ሆሴዕ 13፡9 ላይ *"እስራኤል ሆይ፣ በእኔ በረዳትህ ላይ በመነሳትህ ጥፋትህ ነው"* ተብሎ ተጽፏል። እግዚአብሔር ለእስራኤል ረዳቱ ነው። ምን ማለቱ ነው? የሚያስፈልገውን ነገር የሚያደርግለት፤ እርሱን ተክቶ የእርሱን ሥራ የሚሰራ ማለት ነው። በዚህ ቃል ሃሳብ መሠረት እግዚአብሔር የእስራኤል ረዳት መሆኑ የእስራኤል የበታች ያሰኘዋልን? በእግዚአብሔር ሃሳብ ሴት ረዳት ማለት ናት። ረዳት የሚለው ቃል የእርሱን ከእርሷ ማነስ ሳይሆን የምታደርግለትን የሚያመለክት ነው። መጽሐፈ ምሳሌ 31፡11-12 ስለ ልባሚ ሴት ሲናገር *"የባልዋ ልብ ይታመንበታል፣ ምርኮም አይጎድልበትም። በሕይወት ዘመኗ ሁሉ መልካም ታደርግለታለች እንጂ አትጎዳውም"* ብሎ ይናገራል።

እግዚአብሔር ለእስራኤል "በእኔ በረዳትህ ላይ ስለተነሳህ" የሚለው ቃል መልካም በማደርግልህ በእኔ ላይ ማለቱ ነው። ረዳት የሚለው ቃል ሚስት ለባሏ የምታደርግለትን የሚያመለክት ቃል ነው። መጽሐፈ ምሳሌ 31:23 ላይም "ባሏ በአገር ሽማግሌዎች መካከል በአደባባይ በተቀመጠ ጊዜ የተከበረ ነው" ይላል። ይህ ሰው ታዋቂ እና አንቱ የተባለ የተከበረ ሰው የሆነው እርሷ ዕድሜ ልኳን ከምታደርግለት ነገር የተነሳ ነው። ምንም የማይጎድልበት ሰው ስለሆነ ነው። ሔዋንን ረዳት ያሰኛት ይህ ነው።

ታዲያ ወንድ መሪ ነው ከተባለና ሴት ረዳቱ ሆና የምትከተለው ከሆነ እርሷስ የራሷ ሃሳብ ሊኖራት አይችልምን? ልዩነትስ ሊኖራት አይችልምን? ለዚህ ጥያቄ መልሴ አዎን ሊኖራት ይችላል። በሃሳብ ሊለያዩ ይችላሉ። ፍጹም ሃሳቧን ማቅረብ ትችላለች። ግን ሃሳቡ የሚቀርበው በምክር እና በፍቅር መልክ ነው። በውስጡ ተንኮል፣ ጠብና ንትርክን ያለበት መሆን የለበትም። መሆን ያለበት ጽድቅ፣ እውነትና ገርነት ያለበት ነው።

ለአንድ አፍታ ኤልዛቤል ጋ ልውሰዳችሁ። ኤልዛቤል አንድ ቀን ባሏ አክዓብ ተበሳጭቶና ተቆጥቶ አገኘችው። ከዚያም "እስከዚህ የተበሳጨኸው፤ ምግብስ የማትበላው ለምንድነው?" ብላ ጠየቀችው። እርሱም "ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን የወይን ተክል ቦታህን ሸጥልኝ፤ ከፈለግህ በምትኩ ሌላ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ አልሁት፤ እርሱ ግን የወይን ተክል ቦታዬን አልለቅልህም ስላለኝ ነው" አላት። ኤልዛቤልም "አንተ አሁን የእስራኤል ንጉሥ ትባላለህ? በል ተነሳና እህል ቅመስ፣ ደስም ይበልህ፤ ኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ተክል እኔ እንድታገኝ አደርግሃለሁ" አለችው።

እናም ሂዳ ናቡቴን በክፉ ምክሯ አስገደለችውና እርሻውን የባለቤትነት ስሙን አዙራለት ይኸውልህ የጓጓህለት እርሻ ብላ ሰጠችው። ይኼ ረዳትነት ነው እንዴ? ባሏ ማግኘት የፈለገውን ነገር ከማግኘት አንጻር የረዳችው ነው የሚመስለው። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ ረዳትነት በፍጹም እንዲህ አይደለም። አክዓብ በዚህ ድርጊቱ ተዋረደበት እንጂ አልከበረበትም። የማደርግብህን ታውቃለህ ነው ያለው።

ረዳት መሆን መርዳት ነው። የምትረዳው የልዩነት ሃሳቧን በማቅረብ ጭምር ነው። ኤልዛቤል ባሏን እንዲህ ልትለው ትችል ነበር። "እንዴ!. . .አይሁዳዊ እንዴት አድርጎ ነው የአባቶቹን ርስት የሆነውን መሬት አሳልፎ የሚሰጠው? እየተመኘህ ያለኸው እኮ ልትመኘው የማይገባህን ነው። ሱሪ በአንገት አውልቁ ዓይነት። ከናቡቴ ጋር ዝምድና ቢጤ ካለህ በመቤዠት ሕጋችሁ ምናልባትም መሬቷን ማግኘት ከቻልክ ሞክር፤. . .አለበለዚያ" በአክብሮት በፍቅር እንዲህና እንዲያ ልትለው ትችል ነበር። ለእርሱም ቢሆን እውነትና ጽድቅ ያለበት ምክር ከሆነ ሚስቱን ቢሰማ ነው የሚሻለው። አስተዋይ ሚስት እግዚአብሔር ሰጥቷቸው ሳለ፤ በእነርሱ አዕምሮ ተጠቅመው ብዙ ማትረፍ ሲችሉ ሂደው ከገረዳቸው ጋር ተላትመው ቁስልና ውርደት በቁና የሰፈሩ፤ ነፍሳቸውንም ያጡ ስንት ሞኝ ባሎች አሉ መሰላችሁ!

የመጽሐፍ ቅዱሷን አስተዋይ ሴት አቢግያን ታስታውሷታላችሁ? አቢግያ በቤቷ ላይ ሊመጣ ያለውን ክፉ ነገር ማሸተት እና መለየት እንዲሁም መልካም የሆነው ነገር ምን እንደሆነ መለየት የምትችል ጓዳዋን በጥንቃቄ የምትመራ አስተዋይ ሴት ነበረች።

ይህቺ ሴት አንድ ቀን ሰነፉና ምግባረ ብልሹው ባሏ ናባል ስለ ሰራው የስንፍና ሥራ ስትሰማ ለባሏ ሳትነግረው ወደ ቤቷ እየገሰገሰ የመጣውን የአንድን ሰው ቁጣና በቤቷ ላይ ሊመጣ ያለውን ሞት ልታበርድ ብድግ ብላ አህያዋን ሞና ተነሳች። ሂዳም በእርሷ አቅም የሚደረገውን ነገር ሁሉ በማድረግ የንጉሱን ቁጣ አብርዳ፣ ሰይፍን እና ሞትን ከቤቷ መልሳ መጣች። ረዳት ማለት እንዲህ ነው። በባሏ ላይ የተደገሰውን ሞት ከለከለች። ባሏ ናባል ግን ድግስ ደግሶ ሲበላ ሲጠጣ ሲሳከር ድንገት ነው የሞተው። ወገኖቼ የምናምንቴ ሰዎች መጨረሻቸው እንዲህ ነው።

እስቲ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የሚስትን ኃላፊነቶች በዝርዝር እንመልከት።

ሀ. ረዳትነት

የሚስት የመጀመሪያ ድርሻዋ ባሏን መርዳት ነው። ሚስት በባሏ ላይ ጥበብ የተሞላበት ተጽዕኖ የምታደርግበት መንገድ መርዳት ነው። ይህም ከላይ እንደ ተገለጸው ነው።

ለ. መገዛት

ሁለተኛው መገዛት ነው። መገዛት ወደሚለው ስመጣ በቆላስየስ መልዕክት ምዕራፍ 3፡18 ላይ "ሚስቶች ሆይ በጌታ ዘንድ ተገቢ በመሆኑ ለባሎቻችሁ" ተገዙ ሲል፤ በኤፌሶን መልዕክት ምዕራፍ 5፡24 ደግሞ "እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ፤ ሚስቶችም ለባሎቻቸው በማንኛውም ነገር እንደዚሁ መገዛት ይገባቸዋል" ይላል። ልክ እንደ ረዳት ሁሉ መገዛትን በሚመለከትም የተዛቡ አመለካከቶች አሉ። መገዛት የሚለውን ቃል

እንደ ሞቆና፣ ባርነት የመሰሉ አስከፊ ግዴታዎች አድርገው የሚመለከቱ ሰዎች አሉ። አንዳንድ ሰዎች ይሄ የቆየ ባህል ነው። ይሄ ድሮ ጳውሎስ በነበረበት ዘመን የነበረ ችግር ስለሆነ በዚህ ዘመን ያለነውን ሰዎች አይመለከትም የሚሉም አሉ። ግን ይሄ እኮ ስለ ባርነት ወይም ስለ ሞቆና አይደለም የሚናገረው። እንዲያውም ጳውሎስ በገላትያ መልዕክት ምዕራፍ 3፡28 ላይ "በአይሁድና በግሪክ፤ በባሪያና በነጻ ሰው፤ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፤ ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁ" ብሎ ነው የሚናገረው።

መገዛት ማለት መጨቆን፣ ባሪያ መሆን አይደለም። መገዛት የሚለው ቃል ትርጉሙ በፍጹም ከዚህ የተለየ ነው። ታዲያ በመጽሐፍ ቅዱስ መገዛት የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን ማለት ነው? ካለን የመጀመሪያ መፍቻ ቃላችን ሥላሴን (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን) መመልከት ነው። በሥላሴ መካከል አንዱ ለሌላው እንደሚገዛ በተለይ ደግሞ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የፊልጵስዩስ መልዕክት ምዕራፍ 2፡5-8 እንዲህ ይለናል። *"እርሱ በባሀርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገለጠም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞትም ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ"* (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)

ወደዚህ ዓለም መጥቶ ሥጋ ለብሶ መታዘዙ ይሄ ወልድን ትንሽ አምላክ አያደርገውም። እርሱ ቢታዘዝም እግዚአብሔር ነው። 1 ቆሮንቶስ 15፡27-28 ሥጋ ለብሶ የተገለጠው ጌታ ለአባቱ ስለመገዛቱ ሲናገር *"ሁሉን ነገር ከእግሩ በታች አስገዝቶለታል ተብሏልና፣ ነገር ግን ሁሉን ነገር አስገዛሉት ሲል ሁሉ ነገር*

በክርስቶስ ሰር እንዲገዛለት ያደረገውን እግዚአብሔርን እንደማይጨምር ግልጽ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልድ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ለእርሱ ይገዛል" የሚል ቃል ታገኛላችሁ። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በማንነትና በህልውና መለኮት ነው። ይሁንና ድርሻቸውን ስንመለከት ግን አንዱ ለሌላው ሲላክ፣ ሲገዛ እናገኛለን።

አባት ልጁን ወደዚህ ምድር ሊልክ በወደደ ጊዜ ልጁ እሺ ብሎ በመታዘዝ ወረደ። አባትም በዚህ በልጁ መታዘዝ ደስ ተሰኘ። ልጁም በነገር ሁሉ ለአባቱ ለመገዛት እስከ መስቀል ሞት ድረስ ታዘዘ። ልጅ ከሞት በተነሳና በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ ጊዜም መንፈስ ቅዱስን ለመላክ ወደደ። መንፈስ ቅዱስን በላከው ጊዜም መንፈስ ቅዱስ ወርዶ እስካሁን ድረስ በምድር ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቀደ። መንፈስ ቅዱስ ለአብና ለወልድ ያለውን መገዛት ልናስተውል ይገባል። በዚህ ግንኙነት ውስጥ ጭቆና፣ ባርነት፣ ክፋት፣ ጠማማነት የሚባሉ ነገሮች የሉበትም።

የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ የምትገዛበትን መገዛት ያሳየበት ስዕል አለው። ስዕሉም ራስ እና አካል በሚል በምሳሌነት የሚያቀርባቸው የራሳችንን የሰውነት ክፍሎች ነው። ራስ ጧት ተነስቶ "ይሄ አካል የሚባለው እኮ አስቸገረኝ! ቆይ ልኩን አሳየዋለሁ!" ብሎ በጭካኔ ጉዳት አያደርስበትም። ራስና አካል በትብብር ነው የሚኖሩት። ራስና መላው አካላችን በትብብር ስለሚሰሩ ነው በሰላም ወጥተን በሰላም የምንገባው። አንዱ ለሌላው ይገዛል። ራስ አካልን "አሁን በቃ ብቻህን ሻወር ውሰድ፣ ተጣጠብ" ሲለው፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ "ትንሽ ሮጥ፣ ሮጥ እንበል" ይለዋል።

በባል እና ሚስት መካከል ያለው መገዛትም በትብብር ነው። ሁለቱም እንዲያምርባቸው እርሱም ሆነ እርሷ ባለ ሞገስ እንዲሆኑ እርስ በርስ ተፈቃቅደው ሚስት ለባልዋ መገዛት ነው ያለባት።

መገዛት የሚለው ቃል ባል እና ሚስት እንዲላላካቸው፣ እንዲያምርባቸው እና እርሱም ሆነ እርሷ ሞገስ የጠገቡ እንዲሆኑ ሁለቱም አውቀውና ፈቅደው ነው የሚገዙት። ይህ ዓይነቱ መገዛት በውስጡ ጭቆና፣ ባርነት፣ ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት የለበትም። ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ የሚለውን ቃል ትርጉም ለማወቅ ከፈለጋችሁ 1 ጴጥሮስ 5፡5 ላይ *"ጎልማሶች ሆይ፣ እናንተም እንዲሁ ለሽማግሌዎች ተገዙ፣ ሁላችሁም እርስ በርስ በመከባበር ትህትናን ልበሱ፣ ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፣ ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል"* የሚለውን ቃል ታገኛላችሁ። እዚህ ቦታ ላይ ሽማግሌዎች የሚላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ነው። ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንድንገዛ ታዘናል። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚያስተዳድሩን በግድና በኃይል ሳይሆን፣ እነርሱን መሪዎች አድርጎ የሰጠን እግዚአብሔር በመሆኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል ወደንና ፈቅደን ነው የምንገዛው።

በፊልጵስዩስ ምዕራፍ ሁለት ላይ *"በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ያ አስተሳሰብ (አመለካከት) በእናንተም ዘንድ ይሁን"* እንደሚል ነገሩ የአመለካከት ጉዳይ ነው። መቀየር ያለበት አስተሳሰባችን ወይም አመለካከታችን ነው። መገዛት ግን ባርነት ወይም ጭቆና የለበትም።

ሐ. መቆነጃጀት

መጽሐፍ ቅዱሳችን በአንደኛ ጴጥሮስ 3፡1-5 ላይ *"ሚስቶች ሆይ፤ እናንተም እንደዚሁ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ አንዳንድ ለቃሉ የማይታዘዙ ቢኖሩ፤ ያለ ቃል በሚሰቶቻቸው አኗኗር ተማርከው ይመለሳሉ፤ ይህም የሚሆነው ንጹህና ፍጹም አክብሮት የተሞላውን ኑሯችሁን ሲመለከቱ ነው። ውበታችሁ በውጫዊ ነገሮች በመሸሞንሞን ይኹም ሸሩባ በመሠራት፤ በወርቅ በማጌጥና በልብስ አይሁን። ነገር ግን ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን። ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ የጣሉ የቀድሞ ቅዱሳት ሴቶች ራሳቸውን ያሰዋቡት በዚህ ዓይነት ለባሎቻቸው በመገዛት ነበርና"* ይላል።

እነዚህ ቅዱሳን ሴቶች ራሳቸውን ያስዋቡት፣ ያሸሞነሞኑት ለባሎቻቸው በመገዛት ነበር። የእግዚአብሔር መልክ ይታይባቸው እንደነበሩ የእግዚአብሔር ቃል የመሰከረላቸው እነዚህ የቀድሞ ቅዱሳት ሴቶች ለባሎቻቸው ሲገዙ ራሳቸውን እንደሚገባ ያቆነጃጁ፣ ይሸላልሙ ነበር። በዚህ ሁላችንም እንስማማለን። በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ መቆንጃጀት የሚለው ነገር ጥሩ ነው። ወንዶች የሚስቶቻችንን መቆነጃጀት መጥላት የለብንም። ሴቷ ውብ፣ ቆንጆ ለመሆን በምታደርገው ጥረት መጣላት፣ መጨቃጨቅ አያስፈልግም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያበረታታው ቆንጆ ለመሆን መሞከሯ ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን ቁንጅናን በተመለከተ የውጪ ውበትና የውስጥ ውበት ብሎ ለሁለት ከፍሎ ነው የሚናገረው።

በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ሞገሳም የምንሆነው እነዚህን ሁለት ውበቶች በጥንቃቄ ስናውቅ ነው። የውጭ እና የውስጥ

የተባሉትን ውበቶች በዕውቀት ካልያዝናቸው ግን ሁልጊዜ ሚዛናቸውን ያጡ ይሆናሉ። ውጪያችን ቆንጆ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ አይቃወምም። እንዲያውም የዘጸአት መጽሐፍ ምዕራፍ 28፡5 ብታነቡት *"ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ የተለየ ይሆን ዘንድ ጥበብ ለሰጠኋቸው በዚህ ጉዳይ ላይ ጥበበኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ ለአሮን መጎናጸፊያውን እንዲሠሩለት ንገራቸው። የሚሠሯቸው መጎናጸፊያዎች የደረት ልብስ፣ ኤፉድ ቀሚስ፣ ጥልፍ ሸሚዝ፣ ጥምጥምና መታጠቂያ ናቸው። ወርቅ ሰማያዊ ሐምራዊ ቀይ ማግና እንዲሁም ቀጭን በፍታ ይጠቀሙ"* (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ይላል። ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደምንረዳው የእስራኤል ካህናት በተለይም ሊቀ ካህናቱ በጎብረ ቀለማት ያጌጡ አልባሳትን እንዲለብሱ ያዘዛቸው እኮ እግዚአብሔር ራሱ ነው። እኔ ቆንጆ ልብስ መልበስ ደስ ይለኛል። የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ጌታ እግዚአብሔርም በጎብረ ቀለማት ያጌጠ ነገር አይቃወምም፤ ቆንጆ ነገር በራሱ ምንም ችግር የለውም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እውነት በ1 ጢሞቴዎስ 2፡8 ላይ ሲገልጠው *"እንዲሁም ሴቶች በጨዋነትና ራሰን በመግዛት ተገቢ የሆነ ልብስ ይልበሱ እንጂ በሹሩባ ወይም በዕንቁ ወይም ዋጋቸው ውድ በሆኑ ልብሶች አይሸቀርቀሩ፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን የሚሉ ሴቶች ሊያደርጉ እንደሚገባ በመልካም ተግባር ይዋቡ"* ይላል።

ክርስቲያን ማሳየት ያለበት የውስጡን እንጂ የውጭውን አይደለም። የውሃ ጥምቀት ስርዓትን ስንፈጽም በምንገባው ቃል ኪዳን መሠረት ከእንግዲህ ለራሴ ሳይሆን አሮጌው እኔነቴ ሞቶ በአዲሱ ማንነቴ ለክርስቶስ ልኖር ከክርስቶስ ጋር ሞቻለሁ፤

ተለውጫለሁ እንደምንለው እንደዚያው የምንለብሰው ልብሳችንም ሆነ መቆንጃጀታችን በውስጣችን የሆንነውን ነገር በውጪ የምናሳይበት ነገር ነው የሚሆነው። እንደ ሌሎቹ ራቁቴን መሄድ የማልፈልገው ውስጤ ካለው ነገር ጋር ስለሚጋጭብኝ ነው።

በውጪ መሽቀርቀሩ ላይ መስታወት ፊት ቆሜ አንዴ ወደፊት አንዴ ወደ ኋላ እያልኩ አንድ ሰዓት ላባክን እችላለሁ። ግን ያ በውስጤ ያለውን በክርስቶስ ያገኘሁትን ሕይወት ያሳያልን? ለእግዚአብሔርስ ክብር ይሆናልን? መለኪያው ያ ነው።

ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ክፍል ውስጥ ሳስተምር ተማሪዎቹን "ከአሁን በኋላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንዶች እና ሴቶች ለየብቻ ነው የምትቀመጡት ቢባል ምንድነው የምትሉት?" ብዬ ብጠይቃቸው፣ የሰጡኝ መልስ "አሁን ያለው ውጥንቅጡ የወጣ አለባበስ ግራ ያጋባን ስለሆነ ይሄማ ግልግል ነበር! አንዳንድ ጊዜ እኮ የት ነው ያለነው? ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይስ . . .እንላለን" የሚል ነበር።

አያችሁ በ1 ጢሞቴዎስ 2፡10 ላይ የተጠቀሰው *"በሚገባ ልብስ"* የሚለው ቃል ካልተጠበቀ እንዲህ ወዳለ አባዜ ውስጥ ነው የሚከተን። ሽኩቻ ይበዛል፣ መገፋፋት፣ መዘናጠል እና እርስ በርስ በክፉ ዓይን መተያያት ይመጣል።

መጽሐፈ ምሳሌ 11፡22 እንዲህ ይላል። *"የወርቅ ቀለበት በእርያ አፍንጫ እንደሆነ ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንዲሁ ናት"*። የእግዚአብሔር ቃል በጣም በአጽንዖት የሚናገረውን ቃል እኛም በዚያው ድምፀት ጠበቅ አድርገን መናገር ይኖርብናል።

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል የመልዕክቱ ማጠንጠኛ ምስል መከሰቻ ተደርጎ የቀረበው እንስሳ አሳማ ወይም እሪያ ነው። ይህ

እንስሳ ደግሞ በአይሁዳውያኑ ዘንድ ፀያፍ ነው። በጣም ነው የሚጠሉት። በሚጠሉት ነገር ላይ ወርቅ ማንጠልጠል ደግሞ ለእነርሱ ከእሳቤያቸው ውጪ ነው። አንዲት ቆንጆ ሴት ከጥበብ የተለየች እስክ ሆነች ድረስ ምንም እንኳ ውበት ቢኖራትም ጥበብ አልባ ሆና ተገኝታለችና የወርቅ ቀለበት ቢደረግለትም ፈጽሞ ሊዋብ እንደማይችል አሳማ ሆና ተገኝታለች ነው አንድምታው። የድፍረት ቃል ልናገር ፈልጌ አይደለም። ቃሉ የሚለው ግን ይህንን ነው። ጌታ ከእኛ የሚፈልግብን የውስጥ ውበትን እንድንከታተል ነውና አዲሱን ሰው ልበሱት።

ጌታ በጣም የተቸገረባቸውና የተቆጣቸው ውስጣቸው ቆሽሾ ሳለ ውጪያቸውን ያጠሩ የነበሩ ሰዎችን ነው። እነዚህን ሰዎች በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 ላይ እናገኛቸዋለን። የውጪውን ውበታችንን ስንጠብቅ ለውስጠኛው ውበት እንድናስብ ጌታን ውስጤንም እጠብልኝ እንድንል ጌታ ይርዳን!

መ. ሠራተኛነቷ

ይህች ቤቷን የምትሰራ አስተዋይ ልባም ሴት የምትታወቅበት አንዱ ባህርይዋ ሠራተኛነቷ ነው። መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 31፡13-27 ስለዚህች በጣም ስለተመሰገነች ሴት ሲናገር እንዲህ ይላል። *". . .የበግ ጠጉርና የተልባ እግር መርጣ፣ ሥራ በሚወዱ እጆቿ ትፈትላቸዋለች። እንደ ንግድ መርከብ ምግቧን ከሩቅ ትሰበስባለች። ገና ሳይነጋ ትነሳለች፣ ለቤተ ሰቧ ምግብ፣ ለሴት አገልጋዮቿም ድርሻቸውን ትሰጣለች። ራቧ አስባ የእርሻ መሬት ትገዛለች፣ በምታገኘውም ገንዘብ ወይን ትተክላለች። ብርታትን ታጥቃ ሥራዋን ታከናውናለች። ክንዶቿም ለሥራ ብርቱ ናቸው። ሥራዋ*

ትርፋማ መሆኑን ታስተውላለች፤ በሌሊትም መብራቷ አይጠፋም። በእጇ እንዝርት ትይዛለች፤ በጣቶቿም ዘንጉን ታሾራለች። ከንዶቿን ለድሆች ትዘረጋለች፤ እጆቿንም ለችግረኞች ፈታ ታደርጋለች። በረዶ ቢጥል ለቤተ ሰዎቿ አትሰጋም፤ ሁሉም ቀይ ልብስ ለብሰዋልና። ለመኝታዋ የአልጋ ልብስ ትሰራለች፤ ቀሚን በፍታና ሐምራዊ ልብስ ለብሳለች። . . .የቤተ ሰዎቿን ጉዳይ በትጋት ትከታተላለች፤ የስንፍና እንጀራ አትበላም" (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ብሎ ይናገራል። የዚህች ሴት ተግባሯ ከሥራ ጋር የተያያዘ ነው።

በእውነቱ እንደ አሜሪካ ባሉ የምዕራቡ ዓለም አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያት እህቶችንን ኑሮ ካየን በጣም ነው የምናዝነው። ቀን ስምንት ሰዓት ይሰራሉ፤ ከዚያም ቤት ሲገቡ ደግሞ ሌላ ከስምንት እስከ አስር ሰዓት የሚሰራ ሥራ ይጠብቃቸዋል። ያንን ሲያደርጉ ደግሞ የራሱ የሆነ የሥነ ልቦና ጫና አለው። ኑሮ ከባድ ነው። ቲቶ 2፡5 *"ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል ባሎቻቸውን የሚወዱ፣ ልጆቻቸውን የሚወዱ፣ ራሳቸውን የሚገዙና ንጹሆች፣ በቤት የሚሰሩ፣ በጎዎች ለባሎቻቸው የሚታዘዙ፣ እንዲሆኑ ይምከሯቸው"* ብሎ ይናገራል።

የሴቷን የሥራ ድርሻ በተመለከተ ቤት ተኮር ህይወት እንድትኖር ይመክራል። በትምህርት የተለያየ የሙያ ዕውቀት የቀሰመች ልትሆን ትችላለች። ከቤት ውጪ ሥራ ላይ ብትሰማራ ብዙ ገንዘብ ልታገኝ የምትችልም ሆና ትገኝ ይሆናል። ግን ቃሉ የሚመክራት ቤት ተኮር ትሁን ነው። ወንዱ ቤት እርሷ ውጪ ከሆነ ውሎዋ ቤቱ ይፈርሳል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ቤተሰብን ሲመሠርት እርሷን ለቤት ውስጥ የቤተሰብ ህልውና ዋነኛ ሚና የምትጫወት አድርጎ ሾሟታል። ቤት ውስጥ በእርሷ ብቻ የሚደፈን

ቀዳዳ አለ።

በእርግጥ ይህንን ጥቅስ አንስተው ባልተገባ መንገድ ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ ወንዶች ይኖራሉ። አዬ እርሷማ የወደቀ ማንኪያም አታነሳ! ይላሉ። ወይም ሴት በፍጹም ውጪ እየሰራች መግባት የለባትም! ይሄ ኃጢአት ስለሆነ ንስሃ ይግቡ! እያሉ በቴሌቪዥንና ሬዲዮ ሲሰብኩ የሚደመጡ አሉ።

እንዲህ ያለ ትምህርት እንዳለ ባውቅም፤ እንደተባለው ግን አይደለም። ችግርና ግዴታ ስለሆነባት እንጂ ማንኛዋም ሴት ውጪ ስምንት ሰዓት፣ ቤት ውስጥ ደግሞ አስር ሰዓት መስራት አትፈልግም። ነገር ግን ስምምነቱ ካለና በአንድ ልብ ቢጸለይ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ የባልን የእጆቹን ሥራ ሊባርክ፣ ቤተሰቡን ከኑሮ ቀንበር ሊያሳርፍ ይችላል። ልጆች በቤት ውስጥ በእናቶቻቸው እንክብካቤ ስር እንዲያድጉ የእግዚአብሔር ሃሳብ ስለሆነ እርሱ መፍትሄውን ሊሰጥ ይቻለዋል። የሚያስፈልገን ጥበብ፣ እምነት፣ ከጌታ ጋር መስራት እና ራዕይ ነው።

ወላጅ ውጪ ሲሰራ ልጆች ለቴሌቪዥን ተጥለው የስንቱ ሕይወት ተበላሸ። ከዚህና በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች የተነሳ የእግዚአብሔር ቃል የሚስት ድርሻ ቤት ተኮር ይሁን ብሎ ይመክራል።

መጽሐፈ ምሳሌ 31፡10,28-29 *"ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቁ እጅግ ይበልጣል። . . .ልጆችዋ ይነሳሉ፤ ምስጋናዋንም ይናገራሉ፤ ባሏ ደግሞ እንዲህ ብሎ ያመሰግናታል። መልካም ያደረጉ ብዙ ሴቶች አሉ፤ አንቺ ግን ከሁሉ ትበልጫለሽ"* ይላል። ይህ ምስጋና የሽንገላ ንግግር ሊሆን አይችልም። ደግሞም

በዓመት አንድ ቀን ሰዓት ጠብቆ የሚናገረው ነገርም አይደለም። ሚስቱ ከክፋት እየመለሰችው፣ እየተገዛችለት በየዕለቱ ታስገርመዋለች፤ በሃሳብ እየተደግመጡ፣ ደግሞ ውበቷን ሲያየው ቤት ተኮር ሆና ስትተጋ ሲያያት ይህች ሴት ያልተመሰገነች ማን ይመስገን?